የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም ማንዋል

ህዳር /2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ይዘት **ገጽ**

1. ጠቅላላ 1
 1.1 መግቢያ 1
 1.2 አጭር ርዕስ 1
 1.3 ትርጓሜ 1
 1.4 የማንዋሉ ዓላማ 3
  1.4.1 የማንዋሉ ዋና ዓላማ 3
  1.4.2 የማንዋሉ ዝርዝር ዓላማዎች 3
 1.5 የማንዋሉ የተፈፃሚነት ወሰን 3
 1.6 የህግ ማዕቀፎች እና ሠነዶች 3
 1.7 የግዥ መርሆዎች 4
  1.7.1 ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት(Value for Money) 4
  1.7.2 በተወዳዳሪዎች እና ተጫራቾች መካከል አድሎዎ አለማድረግ 7
  1.7.3 ውሳኔ የሚሰጥበት መስፈርት ግልጽ እና ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግ 8
  1.7.4 በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያስከትል ግዥ መፈጸም 9
  1.7.5 ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ የሆነ ግዥ መፈጸም 10
  1.7.6 የግዥ አፈጻጸም ተግባራትን በታማኝነት መፈጸም 10
  1.7.7 በሚሰጡ ውሣኔዎች እና የተወሰዱ እርምጃዎች ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ 11
  1.7.8 የቴክኖሎጂ ፈጠራን ማበረታታት 12
 1.8 ውጤታማ የሆነ ግዥ አስፈላጊነት 12
 1.9 የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ የትኩረት አቅጣጫዎች 12
2. በግዥ አፈጻጸም ላይ የሚሳተፉ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት 13
 2.1 የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ዳይሬክተሮች ቦርድ 13
 2.2 የመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ 14
 2.3 የግዥ የሥራ ክፍል 14
 2.4 የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ወይም ቡድን 15
 2.5 የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ 15
 2.6 የቴክኒክ ገምጋሚ ኮሚቴ 15
 2.7 ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች 16
 2.8 ተጠያቂነት 16

3. የግዥ እቅድ እና ዑደት 17
3.1 የግዥ ፍላጎት መለየት 17
3.2 የግዥ ፍላጎት ማሰባሰብ 18
3.3 የግዥ ፍላጎት ማደራጀት 18
3.4 የግዥ ዘዴ መምረጥ 19
3.5 የግዥ መፈፀሚያ ጊዜ መወሰን 19
3.6 የግዥ እቅድ ይዘት 19
3.7 የግዥ እቅድ የሚጸድቅበት እና የሚሻሻልበት ሁኔታ 20
3.8 ዓመታዊ የግዥ ዕቅድን ይፋ ማድረግ 20
3.9 የግዥ ዑደት 21
3.9.1 የግዥ ፍላጎት መሰብሰብ 21
3.9.2 የጨረታ ሰነድ ወይም የፍላጎት መግለጫ ሠነድ ማዘጋጀት 21
3.9.3 ጨረታን መገምገምና አሸናፊውን መለየት 21
3.9.4 የውል አስተዳደር 22
3.10 የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂ 22
4. የኤሌክትሮኒክ የግዥ ስርዓት እና የግዥ ሠነዶች 23
4.1 የኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት 23
4.2 የግዥ ሰነዶች 23
5. የተወዳዳሪዎች ማሟላት ያለባቸው የቅድመ ብቃት መስፈርቶች 23
6. ዘላቂነት ያለው የግዥ ሥርዓትን ተፈጻሚ ስለማድረግ 24
6.1 የህይወት ዘመን ወጪ ትንተና (Life Cycle Cost Analysis) 24
6.2 የአካባቢ ጥበቃ ታሳቢ ያደረገ የመንግስት ግዥ 28
6.3 . የማህበረሰብን ተጠቃሚነት ታሳቢ ያደረገ ግዥ 29
7. የግዥ ዘዴዎች እና አፈጻጸማቸው 30
7.1 በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ 32
7.2 በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ 32
7.3 ሌሎች ዓለም አቀፍ ግዥዎች 34
7.4 በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ 34
7.4.1 የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ 35
7.4.2 የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ 36
7.4.3 በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ 39
7.5 የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ አፈጻጸም 39

7.5.1 በተገደበ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ ... 39
7.5.2 በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ ... 40
7.6 ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ ... 41
7.7 በልዩ ሁኔታ በማስፈቀድ የሚፈጸም ግዥ ... 42
8. የግዥ ስልቶችና አፈጻጸማቸው ... 43
8.1 የግዥ ስልት ዓይነቶች፤ ... 43
8.2 በኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ ... 44
8.3 በራስ ኃይል የሚፈጸም ግዥ ... 44
9. የግንባታ ሥራ ግዥ የብቃት መስፈርቶች ... 44
9.1 አጠቃላይ ልምድን በተመለከተ ... 44
9.2 ተዛማጅ የስራ ልምድን በተመለከተ ... 45
9.3 ፋይናንስ አቋምን በተመለከተ የሚቀመጠው መስፈርት ... 48
9.4 ዓመታዊ የግብይት መጠን (ተርን ኦቨር) ... 48
9.5 በግንባታ ስራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች ትምህርት እና ብቃት ... 51
9.6 ለግንባታ ስራው የሚያስፈልግ መሳሪያ ... 51
9.7 ከአንድ በላይ የግንባታ ስራዎች ግዥ ላይ የልምድ አያያዝ ... 51
10. የጨረታ ሥነ-ስርዓት ... 52
10.1 የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ ... 52
10.2 የቅድመ ብቃት ጥሪ ... 52
10.3 የጨረታ ሠነድ ... 53
10.4 የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ ... 53
10.5 የብቃትና የግምገማ መስፈርት አዘገጃጀት ... 53
10.6 የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ... 54
10.7 ስለ ናሙና አቀራረብ ... 61
10.8 አጠቃላይና ልዩ የውል ሁኔታዎች ... 62
10.9 ጨረታ ለተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ ... 62
10.10 በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ ... 63
10.11 የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ... 64
10.12 የጨረታ ማስከበሪያ ... 64
10.13 የጨረታ አከፋፈት ... 65
10.14 ጨረታን መገምገም እና ማወዳደር ... 65
10.15 የሒሳብ ስህተቶችን ስለማረም ... 67

10.16 የተሰበረ እና የተጋነነ የጨረታ ዋጋ ... 68
10.17 ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ድርድር ... 69
10.18 ድህረ ግምገማ ... 69
10.19 ጨረታን ስለመሰረዝ ... 69
11. የውል አስተዳደር ... 70
11.1 ውል መፈረም ... 70
11.2 ውል ስለማሻሻል ... 70
11.3 የውል ማስከበሪያ ... 71
11.4 የቅድመ ክፍያ አከፋፈል ... 72
11.5 የዋጋ ማስተካከያ ... 72
11.5.1 የግንባታ ሥራ የዋጋ ማስተካከያ ... 73
11.5.2 ለዕቃ እና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ዋጋ ማስተካከያ ... 77
11.5.3 የምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ... 80
11.6 ርክክብ እና ክፍያ አፈፃፀም ... 80
11.7 ውል ማጠናቀቅ ... 81
11.8 የጉዳት ካሳ ... 81
11.9 ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ... 82
12. አቤቱታ እና ይግባኝ አፈጻጸም ... 82
13. ጥፋተኝነት ሪፖርት የሚቀርብበት እና የሚጣራበት ሥርዓት ... 83
14. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ... 85
14.1 ማንዋሉን ስለማሻሻል ... 85
14.2 ማንዋሉ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን ... 85

1. ጠቅላላ

1.1 መግቢያ

በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1333/2016 አንቀጽ 87(3) መሰረት በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1070/2017 በገንዘብ ሚኒስቴር ጸድቆ ሥራ ላይ መዋሉን ተከትሎ መመሪውን ለማስፈጸም የሚያስችል የግዥ አፈጻጸም ማንዋል ማዘጋጀት አስፈላጊ ሁኖ በመገኘቱ፤

የግዥ አፈጻጸም ማንዋሉ በአዋጁ እና በአፈጻጸም መመሪያ የተገለጹ ደንጋጌዎች ተከትሎ ግዥ ሲፈጸም መከተል ያለበትን የአሰራር ሂደቶች፣በአሰራር ሂደቶች ላይ በየደረጃው የሚኖሩ ኃላፊነቶችንና ውክልናዎችን፣የግዥ መረጃ አያያዝን በሚመለከት የበለጠ ግልጽ ለማድረግ፣

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተለያየ አደራጃጀት እና ባህሪ ያላቸው በመሆኑ ይህንን በየጊዜው እያደገ የመጣውን የስራ ስፋትና የአደረጃጀት ለውጥ ታሳቢ ያደረገ እና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል ተጨማሪ የግዥ ማንዋል በማዘጋጀት ስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሁኖ በመገኘቱ፤

በግዥ መመሪያው ቁጥር 1070/2017 አንቀጽ 7(3) መሰረት ይህ የግዥ አፈጻጸም ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

1.2 አጭር ርዕስ

ይህ ማንዋል የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም ማንዋል ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

1.3 ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጣቸው በስተቀር በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ቃላትና ሀረጎች የተሰጡት ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም በዚህ ማንዋል ውስጥ፡-

1) “አዋጅ” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1333/2016 ነው፡፡

2) **"መመሪያ"** ማለት በፌዴራል መንግስት ባለቤትነት የተያዙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1070/2017 ነው።
3) "**ማንዋል**" ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም ማንዋል ነው።
4) **"ባለስልጣን"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 9 እንደገና የተቋቋመው የፌደራል የመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ነው።
5) **"ቦርድ"** ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቱን በበላይ የሚመሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው።
6) **"የጽሑፍ ግንኙነት"** ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በዕጩ ተወዳዳሪዎች፣ ተጫራቾች እና አቅራቢዎች መካከል በደብዳቤ፣ በፋክስ እና በኤሌክትሮኒክ የሚደረግ የመልዕክት ልውውጥ ነው።
7) **"የበላይ ኃላፊ "** ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቱን በበላይ ኃላፊነት የሚመራ ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ፕሬዝዳንት ወይም በተመሳሳይ ኃላፊነት ያለው ኃላፊ ማለት ነው።
8) **"የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ"** ማለት በበላይ ኃላፊ የሚቋቋም ከአንድ አቅራቢ እና ከዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴዎች ውጭ የሆኑ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚፈጸሙ ግዥዎችን ለየግዥ ዘዴዎች የተቀመጡትን ስርዓቶች ጠብቀው መፈጸማቸውን መርምሮ ውሣኔ የሚሰጥ አካል ነው።
9) "**የግዥ ቡድን/ኮሚቴ**" ማለት የሚፈጽሙት ግዥ ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት በግዥ የሥራ ክፍል ለመፈጸም የማይችሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ ግምገማ ለማከናወን ወይም ለመደራደር በበላይ ኃላፊ የሚቋቋሙ ቡድኖች ወይም ኮሚቴዎች ናቸው።
10) **"የቴክኒክ ገምጋሚ ቡድን/ኮሚቴ**" ማለት "ከግዥ የሥራ ክፍል ወይም የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ አቅም በላይ የሆኑ የቴክኒክ ግምገማዎችን ወይም ናሙናዎችን እንዲገመግሙ የሚቋቋም ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ቴክኒካል ገምጋሚ ቡድን/ኮሚቴ ነው፤
11) **"የጸደቀ የአቅራቢዎች ዝርዝር"** ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቱ በሚያወጣው የቅድመ ብቃት ግምገማ መሰረት ያለፉ እና በቀጣይ ለሚፈጸሙ ግዥዎች ብቁ ሁነው የተመዘገቡ ድርጅቶች ናቸው።
12) **"የታገዱ አቅራቢዎች ዝርዝር**" ማለት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግስት የልማት ድርጅቶች በሚፈጸም ግዥ ላይ እንዳይሳተፉ በባለስልጣኑ የታገዱ አቅራቢዎችን ዝርዝር የያዘ መረጃ ነው።

1.4 የማንዋሉ ዓላማ

1.4.1 የማንዋሉ ዋና ዓላማ

ጸድቆ ወደ ስራ የገባውን የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም መመሪያውን ለማስፈጸም የሚያግዝ የግዥ አፈጻጸም ማንዋል ማዘጋጀት አስፈላጊ ሁኖ በመገኘቱ ነው፣

1.4.2 የማንዋሉ ዝርዝር ዓላማዎች

1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ ስርዓት ወጥነት ያለው፣ ግልፅ ፣ ፍትሀዊ እና አድሎ የሌለበት የስራ ፍሰት እንዲኖረው ለማስቻል፤
2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች መመሪውን ተረድተው የግዥ ሂደት ውጤታማ እና ቀልጣፋ እንዲሆን ለማስቻል፤
3. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ ስርዓት ግልፅነት እና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማስቻል፤

1.5 የማንዋሉ የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ማንዋል የግዥ አፈጻጸም መመሪያው ቁጥር 1070/2017 ተፈጻሚ በሚሆንባቸው በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች እና በሥሩ የሚተዳደሩ ተጠሪ ተቋማት፣ዘርፎች፣ ማዕከላት፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ፕሮጀክቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

1.6 የህግ ማዕቀፎች እና ሠነዶች

1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማንኛውንም ግዥ በሚፈጽሙበት ወቅት ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው የግዥ የህግ ማዕቀፎች እና የአሰራር ሠነዶች፡-

   ሀ) የፌዴራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1333/2016፤

   ለ) የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1070/2017፤

   ሐ) መደበኛ የጨረታ ሠነዶች፤

   መ) የግዥ አፈጻጸም ማንዋሎች፣

ናቸው፡፡

2. ሆኖም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (መ) የተገለጸው የግዥ አፈጻጸም ማንዋል አዋጁንና መመሪያውን መሰረት ተደርጎ የሚዘጋጅ የአሰራር ሰነድ እንጂ የህግ አስገዳጅነት የለውም።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም በመንግስት የግዥና ንብረት አዋጅ ቁጥር 1333/2016 አንቀጽ 3 ንዑስ 2 መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ መንግስታት ወይም ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ካደረገው ወይም ከሚያደርገው ስምምነት ወይም ከስምምነቱ ከመነጨ ግዴታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በስምምነቱ ላይ የተመለከተው የበላይነት ይኖረዋል፤

1.7 የግዥ መርሆዎች

የመንግስት የልማት ደርጅቶች ግዥ ግልጽ በሆኑ ዓላማዎች እና መርሆች የሚመራ ሲሆን፣ በግዥ አፈጻጸም ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር ጉዳዮች በሙሉ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከእነዚህ መሰረታዊ መርሆች ጋር የተሳሰሩ ወይም መርሆችን የማስፈጸም ተልዕኮ ያላቸው ናቸው። በፌዴራል መንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ 1333/2016 አንቀጽ 4 መሰረት ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከታች የተዘረዘሩትን መርሆችን የጠበቀ የግዥ አፈፃጸም መርሆች መከተል የሚኖርባቸው ሲሆን መርሆችም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1.7.1 ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት(Value for Money)

በማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ገንዘብ የሚፈጸም ግዥ ከወጣበት ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ አገልግሎት (Value for Money) ማስገኘት ያለበት ሲሆን፤ይህ መርህ የሚሳካው የሚከተሉት አምስቱ ትክክለኞች(5 Rights) በመባል የሚታወቁትን መሰረታዊ ጉዳዮች በስራ ላይ ከማዋል ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው።

ሀ. ትክክለኛ ጥራት

አንድ ዕቃ፣ ግንባታ ወይም አገልግሎት ትክክለኛ ጥራት አለው የሚባለው ዕቃው፣ ግንባታ ወይም አገልግሎቱ የሚፈለገውን ተግባር በብቃት እንዲያከናውን የሚያስችሉትን ባሕርያት (Quality Characteristics) እንደዕቃው ዓይነት ማቴሪያልን፣ ዲዛይንን፣ ያመራረት ዘዴንና አሠራርን (Production Methods & Workmanship) ልከ ቅርጹን (Dimension) ወዘተ. . አካቶ ሲገኝ ሲሆን፣ እነዚህ ባህርያት በአንድ ዓይነት ዕቃ ላይ በከፍተኛ፣ በዝቅተኛ ወይም በትክክለኛ መጠ ን ሊገኙ ይችላሉ። በሌላ አገላለጽ ለአንድ ለተወሰነ ተግባር የሚያስፈልጉትን ባሕርያት አንድ ዕቃ በከፍተኛ ደረጃ ይዞ ሲገኝ የዕቃው የጥራት ባሕርይ ከሚፈለገው በላይ ነው ማለት ሲቻል፣

በሌላ በኩል ደግሞ ዝቅተኛ የጥራት ባሕርያትን የያዘው ዕቃ የሚፈለግበትን ተግባር ለማከናወን አይችልም ማለት ነው:: ሳይበዛ ወይም ሳያንስ ትክክለኛ የጥራት ባሕርያትን የያዘው ዕቃ በሚገባ ተግባሩን ማከናወን ከመቻሉም በላይ በአንፃራዊ መልኩ ዋጋው ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ካለው ይቀንሳል:: ከዚህም መረዳት የምንችለው ከፍተኛ፣ ዝቅተኛና ትክክለኛ በማለት ጥራትን በሦስት ደረጃዎች መክፈል እንደሚቻል ነው:: ዋጋው ዝቅተኛ ቢሆንም ጥራቱ ዝቅተኛ የሆነ ዕቃ ተግባርን ሊያሟላ አይችልም፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው ዕቃም ተግባርን የማከናወን አቅሙ ከሚፈለገው በላይ ይሆናል፣ ዋጋውም ከፍተኛ ነው:: ስለዚህ ትክክለኛ ጥራት ያለውን ዕቃ ወይም አልግሎት ለመግዛት ልዩ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል::

አንድ ምሣሌ እንመልከት፡- እንደሚታዉቀው የኤሌክትሪክ ኃይልን ለማስተላለፍ በጥቅም ላይ የሚውለው ማቴሪያል መዳብ (Copper) ነው:: የመዳብ ኤሌክትሪክ የማስተላለፍ ባሕርይ (Conductivity) በጣም ጥሩ ነው:: የብር (Silver) ኤሌክትሪክ ማስተላለፍ ባሕርይ ደግሞ ከመዳብ ከፍ ያለ ነው:: ነገር ግን ብር ከመዳብ ይወደዳል:: ስለዚህ ለሚፈለገው ተግባር መዳብ ትክክለኛ ጥራት ያለው በመሆኑ ሥራ ላይ የሚውል ሲሆን፣ ብር ከፍተኛ ጥራት ያለውና የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠት ቢችልም ከValue for Money ፅንሰ ኃሳብ አንፃር ለዚህ ተግባር አይመረጥም ማለት ነው::

ለ. <u>ትክክለኛ መጠን</u>

የሚገዙ ዕቃዎች መጠን በማነሱ ምክንያት በመንግስት የልማት ድርጅቱ በሚያከናውነው ተግባር ላይ ችግር እንዳይፈጠር፣ ከሚፈለገው በላይ በብዛት በመገዛታቸው ምክንያት ደግሞ የማከማቻ ቦታ ችግር ወይም ተጨማሪ ወጪ እንዳያስከትል ዕቃዎች በትክክለኛው መጠን መገዛት ይኖርባቸዋል:: ይህ የትክክለኛ መጠን መሠረተ ሀሳብ የሚያተኩረው በዕቃ ግምጃ ቤት በሚከማቹ ዕቃዎች ላይ በመሆኑ በተሟላ ሁኔታ በተጤኑና ተስማሚ በሆኑ የዕቃ ክምችት ቁጥጥር ዘዴዎች በመጠቀም የሚገዛውን ትክክለኛ መጠን ማዘዝ ይገባል:: በአጠቃላይ ግዥ ሊፈጸም የሚገባው ለሚያስፈልገው ሥራ የሚበቃውን መጠን በመለየት፣ በማቀድና ግዥ ፈጻሚ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የጨረታ ሰነዳቸውን በሚያዘጋጁበት ወቅት ትክክለኛ መጠን መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል::

ሐ. <u>ትክክለኛ ዋጋ</u>

ይህ መሰረተ ሀሳብ ከላይ ትክክለኛ ጥራት ተብሎ ከተገለጸው ጋር በጣም የተሳሰረ ነው:: ለምንገዛው ዕቃ እንድንከፍል የምንጠየቀውን ዋጋ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ የውድድር መንፈስ እንዲሰፍን በማድረግ እንደሁኔታው ከታወቀ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ

አገር አምራች ወይም የልማት ድርጅቶች በራሳቸው በሚያደርጉት ጥናት በሚገኝ የገበያ ዋጋ ወደ ትክክለኛ ዋጋ መቅረብ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የቀጥታ ግዥ ጨምሮ የዋጋ ድርድር በመመሪያው በተቀመጡ ድንጋጌዎች መሰረት ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ በአጠቃላይ ትክክለኛ ዋጋ ማለት ከወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጋር የተጣጣመ፣ ያልተጋነነ እና ያልተሰበረ መሆን ይኖርበታል፡፡

መ ትክክለኛ ምንጭ

ትክክለኛ ምንጭ መሠረተ ኃሳብ ትክክለኛ አቅራቢዎችን፣ ሥራ ተቋራጮችን፣ አማካሪዎችን እና አገልግሎት ሰጪዎችን ከመምረጥ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህም ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች ግዥ የሚሳተፉ ድርጅቶች

- ህጋዊነት፣
- የቴክኒክ ብቃት፣
- ድርጅታዊ አቋም፣
- እንደአስፈላጊነቱ የፋይናንስ አቋም፣
- እንደአስፈላጊነቱ ከሽያጭ በኋላ ተገቢውን ድጋፍ (After sales Support Services) መስጠት መቻሉን፣ ...ወዘተ

የሚሉትን መመዘኛዎች መሰረት በማድረግ አቅራቢዎችን፣ ሥራ ተቋራጮችን፣ አማካሪዎችን እና አገልግሎት ሰጪዎችን ግምገማ (Evaluation) በማካሄድ መምረጥ ይገባል፡፡

ሠ. ትክክለኛ ጊዜ

ትክክለኛ ጊዜ ማለት ዕቃ፣ ግንባታ ወይም አገልግሎት በሚፈለግበት ጊዜ ከመገኘቱ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በትክክለኛው ጊዜ ሳይደርስ የቀረ ግዥ ክንውንን የሚያስተጓጉል እንደሚሆን ሁሉ ከሚፈለግበት ጊዜ ቀድሞ የቀረበ ግዥ ደግሞ በሥራ ላይ እስኪውል ድረስ ማከማቸትን ስለሚጠይቅ ተጨማሪ ወጪን ያስከትላል፡፡ የትክክለኛ ጊዜ አስተሳሰብ ምንጭ ከገንዘብ ጋር በቀጥታ የተያያዘ እንደመሆኑ መጠን የግዥ ሂደቱ የሚወስደውን የጊዜ ግምትን /Lead Time/ በጥንቃቄ ማስላት ያስፈልጋል፡፡ ከጨረታ ሰነድ ዝግጅት እስከ ርክክብ የሚወስደውን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

ግዥው ከሚፈለግበት ጊዜ ተነስቶ ወደኋላ ያሉትን ሂደቶች በሚገባ በማጠናቀቅ መቼ አስተዳደራዊ ጉዳዮች መሠራት እንዳለባቸው፣ የግዥ ቅድመ-ዝግጅት መቼ ተጀምሮ መቼ ግዥ መፈጸም እንዳለበት ወዘተ. . . ማስላት ይቻላል፡፡ አንዳንድ ሂደቶች (በተለይም በውጭ አገር ግዥ) ከተገመተው ውጪ ሊሆኑ ቢችሉም ከተገኘ ልምድ አማራጭ እርምጃዎችን በቅድሚያ አስቦ ተግባራዊ በማድረግ ቢያንስ ወደ ትክክለኛ ጊዜ መሠረተ-ሃሳብ መቅረብ ይቻላል፡፡ ወቅታዊ ለሆኑ

ዕቃዎች (Seasonal Items) ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ በሚፈለጉበት ጊዜ እንዲቀርብ ማድረግ ይቻላል፡፡

1.7.2 በተወዳዳሪዎች እና ተጫራቾች መካከል አድሎዎ አለማድረግ

- በግዥ አፈጻጸም ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሳተፍ ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና አቅራቢዎች እኩል የመወዳደር እና ውል የመግባት ዕድል እንዲያገኙ የማድረግ ተግባር ነው፡፡ ይህ ማለት ሁሉንም ተወዳዳሪዎች በእኩል በመመልከት፣ የሚሰጡ ውሳኔዎች በጥቅም፣ በጓደኝነት፤ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በቀለም፣ በብሔር፣ በፆታ፣ በፖለቲካ፣ በአካል ጉዳት፣ በቋንቋ፣ በሃብት ወይም ከሌሎች የውጭ ተጽእኖ ነፃ በሆነ መልኩ በመስጠት በፍትሀዊነት በእኩል አይን መስራት ነው፡፡

- በግዥ ሂደት ውስጥ ከአድልኦ ነፃ የሆነ አሠራር መፍጠር ማለት በአጭሩ ተጫራቾችን በሙሉ በእኩል ዓይን ከማየት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህን የግዥ መርሆ ወደ ተግባር በመለወጥ ረገድ ከሌሎች የግዥ ዘዴዎች ይልቅ ግልጽ ጨረታ ተመራጭነት አለው፡፡ ምክንያቱም በግልጽ ጨረታ አፈጻጸም የጨረታ ማስታወቂያ በይፋ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ስለሚገለጽ፣ ሰፊ የጨረታ ማቅረቢያ ጊዜ ስለሚኖር እና ሁሉንም ተጫራቾች ሊያሳትፍ የሚችል ስፔሲፊኬሽን ስለሚዘጋጅ ነው፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ የትኛውንም ድርጅት በተለየ ሁኔታ ሊጠቅም የማይችል የማወዳደሪያ መስፈርት በማዘጋጀትና ይህንንም የጨረታ ሠነድ ውስጥ በማካተት በቅድሚያ ተጫራቾች እንዲያውቁት ማድረግ ከአድልዎ ነፃ ለሆነ አሠራር አንዱና አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡
- እንዲሁም በጨረታ ጥሪ ለሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች በቂ መረጃ ማግኘታቸውን፣በጨረታ ሂደት ላይ የሚደረጉ ማናቸውምለውጦች ለሁሉም ተወዳዳሪዎች ተደራሽ መሆናቸውን፣ በጨረታ ሰነዱ የተገለጸው ማንኛውም የመወዳደሪያ መስፈርትም ሆነ የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር የተወሰነ ዕጩ ተወዳዳሪን ሊጠቅም በሚችል መልኩ አለመዘጋጀቱን፣ የጨረታው ውጤት ለሁሉም ተሳታፊዎች በእኩል ጊዜ መገለጹን ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡
- የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ግልፅነትን ማዕከል በማድረግ ሥራውን ያለአድልዎ የመፈፀም ግዴታ፣ ሙያዊ ግዴታውን በሚወጣበት ወቅት ሆንብሎ ወይም በቸልተኝነት

ሕግን በመጣስ ማንኛውንም ሰው፣ ቡድን ወይም አካል የሚጎዳ አድሏዊ ተግባር መፈፀም የለበትም፡፡

1.7.3 ውሳኔ የሚሰጥበት መስፈርት ግልጽ እና ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግ

- በግዥ አፈፃፀም ውስጥ ግልጸኝነት ማለት አንዳንድ መረጃዎችን በሚስጥር ለማስቀመጥ ህጋዊ ምክንያቶች እስከሌሉ ድረስ በግዥ ሂደት ላይ ያለው መረጃ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ማለትም ለሥራ ተቋራጮች፣ አቅራቢዎች፣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ አማካሪዎች እና ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ እና ለቁጥጥር አመቺ የሆኑ ሥርዓቶችን መዘርጋት ማለት ነው፡፡
- በጨረታ አከፋፈት ሥነ ሥርዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ተወካዮቻቸው እንዲገኙ ማድረግ የግልጽነት መገለጫ እንደሆነ ቢቆጠርም አብዛኛውን ጊዜ በጨረታ መክፈቻ ዕለት ተጫራቾች ያቀረቡት ዋጋ ብቻ ስለሚነበብና ከዋጋ ውጭ ያሉ ሌሎች በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ተጫራቾች እንዲያውቋቸው ስለማይደረግ በጨረታ መክፈቻ ዕለት የሚካሄደውን ተጫራቾች ያቀረቡትን ዋጋ በዕለቱ ለተገኙት ተጫራቾች ግልጽ የማድረጉ ሁኔታ የግልጽነት (Transparency) መገለጫ ብቸኛ አማራጭ አድርጐ መውሰድ አሳሳች ነው፡፡
- በተጨማሪ ግልጽ የሆነ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መኖር የተሟላ የጨረታ ሠነድ ማዘጋጀትን እና ከጨረታ አከፋፈት ጀምሮ በየደረጃው ያሉ የጨረታ ግምገማና ውድድሮችን ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልጽ የማድረግ ሁኔታን ባይቻል እንኳን የጨረታ ውሣኔዎችና ውሣኔው ላይ ለመድረስ ግምገማ የተካሄደባቸው ሠነዶች፣ በተጫራቾች የሚታዩበትን ስልት መቀየስ ይፈልጋል፡፡ በጨረታ ግምገማ ለወደቁት ተጫራቾች በውድድሩ መሸነፋቸውንና የተሸነፉበትን ምክንያት ማሳወቅም ከግልፅነት መገለጫዎች አንዱ ነው፡፡
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ግዥ በሚፈጽሙበት ወቅት የሚከተሉትን የግልጸኝነት መገለጫዎች ጠብቀው መፈጸም አለባቸው፡፡

    - ✓ የሚዘጋጁ የጨረታ ሠነዶች ለሁሉም ተወዳዳሪዎች እኩል የመወዳደር ዕድል በሚሰጥ መልኩ በግልጽ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣
    - ✓ የሚወጡ ጨረታዎች በግዥ የህግ ማዕቀፎች ላይ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ መሠረት ተጫራቾች የመጫረቻ ሠነዳቸውን አዘጋጅተው ለማቅረብ የሚችሉበት በቂ ጊዜ የተሰጣቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

- ✓ የሚዘጋጁ መገምገሚያ መስፈርቶች እና የፍላጎት መግለጫዎች ጨረታው ከመውጣቱ በፊት መዘጋጀቱን እና የሚዘጋጁ መስፈርቶች በግልጽ የተቀመጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- ✓ በጨረታ ሰነዱ ላይ ከዕጩ ተጫራቾች ለሚቀርብ የማብራሪያ እና የማሻሻያ ጥያቄዎች በወቅቱ ምላሽ መስጠት የተሠጠው ምላሽ ከግዥ ህጉ አኳያ መሆኑን እና ጥያቄውን ያቀረበውን ተጫራች ጨምሮ ለሁሉም ተጫራቾች ተደራሽ መደረጉን ማረጋገጥ፣
- ✓ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ተጫራቾች ለሚያቀርቡት የአቤቱታ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ግልጽ በሆነ መልኩ በህጉ ላይ በተቀመጠው ቀነ ገደብ ውስጥ ምላሽ መስጠት፣
- ✓ በግዥ አፈጻጸም ሂደት ላይ የሚያከናውኗቸውን የሥራ ተግባራትና የሚሰጠውን ውሳኔ ግልጽ ማድረግን፣

ያካትታል፡፡

1.7.4 በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያስከትል ግዥ መፈጸም

በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚፈጸሙ ግዥዎች ለአካባቢው ማህበረሰብ ያላቸውን አዎንታዊ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ተጽዕኖዎችን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም የመንግስት የልማት ድርጅቶች እንደአስፈላጊነቱ የዕቃዎች እና የግንባታ ሥራዎች ግዥን በሚፈጽሙበት ወቅት በአዋጁ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 8 ፊደል ተራ "ለ" የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና መሠረት በማድረግ ግዥ ለመፈፀም በመመሪያ የተመለከቱትን አሰራር ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡

ስለሆነም የሰነድ ዝግጅት፣ መገምገሚያ መስፈርት፣ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ዝግጅት በሚያደርጉበት ወቅት የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተናን ከግምት ማስገባት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ግዥው ከአካባቢ ብክለት የጸዳ፣ መልሶ መጠቀምን እና የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

1.7.5 ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ የሆነ ግዥ መፈጸም

የግዥ ተግባር በቅልጥፍና ባለመከናወኑ ምክንያት ለበርካታ ፕሮጀክቶች መጓተት እንደምክንያት ከመቆጠሩም በላይ ማነቆ እንደሆነ በስፋት ይነገራል፡፡ ለዚህም ነው ግዥን በቅልጥፍና (Efficiently) የማከናወኑ ሁኔታ ከፍተኛ ቦታ እያገኘ የመጣው፡፡

በግዥ አፈጻጸም ያልተማከለ አሠራርን (Decentralization) መፍጠር የግዥ ተግባርን ቀልጣፋ ከማድረግ ጋር ይያያዛል፡፡ ያልተማከለ አሠራር መፍጠር ማለት በየደረጃው አላስፈላጊ የሆኑ የቁጥጥር ሥርዓቶችንና ሪፖርት የሚደረግላቸውን አካላት መቀነስ ማለት ነው፡፡ ይህን ለማድረግ በቅድሚያ በግዥ ሂደት ውስጥ የየራሳቸው ድርሻ ያላቸው ሠራተኞች በሙሉ ሥርዓትንና መመሪያን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ቀልጣፋ የግዥ እንቅስቃሴ ለማድረግ ሙያዊ ብቃትና ልምድ ስለሚጠይቅ በግዥ ተግባር ላይ የተሠማሩ ሠራተኞች የግዥ ሙያና ልምዱ ስለሚያጥራቸው በግዥ ሙያ ተከታታይነት ያለዉ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ለቀልጣፋ እና ውጤታማ የግዥ እንቅስቃሴ የጐላ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

በግዥ አፈፃፀም ትርጓሜ ቁጠባ ማለት ግዥን ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት መፈፀም ሳይሆን ግዥን ስፔሲፊኬሽኑንና ሌሎች በጨረታ ሠነድ ላይ የተመለከቱ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት (Lowest Evaluated Bidder) መፈፀም ማለት ነው፡፡

ግዥን በግልፅ ጨረታ መፈፀም የተጫራቾችን ቁጥር ስለሚጨምር ከበርካታ ተሳትፎና ውድድር ሊገኝ የሚችለውን የዋጋ ቅናሽ በማምጣት ቁጠባን ያስገኛል፡፡ በአንድ ጊዜ ግዥያቸው ሊፈጸም የሚችሉትን ከፋፍሎ በተለያየ ጊዜ መፈጸም የመንግስት የልማት ድርጅቱን ጥቅም የሚያሳጣ በመሆኑ በአንድ ላይ በማድረግ በጥቅሉ መፈጸሙ የተሻለ ቁጠባ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

1.7.6 የግዥ አፈጻጸም ተግባራትን በታማኝነት መፈጸም

- በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪነት በግዥ ውስጥ የሚሳተፉ አካላት ግዥን መፈጸም ያለባቸው በታማኝነት፣ በቅንነት እና በአገልጋይነት መንፈስ መሆን ይኖርበታል፡፡ የግዥ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በግዥ አፈፃፀም ላይ የህዝብን ጥቅም በማስጠበቅ እና በማስቀደም የጋራ ስነ-ምግባር እሴቶችን፣ መርሆችን እና ደንቦችን ወጥነት ባለው መልኩ በመተግበር ለተገልጋይ ታማኝነትን ማሳየት አለባቸው፡፡

- የግዥ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ግዥ ሲፈጽሙ ከግል ጥቅም ይልቅ ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት፣ለህግ ማዕቀፎች ታማኝ መሆን፣ በግዥ አፈጻጸም ሂደት የጨረታ ግምገማ እና ውጤት ማፅደቅ ላይ በታማኝነት ማከናወን፣ ግልጽና ታማኝ በመሆን ኃላፊነትን በትክክል መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡
- በግዥ ሥራ አፈፃፀም ላይ ተሳታፊ የሚሆን ሁሉ የኃላፊነት ስሜት የሚሰማው፣ ለተሻለ ለውጥ የሚሰራ፣ የተቋሙን ስም የሚጠብቅ፤ ተቀናጅቶና ተግባብቶ ስራን የማከናወን ባህልን የሚያዳብር ሙያውን በብቃት መወጣት፣ የዜጎችና የሕዝቡን ጥቅሞች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እንዲሁም ልዩ ትኩረት የሚሹ አካላትን በተገቢው መንገድ በታማኝነትና በቅንነት ማገልገል ተገቢ ይሆናል፡፡

1.7.7 በሚሰጡ ውሣኔዎች እና የተወሰዱ እርምጃዎች ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ

- የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ለኪሣራ በሚዳርግ ሁኔታ ግዥ የፈጸሙ የግዥ ሠራተኞች ላይ የዲስፒሊን እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ጥፋቱ ሆን ተብሎ በግዴለሽነት መፈጸሙ ከተረጋገጠ ከዲስፒሊን እርምጃም ያለፈ ቅጣት ሊያስከትልም ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ በሕዝብ ተጠያቂ የመሆን መርህ በሁሉም የግዥ ሂደት እና ደረጃዎች ላይ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ተጠያቂነት በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚገኙ የግዥ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ለተወሰኑ ውሳኔዎች እና ውጤቶቹ የማብራራት፣ የማስረዳት እና ኃላፊነት የመውሰድ ግዴታ ነው፡፡ ተጠያቂነት በግዥ አፈፃጸም ሥራ ላይ የግዥው አፈፃፀም ሂደት በምን ውጤት ላይ እንደሚገኝ እና ውሳኔዎቹ እንዴት እንደተወሰኑ ምላሽ ከመስጠት ጋር የተያያዘ ነው፡፡
- በተጨማሪም ለድርጊቱ እና ለውጤቱ በህግ ስልጣን ለተሰጣቸው ምላሽ የመስጠት ሁኔታ ሲሆን፤ ኃላፊነትን ለመቀበል እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማብራሪያዎችን ወይም ምክንያቶችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆንን ያካትታል፡፡
- በውሳኔዎቻቸውና ባከናወኗቸው ሥራዎች ላይ ለሚቀርብላቸው ተገቢ የሆነ የማጣራት ሥራ ራሳቸውን ዝግጁ የማድረግ፣ በተፈለጉ ጊዜ የመቅረብ ወይም የመገኘት ወይም ከሚጣራው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለውን መረጃ የማቅረብ እና የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

- የግዥ የህግ ማእቀፎችን የመፈጸም ግዴታ፣ በግዥ ስራ ላይ የተሰጠን ግዴታ በወቅቱ መወጣት፣ የግዥ እቅድ እና የአፈጻጸም ሪፖርት በወቅቱ ይፋ ማድረግ፡፡

1.7.8 የቴክኖሎጂ ፈጠራን ማበረታት

በግሉ ዘርፍ ውስጥ ለአሁንና ለወደፊት የአገልግሎት ፍላጎቶች የሚሰጡትን ምላሽ በማነቃቃት አዳዲስ ፈጠራዎችን ማበረታታት ይኖርበታል፡፡ ይህ ማለት አዳዲስ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ፍላጎቶችን በማመንጨት ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲውሉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ በግዥ አፈጻጸም ውስጥ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመጠቀም የግዥ ሂደቱን ቀልጣፋ፣ግልጽነት ያለው፣እኩል ተደራሽነትን ታሳቢ የሚያደርግ፣ የተሻለ አገልግሎት የሚሰጥ፣ አዳዲስ ፈጠራን የሚያበረታታ፣ ወደፊት የሚፈጠሩ ፍላጎቶችን ያማከለ እንዲሁም ዘለቄታዊነትን ታሳቢ ያደረገ በተጨማሪም ለህብረተሰቡ ፍላጎት ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ እና የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን በሚያጎላ መልኩ የመጠቀምን ሂደት የሚደግፍ ከመሆኑም በላይ እንደ አገርም ሥራዎች በአጠቃላይ ወደ ዲጂታላይዝ እየተቀየሩ ከመሆኑ ጋር በተገናኘ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የቴክሎጂ ፈጠራን በግዥ ሂደት ውስጥ በማካተት አገርንና የፈጠራ ባለቤቶችን በሚጠቅም መልኩ መጠቀም አለባቸው፡፡

1.8 ውጤታማ የሆነ ግዥ አስፈላጊነት

በመንግስት የልማት ድርጅቶች ለግዥ የሚውለው ገንዘብ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ የኢንቨስትመንት ምንጭ ነው፡፡እነዚህን ኢንቨስትመንቶች ከመሰረተ ልማት መስፋፋትና የተቋምንና የሰው ኃይል አቅምን ከመገንባት አኳያ ለአገር ዕድገት መሠረት ጁዓላሉ፡፡ ስለዚህ የግዥ አፈፃፀምን ውጤታማ ማድረግ ለአገር ኢኮኖሚ የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

1.9 የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ የትኩረት አቅጣጫዎች

- አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት □ዴ ለመ□□ም የሚፈልጋቸው ዕቃዎችን፣ የግንባታ □ርአ ስራዎችንና አገልግሎቶችን ግዥ በሚፈጽምበት ጊዜ ለቁጠባና ለአፈፃፀም ብቃት ተገቢውን ትኩረት መስጠት፣
- የተመደበው ገንዘብ ለታቀዱ □ዴ□ች ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣ ለሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች □መዉቴ□ር ዕትል የሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ ናቸው፡፡፡

2. በግዥ አፈጻጸም ላይ የሚሳተፉ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት

በግዥ አፈጻም ላይ የሚኖረው ኃላፊነት እና ተግባር የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባላቸው የስራ ባህሪ እና አደረጃጀት መሰረት የሚወሰን ሆኖ፣

1. ከግዥ ዘዴ መወሰን ጀምሮ የግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በግዥ አዋጁ እና በአፈጻጸም መመሪያው መሰረት መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችንና ሌሎች መረጃዎችን ተንትኖ ለውሳኔ የማቅረብ ኃላፊነት ግዥን የሚመሩ የስራ ክፍሎች፣በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች እና ኮሚቴዎች ይሆናሉ፡ ፡
2. የቀረቡትን ቅድመ ሁኔታዎች እና ትንተናዎች መሰረት በማድረግ የሚቀርቡ የውሳኔ ኃሳቦችን ውሳኔ በመስጠት ሂደት የሚሳተፉት ደግሞ የመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ፣በበላይ ኃላፊው ውክልና የሚሰጣቸው ኃላፊዎች ናቸው፡፡

2.1 የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ስልጣንና ተግባር በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 4 ስር በተገለጹት መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

2.2 የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ዳይሬክተሮች ቦርድ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ዳይሬክተሮች ቦርድ ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚኖራቸው ኃላፊነትና ተግባር በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 6 ስር በተገለጹት መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም፤

1. ለመንግስት የልማት ድርጅቱ ከጸደቀው በጀት ውጪ ተጨማሪ በጀት የሚጠይቁ ግዥዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤
2. የዕለት ተዕለት የግዥ ዝርዝር አፈጻጸም (Operational) በሆኑ ጉዳዮች ውሳኔ ላይ የማይሳተፍ ቢሆንም የግዥውን ውጤታማነት ለመገምገም የሚያስችል አሰራር ስርዓት በመዘርጋት የግዥ አፈጻጸሙን ላይ ግምገማ ያደርጋል፤
3. የግዥ አዋጁ እና የአፈጻጸም መመሪያው ተፈፃሚነት በበላይነት ይከታተላል፡፡

2.3 የመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ

የመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚኖራቸው ኃላፊነትና ተግባር በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 7 ስር በተገለጹት መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪም፤

1. በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግዥ ዘዴዎችን የግዥ ሂደታቸው ከመጀመሩ በፊት መርምሮ ያጸድቃል፤
2. ከአንድ አቅራቢ እና በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸሙ ግዥዎችን የግምገማ ውሳኔ ኃሳቦችን መርምሮ ማጽደቅ ወይም በሚወክለው አካል እንዲጸድቅ ውክልና ይሰጣል፣
3. ዋጋ ማስተካከያዎችን ጨምሮ የውል ማሻሻያዎችን ያጸድቃል ወይም ውክልና ይሰጣል፤
4. በመንግስት የልማት ድርጅቱ ስር ላሉ ተጠሪ ተቋማት፣ዘርፎች፣ማዕከላት፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወይም ሪጅኖች እና ፕሮጀክቶችን ለሚመሩ ኃላፊዎች የግዥ ዕቅድን ከማጽደቅ ውጪ ያሉ በዕቅድ የተያዘ ግዥ ለመፈጸም በመንግስት የልማት ድርጅቱ በሚሰጣቸው የገንዘብ ገደብ ውክልና መሰረት በሚፈጽሟቸው ግዥዎችም ላይ የመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚኖረውን ኃላፊነት እንዲኖራቸው ውክልና ይሰጣል፤
5. በመንግስት የልማት ድርጅቱ ስር ላሉ ተጠሪ ተቋማት፣ዘርፎች፣ ማዕከላት፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወይም ሪጅኖች እና ፕሮጀክቶች የራሳቸው አጽዳቂ ኮሚቴ ሊያቋቁሙ ይችላሉ፤

2.4 የግዥ የሥራ ክፍል

የግዥ የስራ ክፍል ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚኖራቸው ኃላፊነትና ተግባር በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 8 ስር በተገለጹት መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪም፤

1. የግዥ እቅድ ለማዘጋጀት ከየስራ ክፍሎች የግዥ ፍላጎቶችን ከማሰባሰብ ጀምሮ በተለያየ የግዥ ዘዴ የሚፈጸሙ ግዥዎችን በመገምገም የውሳኔ ኃሳብ ማቅረብ እና የግዥ መረጃዎችን አደራጅቶ መያዝ፣
2. የገበያ ጥናት የስራ ክፍል ወይም ባለሙያ እንዲኖር በማድረግ የገበያ ጥናት መረጃዎችን አጠናክሮ መያዝ እና ለግምገማ እና ለዋጋ ማስተካከያ ዓላማ እንዲውሉ ማድረግ፣ሆኖም የገበያ ጥናቱን የሚያካሂዱት በግዥ ሂደቱ ላይ መሳተፍ አይኖርባቸውም።

2.5 የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ወይም ቡድን

የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚኖራቸው ኃላፊነትና ተግባር በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 8 ስር በተገለጹት መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪም፤

1. ይህ ኮሚቴ ወይም ቡድን ከፍተኛ ግዥ በሚፈጸምባቸው እና የግዥ ስራውን በግዥ የስራ ክፍል ብቻ ለማከናወን አስቸጋሪ በሚሆንባቸው የመንግስት የልማት ድርጅት የበላይ ኃላፊ የሚቋቋም ነው፤
2. በተለያየ የግዥ ዘዴ ለሚፈጸሙት ግዥዎች የጨረታ ሠነድ ወይም የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት እና የግዥ ግምገማዎችን በመገምገም ለሚያጸድቀው አካል የውሳኔ ኃሳብ ማቅረብ፤
3. ሌሎች ከግዥ አፈጻጸም ሂደት ጋር የተየያዙ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊው በሚሰጠው ውክልና መሰረት ያከናውናል፡፡

2.6 የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ

የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የሚኖረው ኃላፊነትና ተግባር በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 9 ስር በተገለጹት መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪም፤

1. ከአንድ አቅራቢ እና በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸሙ ግዥዎችን ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ለሚፈጸሙ ግዥዎች ከግዥ የስራ ክፍል ወይም በገምጋሚ ኮሚቴ ተገምግሞ በበላይ ኃላፊ የሚመራለትን የግምገማ ውሳኔ ኃሳቦችን መርምሮ ማጽደቅ፤
2. አጠቃላይ የግዥ ግምገማ ሂደቱን ጨረታው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት ለማጠናቀቅ የመንግስት የልማት ድርጅቱ በሚያዘጋጀው የውስጥ አሰራር በሚያስቀምጠው ቀናት ውስጥ ግዥውን ማጽደቅ አለባቸው፡፡
3. በመንግስት የልማት ድርጅቱ ስር ላሉ ተጠሪ ተቋማት፣ዘርፎች፣ ማዕከላት፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወይም ሪጅኖች እና ፕሮጀክቶች የሚቋቋመው አጽዳቂ ኮሚቴ በዚሁ መሰረት ስራቸውን ያከናውናሉ፡፡

2.7 የቴክኒክ ገምጋሚ ኮሚቴ

የቴክኒክ ኮሚቴ የሚኖረው ኃላፊነትና ተግባር በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 10 ስር በተገለጹት መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም፤

1. የጥቅም ግጭት የሌለባቸው መሆኑን በመግለጽ የሥነ ምግባር ደንቡን መፈረም አለባቸው፤
2. በተለየ ሁኔታ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተጨማሪ ትዕዛዝ ካልተሰጣቸው በስተቀር ኮሚቴው ከቴክኒክ ግምገማ ውጪ ዋጋ እና ተዛማጅ ግምገማዎችን ማከናወን የለባቸውም፤
3. በጨረታ ሠነድ ላይ ከተቀመጠ የቴክኒክ መስፈርት ውጪ ግምገማ ማድረግ የለባቸውም፤
4. አጠቃላይ የግዥ ግምገማ ሂደቱን ጨረታው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት ለማጠናቀቅ የመንግስት የልማት ድርጅቱ በሚያዘጋጀው የውስጥ አሰራር በሚያስቀምጠው ቀናት ውስጥ የቴክኒክ ግምገማውን ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

2.8 ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች

በመንግስት የልማት ድርጅቶች የስራ መዋቅር እና የስራ ባህሪይ የሚወሰን ሆኖ ተጠቃሚ የስራ ክፍሎች በግዥ አፈጻጸም ሂደት ውስጥ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ሊኖራቸው ይችላል፡፡

1. ለግዥ ዕቅድ ግብዓት የሚሆን የግዥ ፍላጎታቸውን የግዥው ዓይነትና መጠን፣ የጥራት ደረጃን እና ግዥ የሚፈልጉበትን ጊዜ እንዲሁም ለግዥው የተያዘውን በጀት ያካተተ መረጃ በግዥ ፍላጎት ማሰባሰቢያ ጊዜ ውስጥ ግዥውን ለሚመራው የስራ ክፍል መላክ አለባቸው፤
2. እንደአስፈላጊነቱ በጸደቀው የግዥ እቅድ መሰረት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ፣ የጨረታ የመነሻ ዋጋ ግምት እና ሌሎች ተፈላጊ ሰነዶች እና መረጃዎችን በመጥቀስ እና በማያያዝ የግዥ ጥያቄ ማቅረብ፤
3. እንደአስፈላጊነቱ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሲታዘዙ ወይም ሲሰየሙ በጨረታ አከፋፈት፣በቴክኒክና በሌሎች የግዥ ግምገማዎች፣በድርድር እና በውል አስተዳደር ስራዎች ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

2.9 ተጠያቂነት

የመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊዎች እና ዘርፎችን የሚመሩ ኃላፊዎች፣ የግዥ የሥራ ክፍሎችን የሚመሩ ኃላፊዎች፣ ለግዥ ሥራ የተመደቡ ሠራተኞች፣ ባለሙያዎች፣የግዥ አጽዳቂና ቴክኒኪ ኮሚቴዎች እንዲሁም ሌሎች በግዥ ሥራ እና ውሳኔ ላይ የሚሳተፉ የኮሚቴዎች

አባላቶች ይህንን መመሪያ እና ሕግን ያልጠበቁ ስራዎች ከፈጸሙ ለተፈጸሙ ግድፈቶች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

3. የግዥ እቅድ እና ዑደት

1. የመንግስት የልማት ድርጅቱ የበጀት ዓመቱ ከመጀመሩ በፊት በሚቀጥለው በጀት ዓመት የታቀዱ የስራ ፕሮግራሞቹን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ግዥ በወቅቱ ለመፈፀም የሚያስችል በበጀት፣ በጊዜ እና bመርሃ ግብር የተደገፈ የግዥ እቅድ በማዘጋጀት በበላይ ኃላፊ በማጸደቅ ስራ ላይ ማዋል አለበት፤
2. በመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚፈጸሙ ግዥዎች እስከተቻለ ድረስ በጸደቀው ዕቅድ መሰረት መፈጸም አለበት፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ፣ በዕቀድ ውስጥ የተካተቱ ቢሆንም በአስገዳጅ ሁኔታ በዕቅዱ ውስጥ ከተገለጸው በተለየ ሁኔታ ግዥ መፈጸም ሲያስፈልግ እንዲሁም ጥቃቅን ግዢዎችን መፈጸም አስፈላጊ መሆኑ ሲታመነበት እና በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ውክልና በተሰጠው አካል ሲፈቅድ ከዕቅድ ውጭ ግዥዎች ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡

3.1 የግዥ ፍላጎት መለየት

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ ፍላጎት በሚያዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡-

1. ፍላጎቱ በመንግስት የልማት ድርጅቱ ውስጥ ባለ እና ጥቅም ላይ ባልዋለ ሌላ ሃብት ወይም ንብረት ሊሟላ የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ፤
2. ፍላጎቱ በገበያ ላይ በሚገኝ ምርት ወይንም አገልግሎት ሊሟላ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፣
3. የግዥ ፍላጎቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ እሴቶችን ያላካተተ እና ድርጅቱን ለአላስፈላጊ ወጪ የማይዳርግ መሆኑን ማረጋገጥ፣
4. በተለይ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ ታስበው የሚከናወኑ ግዥዎች በሚሆኑበት ጊዜ የግዥ ፍላጎቱ ወደፊት የሚፈጠር የፍላጎት እድገትን ያገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ፤
5. አስገዳጅ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ መደበኛ አቅርቦት ወይም ስታንዳርድ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማረጋገጥ፤

6. የግዥ ፍላጎቱ የማህበረሰቡን የአካባቢ ደህንነት እና ጥበቃ የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ፤ አለበት፡፡

3.2 የግዥ ፍላጎት ማሰባሰብ

የመንግስት የልማት ድርጅቱ የግዥ ስራ ክፍል የስራ ክፍሎችን የግዥ ፍላጎታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን መፈፀም አለበት፡-

1. የስራ ክፍሎች የግዥ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፤
2. ከስራ ክፍሎች የቀረበው የግዥ ፍላጎት በግዥ አይነት፤ ብዛት፤ ጥራት፣ ደረጃ እና የሚገኝበት ቦታ መለየት፤
3. ልዩ ትኩረት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እቃዎች የግንባታ ስራና አገልግሎቶች መለየት፤
4. የቀረበው ፍላጎት በቂ አቅራቢ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ማጣራት፤
5. በመንግስት የልማት ድርጅቱ በተደረገ ጥናት ወይም ከሌሎች ምንጮች በተገኘ የገበያ መረጃ ለግዥው የሚያስፈልገውን የዋጋ ግምት ማወቅ፤
6. የፍላጎት መግለጫ በተጠቃሚዎቹ መዘጋጀቱን ወይም በሚመለከተው አካል የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

3.3 የግዥ ፍላጎት ማደራጀት

የመንግስት የልማት ድርጅቱ ከስራ ክፍሎች የተሰባሰበውን ፍላጎት ከገበያ ጥናት የሚገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ እና የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የግዥ ፍላጎቱን ማደራጀት አለበት፡-

1. የሚገዛው ዕቃ፣ አገልግሎት ወይም የግንባታ ስራ ግዥ በአንድ ላይ የሚፈፀምበት ሁኔታ ሲያጋጥም አብላጫ ድርሻ ያለውን የግዥ አይነት መሰረት በማድረግ መፈፀም፣ እስከተቻለ ድረስ ተቀራራቢ እና ተመሳሳይ ፍላጎቶችን በአንድ ላይ ማሰባሰብ፣
2. በአንድ ላይ የሚፈፀሙ ግዥዎች በቂ አቅራቢ በገበያ ላይ መኖሩን ወይም ግዥው በሚኖረው የአቅራቢ አይነት በተለያየ ምድብ /ሎት/ በመከፋፈል በቂ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ማረጋገጥ፤
3. ግዥው ለአፈፃፀም አመቺ እና አደናቃፊ ሁኔታዎች የሌሉበት መሆኑን ማረጋገጥ፤
4. እስከተቻለ ድረስ የአገር ውስጥ አምራቾች የመወዳደር እድልን በሚያሰፋ መልኩ ግዥው እንዲደራጅ ማድረግ፡፡

3.4 የግዥ ዘዴ መምረጥ

1. በግዥ እቅድ ዝግጅት ወቅት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ውስጥ አግባብነት ያለውን በመምረጥ በእቅዱ ላይ ማመልከት አለበት፤
2. የግዥ እቅዱ በሚዘጋጅበት ወቅት ሁሉም የግዥ ፍላጎቶች በእቅዱ ውስጥ መካተታቸውን እና ለእያንዳንዱም ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ መመረጡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3.5 የግዥ መፈፀሚያ ጊዜ መወሰን

የግዥ ስራ ክፍሉ በግዥ ዕቅዱ ሰነድ መሰረት በማዘጋጀት በግዥ ሂደቱ ውስጥ ዋና ዋና ተግባራት የሚከናወኑበትን ጊዜ መወሰን አለበት፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን እና እንደሚፈፀመው የግዥ አይነት ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይገባል፡-

1. ግዥው የሚከናወንበት ጊዜ ከስራ ክፍሎች የስራ ፕሮግራም ጋር የተጣጣመ መሆኑን፤
2. በገበያ ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚኖርበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን፤
3. ዝቅተኛ የጨረታ መቆያ ጊዜን የጠበቀ እና እስከተቻለ ድረስ ሰፊ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጃ ተጨማሪ ጊዜ የሰጠ መሆኑን፤
4. በተለይ ውስብስብ ለሆኑ እና ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ላላቸው ግዥዎች በቂ የሰነድ ማዘጋጃ፣ መገምገሚያ እና ማጽደቂያ ጊዜ የተሰጣቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ግዥው ዋና ዋና ተግባራትን ለማከናወን ከሚያስፈልገው ጊዜ የረዘመ ጊዜ እንዳይወስድ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

3.6 የግዥ እቅድ ይዘት

በመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚዘጋጀው የግዥ ዕቅድ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

1. የግዢው አይነትና ዘዴ፤
2. የግዥውን ምድብ፤
3. የግዥው ዓይነት ወይም መግለጫ፤
4. በመጠን መገለጽ የሚችል ከሆነ የግዥውን መጠን፤

5. የግዥውን ዝርዝር አፈፃፀም የሚከተላቸውን አሰራሮች፤
6. ግዥውን ለማጠናቀቅ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚፈፀሙበትን ጊዜ፤
7. ለግዥው የሚያስፈልገውን ግምታዊ ዋጋ፣ የተያዘው በጀት መጠንና የፋይናንስ ምንጭ፤
8. በግዥ አፈፃፀም ሂደቱ የሚሳተፉ ዋና ዋና አካላትን የተሳትፎ ሁኔታ፤
9. ለግዥው ተስማሚ የሆነ የውል አይነት እና ሌሎች ትኩረትን የሚሹ ጉዳዮችን፤

ያካተተ ይሆናል።

የግዥ ዕቅድ ማቅረቢያ ቅጽ በዚህ ማንዋል አባሪ 1 መሰረት ማቅረብ ይችላል።

3.7 የግዥ እቅድ የሚጸድቅበት እና የሚሻሻልበት ሁኔታ

1. የግዥ ስራ ክፍሉ ያዘጋጀውን የግዥ እቅድ የበጀት ዓመቱ ከመጀመሩ በፊት ለመንግስት ልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በማቅረብ እንዲፀድቅ ያደርጋል፤
2. በመንግስት የልማት ድርጅቱ ተጠሪ የሆኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ፕሮጀክቶች ወይም ተቋማት ለመንግስት ልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በማቅረብ ማጸደቅ አለባቸው፤
3. የጸደቀውን የግዥ ዕቅድ ለአፈፃፀም በስሩ ላለ የግዥ ስራ ክፍል እና ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች መላክ አለበት፤
4. እስከተቻለ ድረስ የግዥ እቅዱ ከፀደቀ በኂላ ግዥ አፈፃፀሙን በጸደቀው ዕቀድ መሰረት መሆን አለበት፤
5. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እቅዱን ያፀደቀው አካል በማንኛውም ጊዜ የግዥ እቅዱን ሊያሻሽለው ይችላል፤
6. የተሻሻለው የግዥ ዕቅድ የመጀመሪያው እቅድ ለተላከላቸው የስራ ክፍሎች መላክ አለበት፡ ፡

3.8 ዓመታዊ የግዥ ዕቅድን ይፋ ማድረግ

የመንግስት የልማት ድርጅቱ በዚህ መመሪያ መሰረት ያዘጋጀውን አመታዊ የግዥ እቅድ እንደአስፈላጊነቱ በየግዥው አይነት በመለየት በመንስት የግዥና ንብረት ባለስልጣን ወይም በመንግስት ድርጅቱ ዌብሳይት እና አመቺ በሆነ መንገድ ለህዝብ በኩል ይፋ ያደርጋል።

3.9 የግዥ ዑደት

የግዥ ዑደት ማለት ከግዥ ፍላጎት መጠየቂያ ጀምሮ ግዥው ለተጠቃሚው እስኪደርስ ደረስ የሚከናወኑ ተግባራት እና በየደረጃው የሚሳተፉ አካላትን ኃላፊነት እና ዝርዝር ተግባር የሚያሳይ የግዥ አፈጻጸም ሂደት ሲሆን የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

3.9.1 የግዥ ፍላጎት መሰብሰብ

1. ፍላጎትን ከተጠቃሚዎች በማሰባሰብ የሚገዙ ዕቃዎችን፤አገልግሎቶችን እና የግንባታ ስራዎችን መለየት፤
2. ፍላጎቶችን ማጠናቀርና ማደራጀት፤
3. የተጠየቁ ፍላጎቶች በግዥ ዕቀድ ውስጥ መኖር አለመኖራቸውን ማረጋገጥ፤
4. ለግዥው በቂ በጀት መኖሩን ማረጋገጥ፤
5. የተጠየቁ ፍላጎቶች በግዥ ዕቅድ ውስጥ መኖሩን ወይም በግዥ ዕቅድ ውስጥ ከሌሉ የግዥ ዘዴዎውን በመምረጥ ለበላይ ኃላፊ ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል በማስፈቀድ፤

3.9.2 የጨረታ ሰነድ ወይም የፍላጎት መግለጫ ሠነድ ማዘጋጀት

1. ከተጠቃሚ ወይም ከቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በመሆን ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት፤
2. በጨረታ ሰነድ ውስጥ የሚካተቱ ክፍሎችን የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠነጠረዥን ጨምሮ፣የግመገማ መስፈርቶችን እንዲሁም የልዩ የውል ሁኔታዎችን በግዥ መመሪያው መሰረት ማዘጋጀት፤
3. እንደአስፈላጊነቱ ግዥው ናሙና ወይም ፍተሻ የሚያስፈልገው ከሆነ በጨረታ ሠነዱ ውስጥ ማካተት፣
4. ጨረታውን ዝቅተኛውን የጨረታ መቆያ ጊዜ በመስጠት ለተጫራቾች ክፍት ማድረግ፤

ያስፈልጋል፡፡

3.9.3 ጨረታን መገምገምና አሸናፊውን መለየት

1. ጨረታውን በጨረታ ሠነዱ ላይ በተለጸው መሰረት መክፈት፤

2. ከተጫራቾች የቀረበውን የመጫረቻ ሠነድ በጨረታ ሠነዱ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መገምገም፤
3. አሸናፊ ተጫራቾችን መለየት እና የጨረታውን ውጤት ለሁሉሉ ተሳታፊ ተጫራቾች ማሳወቅ፤

ያስፈልጋል፡፡

3.9.4 የውል አስተዳደር

1. ውል ከመፈረሙ በፊት በጨረታው ውጤት ቅር የተሰኙ ተጫራቾች አቤቱታ እንዲያቀርቡ የአቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ መስጠት፤
2. በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው የውል ሰነድ መሰረት ውል መፈራረም፤
3. የውል ስምምነቱን የሚከታተል አካል በመሰየም የውል አፈጻጸምን መከታተል፤
4. በውል ስምምነቱ መሰረት መከናወኑን በመከታተል የክፍያ አፈጻጸምን መከታተል፡ ፡

3.10 የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂ

1. የፕሮጀክት ግዥ ስትራቴጂው ቢያንስ ፕሮጀክቱን ለማሳካት የሚያስችል የግዥ ፍላጎት እና ዓይነት፣ የገንዘብ መጠን፣ በግዥው ወቅት ሊያጋጥም የሚችለውን ስጋትና ማቅለያ መንገዶች፣ የገበያ ጥናት፣ አማራጭ የግዥ ዘዴ እና የውል ዓይነት ያካተተ መሆን አለበት፤
2. ፕሮጀክቶች በተለይም የአለም ባንክ ወይም ሌሎች አበዳሪ ወይም ለጋሽ ተቋማት ከሚገኝ ገንዘብ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ግልፅ ዝርዝር የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

4. የኤሌክትሮኒክ የግዥ ስርዓት እና የግዥ ሠነዶች

4.1 የኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸማቸውን ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት እስኪፈጽሙ ድረስ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 14 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. ከአቅራቢዎች ጋር የሚደረጉ የኢሜል እና ሌሎች ተመሳሳይ የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቶች አድርሻው በመንግስት የልማት ድርጅቱ ስም በተከፈተ ኢሜል አድራሻ መላክ ይኖርበታል፤
2. በተመሳሳይ ከአቅራቢዎች የሚላከው ኢሜል በግለሰቦች አድራሻ ሳይሆን በድርጅቱ ስም በተከፈተ ኢሜል አድራሻ መላክ ይኖርበታል፤
3. ከአቅራቢዎች በኢሜል የሚላከው ሰነድ በግል የሚስጥር ቁልፍ ደህንነቱ ተጠብቆ ለመንግስት የልማት ድርጅት የሚላክ ሆኖ የተላከውን የመጫረቻ ሰነድ ለመክፈት የሚያስችለውን የሚስጥር ቁልፍ የጨረታው መዝጊያ ጊዜ ከተጠናቀቀ እና ከጨረታ መክፈቻ በፊት በኢሜል አድራሻ መላክ ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ1-3 መሰረት የማይፈጸም ከሆነ ከተጫራቾች የሚቀርቡ የመጫረቻ ሰነዶች በታሸገ ፖስታ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

4.2 የግዥ ሰነዶች

በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 14 ንዑስ 1 የተገለጹት እና ማንኛውም ከግዥ አፈጻጸም ጋር የሚደረጉ ውሳኔዎች እና ውሳኔ ኃሰቦች በጥንቃቄ በግዥ ወይም በፋይናንስ የስራ ክፍል ተቀምጠው በሚፈለጉበት ወቅት መቅረብ አለባቸው፡፡

5. የተወዳዳሪዎች ማሟላት ያለባቸው የቅድመ ብቃት መስፈርቶች

ተወዳዳሪዎች ማሟላት ስላለባቸው የቅድመ ብቃት መስፈርቶች በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1333/2016 አንቀጽ 24 እንዲሁም ስር የተደነገጉትን የተወዳዳሪዎች ቅድመ ብቃት መስፈርቶች ተከትሎ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

6. ዘላቂነት ያለው የግዥ ሥርዓትን ተፈጻሚ ስለማድረግ

6.1 የህይወት ዘመን ወጪ ትንተና (Life Cycle Cost Analysis)

1. ‹‹የህይወት ዘመን ወጪ ትንተና›› ማለት የግዥውን መነሻ ዋጋ እና ንብረቱ አገልግሎት ላይ በሚውልበት፣ እንዲሁም እንደሁኔታው በሚወገድበት ጊዜ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ወጪ የሚያካትት ትንተና ነው፤ይህ ትንተና አንድ ዕቃ ወይም የግንባታ ሥራ የሚኖረውን የጠቅላላ ወጪ ለመገምገም የሚጠቅም ሲሆን ከመደበኛ የዋጋ ግምገማዎች በተለየ መልኩ የመጫረቻ ዋጋ ብቻ ላይ ያልተመሰረተ እና በተሻለ ሁኔታ ተመጣጣኝ እና ተቋማዊ የሆነ ውሳኔ ለመስጠትን ይረዳል፤
2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የዕቃዎች እና የግንባታ ሥራዎች ግዥን በሚፈጽሙበት ወቅት በአዋጁ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 8 ፊደል ተራ "ለ" የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና መሠረት ግዥ ለመፈፀም በመመሪያው አንቀጽ 20 የተመለከቱትን አሰራር ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፤
3. የሕይወት ዘመን ትንተና ተግባራዊ የሚደረገው ከዚህ በታች የተቀመጠውን ስሌት መሠረት በማድረግ መሆን ያለበት ሲሆን የሚያገለግለውም በባለስልጣኑ ለተለዩ የግንባታ ዘርፍ ወይም የዕቃ ግዥዎች ብቻ ነው፤
4. የሕይወት ዘመን ወጪ = የመጫረቻ ዋጋ + የሕይወት ዘመን ወጪዎች ድምር (ማለትም የስራ ማስኬጃ ወጪ + የጥገና እና የመለዋወጫ ወጪ+ የማስወገጃ ወጪ) - የንብረቱ ቀሪ ዋጋ፤

   ሀ/ “የመጫረቻ ዋጋ” ማለት የዕቃዎች እና የግንባታ ሥራዎች የመጀመሪያ ግዥ ዋጋ ነው፤

   ለ/ “የሕይወት ዘመን ወጪዎች ድምር” ማለት ዕቃው እና የግንባታ ሥራው አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት እስከ ንብረቱ የመጨረሻ ዓመት ያለውን የስራ ማስኬጃ ወጪ፣ የጥገና እና መለዋወጫ ወጪ፣ የማስወገጃ ወጪን ያካትታል፤

   ሐ/ “የሥራ ማስኬጃ ወጪ” ማለት ለዕቃው ወይም ለሥራው የሕይወት ዘመን አስፈላጊ የሆኑ የጥገና፣ የኃይል ፍጆታ እና ሌሎች ንብረቱን ከመጠቀም ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ያካትታል፤

መ/ “የጥገና/መለዋወጫ ወጪ” ማለት በየወቅቱ የሚከሰቱትን ዋና ዋና ወጪዎች ሲሆን እንደ ምትክ ወይም ጥገናን ያካትታል፤

ሠ/ “የማስወገጃ ወጪ” ማለት በንብረቱ የሕይወት ዘመን መጨረሻ ላይ ለማስወገድ የሚወጣ ወጪ ሲሆን የንብረቱ ቀሪ ዋጋ ተቀናሽ መደረግ አለበት፤

ረ/ “ቀሪ ዋጋ” ማለት ንብረቱ የሕይወት ዘመኑ ሲያልቅ ሊሸጥ የሚችለው የተገመተው ዋጋ ነው፡፡

5. የሚቀርበው የሕይወት ዘመን ወጪ ተዓማኒነት ያለው እና በአምራች ወይም በሌሎች በሚመለከታቸው ተቋማት የተረጋገጠ መሆን አለበት፤
6. የሚቀርበው የሥራ ማስኬጃ፣የጥገና፣የመለዋወጫ እና የማስወገጃ ወጪዎች ሲቀርቡ ተገቢውን የወለድ እና የቅናሽ ዋጋ ተመንን በመጠቀም ወጪዎቹ በሚወጡበት ወቅት የሚኖረውን የገንዘብ የመግዛት አቅም ታሳቢ ባደረገ መልኩ መሆን አለበት፤
7. የመንግሥት የልማት ድርጅቱ የሚቀርብለትን የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና የዋጋ ውድድር በሚያከናውንበት ወቅት እንደ ማወዳደሪያ መያዝ አለበት፤
8. የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና በቂ ዕውቀት እና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች መሰራት አለበት፡፡

ለምሳሌ ፡-

አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት የህይወት ወይም የቆይታ ዘመኑ 5 ዓመት የሆነ ዕቃ ወይም ሥራዎች ለመግዛት ቢያስብና በጨረታው ሁለት ተወዳዳሪዎች ለፋይናንሻል ወድድሩ ቢቀርቡ የህይወት ዘመን ወጪ ትንተናው እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ተጫራች "ሀ"					
የሚገዙ ዕቃዎች ወይም ሥራዎች የዋጋ ዝርዝር መግለጫ					
የመጫረቻ ዋጋ (bid price)					9,000,000
የቆይታ ዘመን (Life span (number of years))					5
የጥገና ወጪ (ለ 5 ዓመታት የሚያስፈልግ ጠቅላላ ጥገና)					
ዓ.ም	2019	2020	2021	2022	2023
የጥገና ብዛት በዓመት	1	2	2	3	3
የአንድ ጊዜ የጥገናና የመለዋወጫ ወጪ በብር	35,000	45,000	55,000	65,000	85,000
የጥገናና የመለዋወጫ ወጪ በአመት	35,000	90,000	110,000	195,000	255,000
አጠቃላይ የጥገናና የመለዋወጫ ወጪ (Total Cost of Maintenance required for 5 years)					685,000
የነዳጅ ወጪ	120,000	130,000	150,000	160,000	180,000
አጠቃላይ የነዳጅ ወጪ					740,000
ሌሎች ሥራ ማስኬጃ ወጪዎች (Operating Costs)	120,000	130,000	130,000	150,000	150,000
አጠቃላይ ሌሎች የሥራ ማስኬጃ ወጪ					680,000
የማስወገጃ ወጪ (demolition/disposal costs)	-	-	-	-	45,000
አጠቃላይ የማስወገጃ ወጪ					45,000
የህይወት ዘመን ወጪዎች ድምር					2,150,000
ከ5 ዓመት በኋላ የንብረቱ ቀሪ ዋጋ፣ (የንብረቱ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ)					640,000

የህይወት ዘመን ወጪ =የመጫረቻ ዋጋ + የሕይወት ዘመን ወጪዎች ድምር - የንብረቱ ቀሪ ዋጋ	9,000,000 + 2,150,000 - 640,000 = <u>10,510,000</u>

ተጫራች “ለ”

የሚገዙ ዕቃዎች ወይም ሥራዎች የዋጋ ዝርዝር መግለጫ					
የመጫረቻ ዋጋ (bid price)					9,500,000
የቆይታ ዘመን (Life span (number of years))					5
ለ5 ዓመታት የሚያስፈልግ ጠቅላላ የጥገና ወጪ					
ዓ.ም	2019	2020	2021	2022	2023
የጥገና ብዛት በዓመት	1	1	1	2	2
የአንድ ጊዜ የጥገናና የመለዋወጫ ወጪ በብር	30,000	30,000	40,000	50,000	60,000
የጥገናና የመለዋወጫ ወጪ በአመት	30,000	60,000	40,000	100,000	120,000
አጠቃላይ የጥገናና የመለዋወጫ ወጪ (Total Cost of Maintenance required for 5 years)					350,000
የነዳጅ ወጪ	70,000	70,000	80,000	100,000	100,000
አጠቃላይ የነዳጅ ወጪ					420,000
ሌሎች የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች (Operating Costs)	50,000	60,000	60,000	70,000	80,000
አጠቃላይ ሌሎች የሥራ ማስኬጃ ወጪ					320,000

የማስወገጃ ወጪ (demolition/disposal costs)	-	-	-	-	20,000
አጠቃላይ የማስወገጃ ወጪ					20,000
የህይወት ዘመን ወጪዎች ድምር					1,110,000
ከ5 ዓመት በኂላ የንብረቱ ቀሪ ዋጋ፣ (የንብረቱ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ)					840,000
የህይወት ዘመን ወጪ =የመጫረቻ ዋጋ + የሕይወት ዘመን ወጪዎች ድምር - የንብረቱ ቀሪ ዋጋ					9,500,000 + 1,110,000 - 840,000 = **9,770,000**

9. ከላይ በሰንጠረዡ በተመለከተው የህይወት ዘመን ወጪ መሰረት የተጫራች "ሀ" የሕይወት ዘመን ወጪ ዋጋ 10,510,000 ሲሆን የተጫራች "ለ" የሕይወት ዘመን ወጪ ዋጋ ደግሞ 9,770,000 ብር ነው፡፡ በዚህም መሰረት ተጫራች "ለ" ን አሸናፊ አድርጎ ይመርጣል፡፡ ነገር ግን የውል ዋጋ ለጨረታው ባቀረበው የመጫረቻ ዋጋ (ብር 9,500,000) ነው፡፡

6.2 የአካባቢ ጥበቃ ታሳቢ ያደረገ የመንግስት ግዥ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚፈጽሟቸው ግዥዎች በአዋጁ አንቀጽ 28 መሰረት ከአካባቢ ብክለት የጸዳ፣መልሶ መጠቀምን እና የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ከግምት ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡-

- ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቴክሎጂዎችን፣ የታዳሽ ኃይል ምንጮችን በመጠቀም ወይም ዝቅተኛ ልቀቶችን በመጠቀም የተመረቱ ምርቶችን ሊያበረታቱ የሚችሉ መስፈርቶችን በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነዶች ውስጥ ማካተት አለባቸው፡፡
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች እንደገና ጥቅም ላይ በዋሉ ቁሶች የተዘጋጁ ወረቀቶችን፣ ፕላስቲክ፣ ጎማ ወይም የግንባታ ዕቃዎችን ቅድሚያ በመስጠት ግዥ ሊፈጽሙ የሚችሉበትን አሰራር መከተል አለባቸው፡፡

- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ግዥ ከመፈጸማቸው በፊት እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበት አማራጭ አለመኖሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ከላይ በቀረቡት ድንጋጌዎች መሠረት የሚፈጸሙ የዕቃ አይነቶችን ይወስናል፣ ዝርዝሩን ለመንግሥት መ/ቤቶች በጽሁፍ ያሳውቃል እንዲሁም በጥናት ላይ ተመስርቶ ከሌሎች ከሚመለከታቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን የመንግሥት ግዥ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ስታንዳርድ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተያያዙ ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት፣

- በነዳጅ የሚሰራ መኪና ከመግዛት ይልቅ የአካባቢ ብክለትን የማያስከትሉ በኤሌክትሪክ ሀይል እና በተፈጥሮ ጋዝ የሚንቀሳቀሱ መኪናዎችን መግዛት፤
- ከፕላስቲክ የተዘጋጁ ምርቶች ይልቅ መልሶ ጥቅም ላይ ሊውሉና በቀላሉ ሊበሰብሱ የሚችሉ ምርቶችን መጠቀም፣
- ኃይል ቆጣቢ የሆኑ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን፣የአየር ማቀዝቀዣዎች፣ ትራንስፎርመሮች፣ አምፖሎች…ወዘተ መጠቀም፤
- ከተፈጥሮ ጋር ተስማሚ የሆነ የግንባታ ግብዓቶችንና ዲዛይን ያሟላ አረንጓዴ ሕንጻን ጨምሮ ዘላቂነት ያለው፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለአቅም ደካሞች ምቹ እና የደህንነት ሁኔታን የሚሉ ግንባታዎችን መጠቀም፤
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች የአካባቢ ብክለት የማያስከትሉ ወይም ዝቅተኛ የአካባቢ ብክለት ያላቸውን ምርቶችና አገልግሎቶችን ቅድሚያ በመስጠት መግዛት ይኖርባቸዋል፡፡

6.3 የማህበረሰብን ተጠቃሚነት ታሳቢ ያደረገ ግዥ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚፈጽሟቸው ግዥዎች በአዋጁ አንቀጽ 28 መሠረት የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከዚህ ቀጥሎ የተደነገጉትን ከግምት ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡-

- ☞ በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚፈጸሙ ግዥዎች ለአካባቢው ማህበረሰብ ያላቸውን አዎንታዊ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ተጽዕኖዎችን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፤

☞ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያበረታታ፣ የአካባቢ ማህበረሰቦችን በመደገፍ ግዥው ማህበራዊ ጥቅሞችን ማስገኘት ይኖርበታል።

☞ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ግዥ በሚፈጽሙበት ወቅት ተወዳዳሪዎች ማንኛውም አካባቢያዊ ወይም ማህበራያዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ወይም አካላዊ ወይም ስነ-ምግባራዊ ወይም ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ወይም የጤና ወይም የደህንነት መስፈርቶች ወይም ጥበቃ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ያልታገዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፤

☞ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ግዥ በሚፈጸምበት ጊዜ የፍላጎት መግለጫ ዝግጅት ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የሚገኙ መረጃዎችን በመጠቀም ማዘጋጀት እንዲሁም ፈቃድ የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች ላይ ተወዳዳሪዎች ተገቢውን ፍቃድ የያዙ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል፤

☞ በተጫራቾች የሚቀርቡት የፋብሪካ ውጤት የሆኑ የምግብ ግብዓቶች፣ የምግብ ጨው፣ የስንዴ ዱቄት እና የምግብ ዘይት በሚሆንበት ጊዜ አስፈላጊውን ንጥረ ነገር የያዙና የበለጸጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በጨረታ መገምገሚያ መስፈር ክፍል 3 ላይ የተገለጹትን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እና የምርት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲያቀርቡ መጠየቅ አለበት።

7. የግዥ ዘዴዎች እና አፈጻጸማቸው

1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በተቻለ መጠን ማንኛውንም ግዥ በግልጽ ጨረታ መፈጸም የሚጠበቅባቸው ሲሆን በተለያየ ምክንያት ከግልጽ ጨረታ ውጪ ግዥ ለመፈጸም በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ላይ ለየግዥ ዘዴዎች የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ሲያሟሉ ነው።
2. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 28 መሰረት ማናቸውም የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚከተሉት የግዥ ዘዴዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፣

   2.1 በብሔራዊ እና ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ፣

   2.2 በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ የሚፈጸም ግዥ፣

- በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ፣
- በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ የሚፈጸም ጨረታ፣
- በፍላጎት መጠየቂያ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ፣

2.3 ውስን ጨረታ፣እና

- በተገደበ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ፣
- በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ፣

2.4 በቀጥታ የሚፈጸም ግዥ ናቸው፡፡

3. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ ዘዴ የሚመርጡት በግዥ ዕቅድ በሚያዘጋጅበት ወቅት ሲሆን ትክክለኛውን የግዥ ዘዴ መምረጥ ለሚፈጸመው ግዥ በግዥ ህጉ መሰረት አግባብነት ያለውን የግዥ ዘዴ መመረጡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤
4. የግዥ ዘዴ በሚመረጥበት ወቅት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፤

- የግዥው ዓይነት፣
- የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን፣
- የአቅራቢዎች ውስንነት፣
- የግዥው ውስብስበነት.
- የግዥው አስቸኳይነት፣
- ሌሎች በግዥ ፈጻሚው የሚቀርቡ ቅድመ ሁኔታዎች፣

5. በዕቅድ ውስጥ የተካተቱ የግዥ ዘዴዎች በዕቅዱ በተገለጸው የግዥ ዘዴ መሰረት ለመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል ማቅረብ ሳያስፈልግ የግዥ ሂደታቸው ይጀምራል፤
6. በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ግዥዎች የግዥ ሂደታቸው ከመጀመሩ በፊት የግዥ ዕቅድ ማሻሻያ ይደረጋል ወይም የግዥ ዘዴው በግዥ የስራ ክፍል ወይም በሚመለከተው የስራ ክፍል ተዘጋጅቶ ለመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል በማቅረብ እንዲጸድቅ ይደረጋል፤

7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሁኖ የግዥ ዘዴውን ለማስፈቀድ የሚቀርበው ማብራሪያ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ለየግዥ ዘዴው የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላቱን በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

7.1 በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ግዥ የሚፈጽሙት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 29 ከንዑስ አንቀጽ 1-5 ከተገለጹት ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ሲሟላ ነው፡፡

7.2 በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ

1. የመንግስት የልማት ድርጅተች በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ የሚፈጽሙት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተገለጹት ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ሲሟላ ነው፡፤
2. በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ በሚፈጸም ግዥ ላይ ተሳታፊ አካላት(Stakeholders) ግዥ ፈጻሚው የመንግስት የልማት ድርጅት፣አቅራቢዎች፣ብሔራዊ ባንክ፣የውስጥ እና የውጭ አገር ባንኮች፣ኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ጉምሩክ ኮሚሽን፣የጭነት መርከብ ድርጅቶች፣ የትራንዚት ድርጅቶችና ሰራተኞች ሲሆን በግዥው አፈጻጸም ወቅት የየራሳቸው ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፤
3. በሁሉም ዕቃዎችና አቅርቦቶች ግዥ ሰነዶች በዓለም አቀፍ የንግድ ምክር ቤት በየጊዜው የሚወጡ የጭነት ማጓጓዣ፣ የወጪና የዋስትና አሸፋፈን የውል ዓይነቶችን ኢንኮተርምስ (INCOTERMS) መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ይህም በተዋዋይ ወገኖች (በገዥ እና አቅራቢ) መካከል በትርጉሞች ላይ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለማስቀረት ያግዛል፤
4. በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ሰነድ (L/C) በብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ካገኘ ባንክ ወይም የገንዘብ ተቋም የሚሰጥ ሲሆን ሰነዱ የተሰጠው ሰው ወይም የባንኩ ደንበኛ በሰነዱ ላይ የተገለጸውን የገንዘብ መጠን ከባንኩ የማውጣት ሰልጣን ይሰጠዋል፡፡ በዚህ መንገድ ክፍያ የሚፈጸመው የባንኩ ደንበኛ የሆነው ሰው ዕቃ ወይም አቅርቦት በሚገዛበት ወቅት ሻጩ ለሸጠው ዕቃ ክፍያ እንደሚፈጸምለት ለማረጋገጥ ነው፤

5. በባንክ የተረጋገጠ ክፍያ ሰነድ (L/C) የሚፈጸምበት ሁኔታ በአቅራቢው እና በመንግስት የልማት ድርጅቱ በሚደረገው የውል ስምምነት ሰነድ ላይ በተቀመጡት ሁኔታዎች ላይ የሚመሰረት ነው፤
6. በባንክ የተረጋገጠ ክፍያ ሰነድ (L/C) በሚፈጸም ግዥ ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት፡

- አቅራቢው ወይም ሻጭ እና ግዥ ፈጻሚው የንግድ ልውውጥ ለማድረግ ሲስማሙ፤ ክፍያን ለማረጋገጥ ሻጭ የባንክ ማረጋገጫ ይፈልጋል፤
- ገዥ በሻጭ ስም የባንክ ክፍያ ማረጋገጫ (L/C) ሰነድ እንዲዘጋጅላቸው ለደንበኛው ባንክ ያመለክታል፤
- ባንኩ የገዥውን የመንግስት የልማት ድርጅት ኃላፊነት በመውሰድ ሰነዱን አዘጋጅቶ ውጭ አገር ለሚገኘው አቻ ባንክ ለምክር ወይም ለማረጋገጥ የሚያስተላልፍ ሲሆን አቻው ባንክ ብዙ ጊዜ የሚገኘው ሻጭ በሚኖርበት አካባቢ ነው፤
- ሰነዱ የተላከለት አቻ ባንክ የሰነዱን እውነተኛነት በማረጋገጥ ዋናውን ሰነድ ለሻጭ ያስተላልፋል፤
- ሻጭ ዕቃዎችን ያጓጉዛል ወይም ይጭናል፣በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ አፈጻጸም ሂደቱን የሚያግዙ አስፈላጊ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤
- አስፈላጊ ሰነዶች ከሻጭ ጋር ስምምነት በሚደረግባት ጊዜ ከተለያዩ ስጋቶች አንጻር እንደግዥው ዓይነት ሊለያይ ይችላል፤
- ሻጭ ክፍያ ለመፈጸም የሚያስፈልገውን ሰነድ ለከፋዩ ባንክ ያቀርባል፤
- ክፍያ የሚፈጸመው ወይም የሚረጋገጠው ባንክ በሻጩ የቀረቡት ሠነዶች በባንክ ክፍያ ማረጋገጫ ሰነድ(L/C) ላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች ጋር የሚጣጣም መሆኑን ያረጋግጣል፤
- ሰነዶቹ ትክክል ከሆኑ የሚከፍለው ወይም የሚያረጋግጠው ባንክ ገንዘቡን ይጠይቃል፤
- የባንክ ክፍያ ማረጋገጫ (L/C) ሰነዱን ከሰጠው ባንክ ተቀማጭ ገንዘብ ይቀንሳል፤
- የባንክ ክፍያ ማረጋገጫ (L/C) ሰነዱን የሰጠው ባንክ ሰነዶችን ከተረከበ በኋላ ገንዘቡን እስከሚልክይጠብቃል፤

- የባንክ ክፍያ ማረጋገጫ (L/C) ሰነዱ ላይ በተገለጸው ሁኔታ ሌላ ባንክ የከፈለውን ክፍያ ይተካል፤
- ክፍያ የሚፈጸመው ወይም ስለክፍያ የሚረጋገጠው ባንክ ከሻጭ የተረከባቸውን ሰነዶች የባንክ ክፍያ ማረጋገጫውን (L/C) ለሰጠው ባንክ ይልካል፤
- የባንክ ክፍያ ማረጋገጫው (L/C) የሰጠው ባንክ የተላኩትን ሰነዶች በስምምነቱ መሰረት የተሟሉ ወይም ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ይመረምራል፣ ትክክል ከሆኑ ባንኩ ከገዥው የባንክ ሲሳብ ላይ የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን ይቀንሳል፤
- ከዚህ በኋላ የባንክ ክፍያ ማረጋገጫውም (L/C) የሰጠው ባንክ ከሻጭ ባንክ የተላኩትን የማጓጓዣ ሰነዶች ለገዥው ያስተላልፋል፡፡

7. በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ተጫራቾች በሚወዳደሩበት ወቅት ለግምገማ ዓላማ ዕቃው ከሚያርፍበት ወደብ አንስቶ እስከ ግዥ ፈጻሚው የመንግስት የልማት ድርጅት ለማድረስ የሚከፈል ታክስና ቀረጥ፣ኢንሹራንስ እና የማጓጓዣ ወጭዎችን እና ሌሎች ተያያዥ ክፍያዎች እና ወጪዎችን ታማኒነት ካላቸው የመረጃ ምንጮች በመወሰድ የውጭ አገር ተጫራቾች ከሚያቀርቡት የFOB ዋጋ ላይ በመደመር የአገር ውስጥ አቅራቢዎች በሚያቀርቡት በDDP ዋጋ መሰረት ግምገማው ይከናወናል፡፡

7.3 ሌሎች ዓለም አቀፍ ግዥዎች

በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 31 መሰረት ለዓለም አቀፍ ግዥው እና ለየግዥ ዘዴው የተደነገገው ቅድመ ሁኔታ ሲሟላ ዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተገለጹት ሌሎች አሰራሮች እንደተጠበቁ ሆነው በተገደበ ጨረታ፣በዋጋ ማቅረቢያ እና በቀጥታ የሚፈጸም የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም ዓለም አቀፍ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

7.4 በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ

1. በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ የግዥ ዘዴ በጨረታ መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾችን ከአንድ ደረጃ በላይ በሆነ ውድድር በማጣራት እና በመጀመሪያው ደረጃ የተመረጡ ተጫራቾችን ለቀጣይ ዙር ውድድር በመጋበዝ ከተጫራቾች መካከል የጨረታው አሸናፊ

የሚመረጥበት የግዥ ዘዴ ሲሆን፣ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ፣ የፍላጎት መጠየቂያ ጨረታ እና የሁለት ደረጃ ጨረታን ያካትታል፡፡

2. በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ ሥራ ላይ □ሚዉለዉ ግዥው ትልቅ ወይም ውስብስብ በሆኑ የዕቃ□ችና ተዛማጅ አገልግሎቶች ወይም የግንባታ □ርአ ሥራ□ችና አገልግሎቶች ግዥ ለምሳሌ ምርት ለማምረት የሚያስፈልጉ ፐላንቶችን የሚመለከቱ የተዘጋጁ ውሎች በተጨማሪም □ዲዛይን/የንድፍ የግንባታ፣ መሳሪጸ□ች መገጣጠሚያ የአዲስ ፍብሪካ□ች፣ የከፍተኛ የኮምፒውተርና የመገናኛ ሲስተም የመዘርጋት ሥራ □እና የመሳሰሉት ተግባራት ለመጀመር በማጣሪያ የሚከናወን የግዥ አፈፀፃምን መጠቀም ይቻላል፡፡

3. በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ □ግዥ ዘዴ ለመጠቀም የሚገዙ ነገሮች በባህሪያቸው ውስብስብ በመሆናቸው ቴክኖሎጅው በፍጥነት ስለሚለዋወጥ የተሟላ የቴክኒክ ዝርዝሮችን በቅድሚያ ማዘጋጀት የመንግስት የልማት ድርጅቱን የተሻሉ ፍላጎቶችን የሚያንጸባርቅ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ የመንግስት የልማት ድርጅቱ የማያውቃቸው ሌሎች የቴክኒክ አማራጮች ሊኖሩ ስለሚችሉ የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ሙሉ የቴክኒክ ዝርዝሮችን ማዘጋጀት በማይችልበት ወቅትም ይህ ዘዴ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

7.4.1 የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ግዥ ሲፈጽሙ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ክፍል 4 አንቀጽ 32 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. የቅድመ ብቃት መገምገሚያ መስፈርት በማዘጋጀት በብሔራዊ ወይም በዓለም ግልጽ ጨረታ በማውጣት ጨረታው አቅም ያላቸውን ተጫራቾች በመለየት እነዚህን ተጫራቾች በድጋሜ ዋጋ እና እንደአስፈላጊነቱ የቴክኒክ የመወዳደሪያ ኃሳብ እንዲያቀርቡ በማደረግ የሚወዳደሩበት የግዥ ዘዴ ነው፡፡
2. በስትራቴጂክ አጋርነት ከሚፈጸመው ግዥ የሚለየው ይህ ሊፈጸም ለታሰበው ግዥ ለአንድ ጊዜ የሚፈጸም ሲሆን በስትራቴጂክ አጋርነት ለረጅም ጊዜ (ለሁለት ዓመት) ለሚፈጸም ግዥ አቅራቢዎችን ለመምረጥ የሚከናወን የግዥ ስልት ነው፡፡

7.4.2 የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የፍላጎት መግለጫ ጨረታ ወይም የምክር አገልግሎት ግዥ ሲፈጽሙ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ክፍል 4 አንቀጽ 34 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 9 መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቶች አማካሪዎችን የሚመረጡት፡-
   - በሚከናወን የሥራ ጥራት ላይ፣
   - በጥራትና በዋጋ ላይ፣
   - በዝቅተኛ ዋጋ ላይ፣
   - በቁርጥ በጀት ላይ፣
   - በአማካሪዎች ብቃት ላይ፣

   የተመሠረተ መረጣ ማከናወን የሚችሉ የተለመደው የመምረጫ ዘዴ በጥራትና በዋጋ ላይ የመምረጫ ዘዴ ነው፡፡

2. በጥራት እና ዋጋ ላይ በተመሰረተ መረጣ በመጠቀም አማካሪዎች ሲመረጡ በቴክኒክ ብቃት ምዘና ከመቶ ከተያዘው ውጤት 70% (ሰባ ከመቶ) በታች ያገኙ ተወዳዳሪዎች ውድቅ ተደርገው 70% እና ከዚያ በላይ የሚያገኙት አማካሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ሰነዳቸው የሚከፈት ሲሆን የቴክኒክ ውጤት ወደ 80% ተቀይሮ የዋጋ ግምገማ የነጥብ ድርሻ ደግሞ ወደ 20% በመቀየር በቴክኒክና በዋጋ ድምር ውጤት ከፍተኛ ያመጣው አማካሪ አሸናፊ ይሆናል፡፡
3. ለምሳሌ አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት የምክር አገልግሎት ግዥ ለመፈጸም ባወጣው ጨረታ ላይ ከተሳፉ 4 አማካሪዎች ውስጥ አንድ አማካሪ የቴክኒክ ውጤቱ ከመቶ 70% በታች ያመጣ ስለሆነ የፋይናንስ ሰነዱ ያልተከፈተ ሲሆን ከመቶ ከተያዘው ውጤት 70% እና ከዚያ በላይ ያመጡ 3 አማካሪዎች የቴክኒክ ውጤት እና ዋጋ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡- አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት የምክር አገልግሎት ግዥ ለመፈጸም ባወጣው ጨረታ ላይ ከተሳፉ 4 አማካሪዎች ውስጥ አንድ አማካሪ የቴክኒክ ውጤቱ ከመቶ 70% በታች

ያመጣ በመሆኑ የፋይናንስ ሰነዱ ያልተከፈተ ሲሆን ከመቶ 70% እና ከዚያ በላይ በቴክኒክ ግምገማ ያመጡ 3 አማካሪዎች የቴክኒክ ውጤት እና ዋጋ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

መስፈርት	በመመሪያው ላይ የተቀመጠው	በጨረታ ሰነዱ ላይ የተወሰነው የነጥብ ድርሻ	የተወዳደሩት አማካሪዎች ያገኙት የቴክኒክ ውጤት			
			አማካሪ 1	አማካሪ2	አማካሪ3	አማካሪ4
የአማካሪው የስራ ልምድ	ከ5-10	10	5	7	8	6
የአሰራር ዘዴ	ከ20-50	30	25	30	30	25
የሰው ኃይል	ከ30-60	50	40	45	30	30
የእውቀት ሽግግር	ከ5-10	10	8	8	7	6
ድምር ከ100		100	78	90	75	67

አሸናፊውን አማካሪ ለመምረጥ

- በቴክኒክ 70% እና ከዚያ በላይ ያገኙትን ተወዳዳሪዎች ከ100% ያመጡትን የቴክኒክ ውጤት ወደ 80% ለመቀየር ከ100% ያመጡትን በ0.80 በማባዛት የሚገኝ ሲሆን፤ ለምሳሌ አማካሪ 1 በቴክኒክ ያመጣው ከ100% 78 ሲሆን 78ን በ0.8 ሲባዛ 62.40 ከ 80 ያገኛል፡፡
- በቴክኒክ 70% እና ከዚያ በላይ ያመጡትን አማካሪዎች ያቀረቡት ዋጋ ወደ 20% ለመቀየር ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው አማካሪ ከፍተኛውን ወይም 20% የሚያመጣ ሲሆን ሌሎች አማካሪዎች ከ20% የሚሰላው ዝቅተኛ ዋጋው በግምገማ ላይ ላለው አማካሪ ዋጋ በማካፈል የሚገኘውን ውጤት በ20 በማባዛት ይሆናል፡፡

የአማካሪው የፋይናንስ ውጤት ከ20 = ዝቅተኛ ዋጋ x በ20
በግምገማ ላይ ያለ ዋጋ

- በዚህም መሰረት የአማካሪ 2 ፋናይንስ ውጤት ከ20% = (100,000,000/120,000,000)X20=16.67 ይሆናል፡፡

በዚህም መሰረት፡-

አማካሪዎች ያቀረቡት ዋጋ (በሚሊዮን ብር)፣ የፋይናንስ ውጤት ከ20% የቴክኒክ ውጤት ከ80% እና የፋይናንስ እና የቴክኒክ ውጤት ከ100% እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

አማካሪዎች	ያቀረቡት ዋጋ በሚሊዮን ብር	የፋይናንስ ውጤት ከ20%	የቴክኒክ ውጤት ከ80%	የፋይናንስ እና የቴክኒክ ውጤት ከ100%
• አማካሪ 1	100	20	62.40	82.40
አማካሪ 2	120	16.67	72	88.67
አማካሪ 3	150	13	60	73

እንደ ምክር አገልግሎቱ የመምረጫ ዘዴ አሸናፊ የሚሆነው አማካሪ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- በጥራትና በዋጋ ላይ ጥራት የተመሰረተ መረጣ ከሆነ በቴክኒክ እና በዋጋ ድምር 88.67%ከ100% ያመጣው አማካሪ 2 አሸናፊ ይሆናል፡
- በሚከናወን የሥራ ጥራት ላይ የተመሰረተ መረጣ ከሆነ በጥራት አንደኛ የሆነው በቴክኒክ 90%ከ100% ያመጣው አማካሪ 2 አሸናፊ ይሆናል፡፡
- በቁርጥ በጀት ላይ የተመሰረተ መረጣ ከሆነ እና በጀቱ ብር 130 ሚሊዮን ቢሆን በቴክኒክ እና በዋጋ ድምር 88.67% ከ100% ያመጣው አማካሪ 2 አሸናፊ ይሆናል፡ ፡
- በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሰረተ መረጣ ከሆነ በቴክኒክ ካለፉት መካከል ዝቅተኛ ዋጋ (ብር 100 ሚሊዮን) ያቀረበው አማካሪ 1 አሸናፊ ይሆናል፡

7.4.3 በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ

በሁለት ደረጃ የሚፈፀም ግዥ እንደግዥው ዓይነት ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ ይፈጸማል፡፡ ዝርዝር የጨረታ አፈጻጸሙን በሚመለከት በግዥ መመሪያው አንቀፅ 33 ስር የተመለከቱትን መሰረታዊ ጉዳዮች መሠረት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

7.5 የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ አፈጻጸም

1. የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት ሳያስፈልግ ቁጥራቸው ውስን ለሆኑ ተሳታፊዎች በደብዳቤ ወይም የኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን በመጠቀም በአድራሻቸው በሚላክ ግብዣ መሠረት የሚቀርቡ ተጫራቾችን በማወዳደር የጨረታ አሸናፊ የሚመረጥበት የግዥ ዘዴ ነው፡፡
2. የውስን ጨረታ ግዥ ዘዴ የሚፈፀመው በአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በተገደበ ጨረታ ወይም በዋጋ ማቅረቢያ መሆን አለበት፡፡

7.5.1 በተገደበ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች በተገደበ ጨረታ ግዥ የሚፈጽሙት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 40 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. በተገደበ ጨረታ ለማወዳደር የሚጋበዙት ድርጅቶች በተቻለ መጠን በተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ደረጃ ያላቸውን ድርጅቶች ወይም አቅርቦቶችን ነው፤
2. የሚጋበዙት ደብዳቤ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አባሪ 3 ለተገደበ ጨረታ የተቀመጠውን የጨረታ መቆያ ጊዜ ሆኖ ሁሉም የተጋበዙ ድርጅቶች የጨረታ መቆያ ጊዜው ሳይደርስ የመወዳደሪያ ኃሳባቸውን ከአቀረቡ ለተወዳዳሪዎች በማሳየት ጨረታውን መክፈት ይችላሉ፤
3. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 40 ለተገደበ ጨረታ ለመፈጸም በተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ መሰረት በዚሁ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3(ሠ) መሰረት በአገር ውሰጥ የተገደበ ጨረታ እንዲሁም አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3(ረ) መሰረት በዓለም አቀፍ የተገደበ

ጨረታ በተቀመጠው የገንዘብ ገደብ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚፈጸሙ ማንኛውንም ግዥዎችን መፈጸም ይችላሉ፤

4. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 40 ለተገደበ ጨረታ ለመፈጸም በተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ መሰረት በዚሁ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 12 መሰረት በተቀመጠው የገንዘብ ጣሪያ ግዥ መፈጸም የሚቻለው በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 48 መሰረት ለመንግስት የልማት ድርጅቱ የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት እና አስተማማኝ የሆነ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ ለሚያስፈልጉ ግዥዎች እና በስትራቴጂክ አጋርነት የግዥ ስልት በቅድመ ብቃት ተወዳድረው በአቅራቢነት የተመዘገቡ ድርጅቶች መካከል የተሻለ ብቃት ያላቸውን ድርጅቶች በመጋበዝ ነው፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 4 የተገለጸው ቢኖርም በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በስትራቴጂክ አጋርነት ያልተመዘገቡ ተጨማሪ አቅራቢዎች በተገደበ ጨረታ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

7.5.2 በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ የሚፈጽሙት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 41 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. በዋጋ ማቅረቢያ ለማወዳደር የሚጋበዙት ድርጅቶች በተቻለ መጠን በተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ደረጃ ያላቸውን ድርጅቶች ወይም አቅርቦቶችን ነው፤
2. በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ዋጋ ለመሰብሰብ የሚጋበዙት ድርጅቶች ግዥ አፈጻጸም መመሪያው አባሪ 3 ላይ ለዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተቀመጠውን 2 ቀን አነስተኛ የመቆያ ጊዜ ገደብ ሆኖ ሁሉም የተጋበዙ ድርጅቶች ከመቆያ ጊዜው ሳይደርስ የመወዳደሪያ ኃሳባቸውን ከአቀረቡ የዋጋ ማቅረቢያውን መክፈት ይችላሉ፤
3. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 41 መሰረት በዋጋ ማቅረቢ የግዥ ዘዴ ለመፈጸም በተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ መሰረት በዚሁ የአፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በአገር ውስጥ የዋጋ ማቅረቢያ እንዲሁም አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በዓለም አቀፍ የዋጋ ማቅረቢያ በተቀመጠው የገንዘብ ገደብ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚፈጸሙ ማንኛውን ግዥዎችን መፈጸም ይችላሉ፤

4. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 41 በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ለመፈጸም በተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ መሰረት በዚሁ የአፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በተቀመጠው የገንዘብ ጣሪያ ግዥ መፈጸም የሚቻለው በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 48 መሰረት ለመንግስት የልማት ድርጅቱ የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት እና አስተማማኝ የሆነ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ ለሚያስፈልጉ ግዥዎች እና በስትራቴጂክ አጋርነት የግዥ ስልት በቅድመ ብቃት ተወዳድረው በአቅራቢነት የተመዘገቡ ድርጅቶች መካከል የተሻለ ብቃት ያላቸውን ድርጅቶች በማወዳደር ነው፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 4 የተገለጸው ቢኖርም በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በስትራቴጂክ አጋርነት ያልተመዘገቡ ተጨማሪ አቅራቢዎች በማሳተፍ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

7.6 ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከአንድ አቅራቢ የግዥ ዘዴ ግዥ የሚፈጽሙት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 42 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በዓይነት እና በዋጋ አንድ ዓይነት የሆኑ ዕቃዎችን፣የምክር እና ከምክር ውጪ የሆኑ አገልግሎቶችን ቀደም ሲል እነዚህን አቅርቦቶች በግልጽ ወይም በተገደበ ጨረታ ተወዳድሮ ከአሸነፈ ድርጅት ሲሆን በዋጋ ማቅረቢያ እና ከአንድ አቅራቢ በተፈጸመ ግዥ በዚህ አንቀጽ ተጨማሪ ግዥ መፈጸም አይቻልም፤
2. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ያልታሰቡና በመጀመሪያው ውል ውስጥ ሊካተቱ ያልቻሉ ተጨማሪ እና ተመሳሳይ (Suplementary & Variation) የግንባታ ሥራዎችን ማሰራት የሚቻለው እስከ 40% ሲሆን ተጨማሪ ስራው ከ40% በላይ ከሆነና በተጨማሪነት ለመስራት የመንግሰት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በልዩ ሁኔታ ማስፈቀድ ሰፈልጋል፤
3. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት በዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ እና አነስተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸውን ወይም ዋጋቸው ከብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) ያልበለጡ ጥቃቅን ግዥዎች ለአንድ በጀት ዓመት ውስጥ ብር 5,000,000.00 (አምስት ሚሊዮን ብር) የተፈቀደው ለመንግስት የልማት ድርጅቱ እና በስሩ ላሉ ተጠሪ ተቋማትን

ጨምሮ ሲሆን፤የተጠሪ ተቋማትን የድርሻ መጠን በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚወሰን ይሆናል፡፡

4. በቁርጥ ዋጋ ግዥ ለመፈጸም በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፦
    4.1 በቁርጥ ዋጋ ለሚፈጸሙ ግዥዎች ዋጋ ለመወሰን ዝርዝር ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት በየወቅቱ በማከናወን ለመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቦ መፅደቅ ይኖርበታል፤
    4.2 በተቻለ መጠን በዚህ የግዥ ዘዴ የሚፈጸመው ግዥ ውስብስብነት የሌለው፣ ዋጋው በቀላሉ ሊገኝ የሚችል እና በትክክል ሊገለጽ የሚችል መሆን አለበት፤
    4.3 በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 43 የልዩ የቀጥታ ግዥ አፈጻጸም ላይ የተቀሱት አቅርቦቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4.1 በተወሰነው ዋጋ መሰረት ግዥው ይፈጸማል፤
    4.4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4.3 ከተደነገገው ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የቀርጥ ዋጋን ለመጠቀም በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 44-46 በተገለጸው መሰረት በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ከሚፈቀዱ ጉዳዮች አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡
5. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው መሰረት ለሚፈጸሙ ጥቃቅን ግዥዎች ካልሆነ በስተቀር የመንግስት የልማት ድርጅቱ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጸም ግዥ የሚፈጸመውን የግዥ ዓይነትና መጠን እንዲሁም የፍላጎት መግለጫ የሚያዘጋጅ ሲሆን በተዘጋጀው የፍላጎት መግለጫ መሰረት ከድርጅቱ የሚቀርብ የመወዳደሪያ ኃሳብ የአንድ አቅራቢ ሰርዓትን ተከትሎ መፈጸሙንና ዋጋን ጨምሮ ከአቅራቢው ድርድር ማድረግ ይችላል፡፡

7.7   በልዩ ሁኔታ በማስፈቀድ የሚፈጸም ግዥ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች በልዩ ፈቃድ ግዥ የሚፈጽሙት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ክፍል ስምንት ከአንቀጽ 44-46 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፦

1. በልዩ ፈቃድ ለሚፈጸሙ ግዥዎች ልዩ ፈቃድ የሚሰጠው የግዥ ዘዴውን፣ የውል አፈጻጸም ስርዓቱን ወይም ሌሎች አሰራሮችን ሲሆን፣ ከተፈቀደው የግዥ ዘዴ፣የውል አስተዳደር ጉዳይ ወይም ሌሎች አሰራሮች ወጪ የግዥ አዋጁንና የአፈጻጸም መመሪያው የተገለጹትን መደበኛ የአሰራር ስርዓቶችን ተከትሎ ይሆናል፡፡

2. ለምሳሌ አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር በተገደበ ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ ለመፈጸም ፈልጎ ነገር ግን ግምታዊ ዋጋው በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3(ሠ) መሰረት ለዕቃ ግዥ ከተቀመጠው የገንዘብ ጣሪያ በላይ ቢሆን እና በግልጽ ጨረታ ግዥ ለመፈጸም በቂ ጊዜ የሌለው ወይም በተገደበ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸሙ ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች መኖራቸው ከተረጋገጠ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ መሰረት በልዩ ሁኔታ በተገደበ ጨረታ ግዥ ሊፈጸም ይችላል፤ ሆኖም በልዩ ሁኔታ ፈቃድ የተሰጠው የገንዘብ ጣሪያው ብቻ ስለሆነም ሌሎች ሂደቶች በግዥ አፈጻጸም መመሪያው የተቀመጠውን አሰራር ተከትሎ የሚፈጸም ይሆናል፡ ፡ በመሆኑም የሚጋበዙ ተጫራቾች ብዛት፣ የጨረታው መቆያ ጊዜ፣ የጨረታ መክፈቻ ጊዜ ፣ የግምገማ ሂደት፣ የቅሬታ አቀራረብ እና የመሰሰሉት በመመሪያው ለተገደበ ጨረታ የተደነገገው ተግባራዊ ይሆናል፡፡

8. የግዥ ስልቶችና አፈጻጸማቸው

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ ስልቶችን ለመመረጥ እና ተግባራዊ ለማድረግ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ምዕራፍ አራት ከአንቀጽ 47-58 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ፡-

8.1 የግዥ ስልት ዓይነቶች፤

1. የመንግስት የልማት ድርጀቶች በግዥ አፈጻጸም መመሪው አንቀጽ 47 መሰረት የሚከተሉትን የግዥ ስልቶች በመጠቀም ግዥ መፈጸም ይችላሉ፡፡

   - በማዕቀፍ የሚፈጸም ግዥ፣
   - በጋራ የሚፈጸም ግዥ፤
   - በሊዝ ስምምነት የሚፈጸም ግዥ፣
   - በራስ ኃይል የሚፈጸም ግዥ፣
   - በተርንኪ የሚፈጸም ግዥ፣
   - በኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ፣

   ናቸው፡፡

8.2 በኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሀራጅ ጨረታን በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 58 መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

8.3 በራስ ኃይል የሚፈጸም ግዥ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ግንባታን ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግልቶችን በራስ ኃይል ግዥ ለመፈጸም በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 56 በተደነገገው መሰረት ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉ ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪም፤-

1. በራስ ኃይል የግዥ ስልት ግዥ ለመፈጸም የተቀመጠው የገንዘብ ጣሪያ ብር 50,000,000.00 (ሃምሳ ሚሊዮን) ታሳቢ የሚያደረገው ግዥው በመመሪያው በተቀመጡት አግባብነት ባለው የግዥ ዘዴ ግዥ ቢፈጸም ሊያስወጣ የሚችለው ግምታዊ ዋጋ ነው፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 1 የተቀመጠው የገንዘብ ገደብ ቢኖርም በግንባታ ዘርፍ የተሰማሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ያለ ገንዘብ ጣሪያ የራስ ኃይል በመጠቀም የግንባታ ሥራዎችን ወይም አገልግልቶችን ማሰራት ይችላሉ፡፡

9. የግንባታ ሥራ ግዥ የብቃት መስፈርቶች

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የግንባታ መስፈርቶችን ለመወሰን በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 59-71 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

9.1 አጠቃላይ ልምድን በተመለከተ

1. የሚመለከተው አካል በሚሰጠው ደረጃ መሠረት ከደረጃ 6 እስከ 10 ያሉት የሀገር ውስጥ በስራ ተቋራጭ፣በሽርክና ማህበር (Joint Venture) ወይም ለንዑስ ስራ ተቋራጭነት ልምድ መጠየቅ አያስፈልግም፤
2. የሚመለከተው አካል በሚሰጠው ደረጃ መሠረት ከደረጃ 1 እስከ 5 ያሉት የሀገር ውስጥ በስራ ተቋራጭ፣ በሽርክና ማህበር (Joint Venture) ወይም ለንዑስ ስራ ተቋራጭነት ቢያንስ 2 ዓመት የስራ ልምድ ይጠየቃል፤

3. ጨረታው አለም አቀፍ ከሆነ እና የውጪ ሀገር ስራ ተቋራጮች በጨረታው ስለሚሳተፉ አጠቃላይ የስራ ልምድን በተመለከተ በስራ ተቋራጭ፣ በሽርክና ማህበር ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭ ደረጃ በዘርፉ ቢያንስ የ4 ዓመት ልምድ ይጠየቃል፡፡

9.2 ተዛማጅ የስራ ልምድን በተመለከተ

1. የግንባታ ሥራው ግምታዊ ዋጋ ከብር ሦስት ቢሊዮን በታች በሚሆንበት ጊዜ የሚወጣው ጨረታ ለሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ብቻ በሚሆንበት ጊዜ በተዛማጅ የስራ ልምድነት የሚጠየቀው መስፈርት፡- የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ስራ ጋር በተመሳሳይ ቢያንስ አንድ የግንባታ ስራ በስራ ተቋራጭነት፣በሽርክና ማህበር አባልነት ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭነት የሰሩና ቢያንስ የስራውን 70% (ሰባ በመቶ) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ ወይም የተጠየቀውን የተዛማጅ ስራ ልምድ ዋጋ በአንድ ኘሮጀክት በሰሩት የስራ ልምድ ብቻ ማሟላት ካልቻሉ ሊሰራ ከተፈለገው ስራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሦስት ኘሮጀክቶች የሰሩና ቢያንስ የስራውን 70% (ሰባ በመቶ) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ የተጠናቀቁ የዋጋ ድምር በልምድነት ሊያዝላቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም የሶስቱ ኘሮጀክቶች የተናጠል ዋጋ ማሟላት ከሚገባቸው የስራ ልምድ ዋጋ ከሲሶ (1/3) በታች መሆን የለበትም፡፡

ለምሳሌ፡-

- የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ= 3,000,000,000.00 ብር ቢሆን ለተዛማጅ የስራ ልምድነት የሚጠየቀው፡- የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ስራ ጋር በተመሳሳይ ቢያንስ አንድ የግንባታ ስራ በስራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማህበር አባልነት ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭነት ቢያንስ የ3,000,000,000.00 ብር የግንባታ ሥራ ውል እና ቢያንስ የስራውን 70% (ሰባ በመቶ) (በብር 2,100,000,000.00) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ ወይም፣
- ሊሰራ ከተፈለገው ስራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሶስት ኘሮጀክቶች እያንዳንዳቸው በብር የ1,000,000,000.00 ብር የግንባታ ሥራ ውል እና ቢያንስ የስራውን 70% (ሰባ በመቶ) (በብር 700,000,000.00) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ ወይም፣

2. የግንባታ ሥራው ግምታዊ ዋጋ ከብር ሦስት ቢሊዮን በላይ በሚሆንበት ጊዜ የሚወጣው ጨረታ አለም አቀፍ ሆኖ፤

2.1 ለሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች የሚጠየቀው መስፈርት፡-

☞ ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ስራ ጋር በተመሳሳይ ቢያንስ አንድ የግንባታ ስራ በስራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማህበር አባልነት ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭነት የሰሩና ቢያንስ የስራውን 70% (ሰባ በመቶ) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ ወይም

☞ ሊሰራ ከተፈለገው ስራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ አራት ኘሮጀክቶች ቢያንስ የስራውን 70% (ሰባ በመቶ) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ በልምድነት ሊያዝላቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም የአራቱ ኘሮጀክቶች የተናጠል ዋጋ ማሟላት ከሚገባቸው የስራ ልምድ ዋጋ ከሩብ (1/4) በታች መሆን የለበትም፡፡

ለምሳሌ፡-

- የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ=4,000,000,000.00 ብር ቢሆን ለተዛማጅ የስራ ልምድነት የሚጠየቀው፡- የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ስራ ጋር በተመሳሳይ ቢያንስ አንድ የግንባታ ስራ በስራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማህበር አባልነት ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭነት ቢያንስ የ4,000,000,000.00 ብር የግንባታ ሥራ ውል እና ቢያንስ የስራውን 70% (ሰባ በመቶ) (በብር 2,800,000,000.00) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ ወይም፣
- ሊሰራ ከተፈለገው ስራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ አራት ኘሮጀክቶች እያንዳንዳቸው በብር የ1,000,000,000.00 ብር የግንባታ ሥራ ውል እና ቢያንስ የስራውን 70% (ሰባ በመቶ) (በብር 700,000,000.00) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ ወይም፣

2.2 ለዉጭ አገር ስራ ተቋራጮች የሚጠየቀው መስፈርት

ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ በጨረታ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ስራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ቢያንስ ሁለት የግንባታ ሥራዎችን በሥራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማህበር አባልነት ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት የሰሩ እና ቢያንስ የሥራውን 80% (ሰማኒያ በመቶ) በአስተማማኝ እና በአጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው ተብሎ ይጠየቃል፡፡

ለምሳሌ፡-

- የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ= 4,000,000,000.00 ብር ቢሆን ለተዛማጅ የስራ ልምድነት ለውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች የሚጠየቀው፤
- ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ በጨረታ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ስራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ቢያንስ ሁለት የግንባታ ሥራዎችን በሥራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማህበር አባልነት ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት እያንዳንዳቸው በብር 4,000,000,000.00 የግንባታ ሥራ ውል የሰሩ እና ቢያንስ የስራውን 80% (ሰማንያ በመቶ) (በብር 3,200,000,000.00) በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ፣
- በመሆኑም "በአጥጋቢ ሁኔታ የተጠናቀቀ" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የሥራው 70% (ሰባ በመቶ) ወይም 80% (ሰማኒያ በመቶ) እና ከዚያ በላይ የተጠናቀቀ የግንባታ ሥራ ፕሮጀክት ማለት ሲሆን በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቀ ማለት በሥራ ተቋራጩ የተሰራው 70% (ሰባ በመቶ) እና ከዚያ በላይ ሥራ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳና የጊዜ ማራዘሚያ እንዲሁም በተረጋገጠ የክፍያ ሰነድ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለመሰራቱ ከአሰሪ ድርጅቱ የተሰጠ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ የቀረበበት የግንባታ ስራ ፕሮጀክት ማለት ነው፡፡ነገር ግን በግዥ መመሪያው የተደነገገው የተዛማጅ የሥራ ልምድ መስፈርቶች ከደረጃ 6 እስከ 10 ላሉት ሥራ ተቋራጮች ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡
- ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሥራ ተቋራጩ በተዛማጅ የሥራ ልምድነት እንዲያዝለት በሚያቀርበው የግንባታ ዋጋ ላይ ማስተካከያ የሚደረገው፣ ጨረታ ከሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን 28 ቀናት በፊት የነበረውን የምንዛሪ ምጣኔን ውሉ በተፈረመበት ጊዜ በነበረው የምንዛሪ መጣኔ በማካፈል ከተሰላ በኋላ በሚገኘው ውጤት በማባዛት ነው፡፡ ማስተካከያው የሚሰላው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚሰጠውን የውጭ አገር ገንዘብ መሸጫ ዋጋ መረጃ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

ለምሳሌ፡-ወቅታዊ የግንባታ ሥራው ዋጋ ከምንዛሪ ምጣኔ ለውጥ አንጻር ሲሰላ፣

- አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት በ2018 በጀት ዓመት G+7 ለቢሮ አገልግሎት የህንጻ ግንባታ ስራ በጨረታ ለመፈጸም በወጣው ጨረታ ላይ ተዛማጅ የሥራ ልምድ የተጠየቀው በአለፉት አስር ዓመታት የ1 ቢሊዮን ብር ግንባታ በአጥጋቢ ሁኔታ

ያጠናቀቀ ይላል፡፡ ነገር ግን አንድ ሥራ ተቋራጭ ያቀረበው ተዛማጅ የሥራ ልምድ የተጠየቀውን 1 ቢሊዮን ብር ሳይሆን ከ5 ዓመት በፊት (በ2012 ዓ.ም) የ500 ሚሊዮን ብር አንድ ግንባታ ያጠናቀቀ መሆኑን የሚገልጽ ስለሆነ ለግምገማ ዓላማ የዚህ ተጫራች ወቅታዊ ዋጋ የሚሰላው እንደሚከተለው ይሆናል፡

2012 ዓ.ም (1 ዶላር = 53 ብር)፣ 2018 ዓ.ም (1 ዶላር =150 ብር)

150/53x500,000,000 = 2.83x500,000,000.00=1,415,094,339.00

- ይህም ማለት ከ5 ዓመት በፊት (በ2012 ዓ.ም) የ500 ሚሊዮን ብር የግንባታ ስራ በአጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቀ ተጫራች አሁን ባለው የግንባታ ሥራ ዋጋ ብር 1,415,094,339.00 ከሚሰራ የግንባታ ሥራ ጋር ተመሳሳይ ነው ማለት ነው፡፡

9.3 ፋይናንስ አቋምን በተመለከተ የሚቀመጠው መስፈርት

1. የስራ ተቋራጮች ያለፉት አምስት ዓመት የፋይናንስ አቋማቸውን የሚያሳይ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረብ እንደሚኖርባቸው፡፡ በ/ቤቱ ከዚህ እስከ እዚህ በሚል ዓመት ምህረቱን ቢያስቀምጥ የተሻለ ይሆናል፡፡

ለምሳሌ፣ ስራ ተቋራጮች ያለፉት አምስት ዓመት (ከ2012 እስከ 2017 ዓ.ም) የፋይናንስ አቋማቸውን የሚያሳይ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጭ ከተመሰረተ ከአምስት ዓመት በታች ከሆነው የሚያቀርበው የፋይናንስ ሪፖርት ከንግድ ምዝገባ ሰርተፊኬት ወይም ከንግድ ሥራ ፈቃዱ ጋር የሚናበብ ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

2. በስራ ተቋራጮቹ የሚቀርበው የፋይናንስ ሪፖርት ከሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ወይም የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ከሚገኝ ሪከርድ ጋር ተመሳክሮ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

9.4 ዓመታዊ የግብይት መጠን (ተርን ኦቨር)

1. የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮችን በተመለከተ ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሚጠየቀው በግንባታ ላይ ካለና ከተጠናቀቀ የግንባታ ስራ ላይ የተሰበሰበ ክፍያ ዓመታዊ ተርንኦቨር መካከል ተቋራጩ ባለፉት አምስት ዓመት ውስጥ ካስመዘገበው የግንባታ ስራ ዓመታዊ ተርንኦቨር

የተሻለውን በመምረጥ ሆኖ፣ ስራ ተቋራጮች እንዲያሟሉ የሚጠየቁት የተርንኦቨር መጠን የሚሰላው ሊሰራ የታሰበውን የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ፣ቀናትን ወደ ሚቀጥለው ሙሉ ወር በማጠጋጋት ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በሚገመትበት ወርሃዊ ጊዜ በማካፈልና ውጤቱን በ0.6 በማባዛት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ= 400,000,000.00 ብር

ግንባታው የሚጠናቀቅበት ጊዜ =12 ወር ከ20 ቀን ቢሆን

*ዓመታዊ ተርን ኦቨር= ሊሰራ የታሰበው የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ/ግንባታ ይጠናቀቃል ተብሎ የሚገመተው ወር*12*0.6*

የሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች እንዲያሟሉ የሚጠየቅ ዓመታዊ የተርንኦቨር መጠን በብር= $\frac{400,000,000.00}{13}$ *x12x0.6 = 221,538,461.5 ነው፡፡*

2. የውጭ ሀገር ስራ ተቋራጮች ከሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ጋር ጥምረት ፈጥረው የሚወዳደሩ ከሆነ እንዲያሟሉ የሚጠየቁት የተርንኦቨር መጠን የሚሰላው ሊሰራ የታሰበውን የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ፣ቀናትን ወደ ሚቀጥለው ሙሉ ወር በማጠጋጋት ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በሚገመትበት ወርሃዊ ጊዜ በማካፈልና ውጤቱን በ 1.2 በማባዛት ነው፡፡

   ለምሳሌ፡- የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ= 400,000,000.00 ብር

   ግንባታው የሚጠናቀቅበት ጊዜ =12 ወር ከ20 ቀን ቢሆን

   *ዓመታዊ ተርን ኦቨር= ሊሰራ የታሰበው የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ/ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ የሚገመተው ወር*12*1.2*

   የውጭ ሀገር ስራ ተቋራጮች ከሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ጋር ጥምረት ፈጥረው የሚወዳደሩ ከሆነ እንዲያሟሉ የሚጠየቅ ዓመታዊ የተርንኦቨር መጠን በብር= $\frac{400,000,000.00}{13}$ *x12x1.2 = 443,076,923.1 ነው፡፡*

3. የውጭ ሀገር ስራ ተቋራጮች እንዲያሟሉ የሚጠየቁት የተርንኦቨር መጠን የሚሰላው ሊሰራ የታሰበውን የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ፣ቀናትን ወደ ሚቀጥለው ሙሉ ወር በማጠጋጋት ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በሚገመትበት ወርሃዊ ጊዜ በማካፈልና ውጤቱን በ2 በማባዛት ነው፡፡

ለምሳሌ፦ የግንባታ ስራ ግምታዊ ዋጋ= 400,000,000.00 ብር

ግንባታው የሚጠናቀቅበት ጊዜ =12 ወር ከ20 ቀን ቢሆን

*ዓመታዊ ተርን ኦቨር= ሊሰራ የታሰበው የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ/ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ የሚገመተው ወር*12*2*

የውጭ ሀገር ስራ ተቋራጮች ከሀገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ጋር ጥምረት ፈጥረው የሚወዳደሩ ከሆነ እንዲያሟሉ የሚጠየቅ ዓመታዊ የተርንኦቨር መጠን በብር = 400,000,000.00 x12x2 = 738,461,538.5 ነው፡፡
13

4. ስራ ተቋራጮቹ በሽርክና ማህበር ደረጃ ጥምረት ፈጥረው የሚወዳደሩ ከሆኑ እያንዳንዳቸው የሽርክና ማህበሩ አጋር ድርጅቶች (አባላት) ማሟላት የሚገባቸው የተርንኦቨር መጠን ከተጠየቀው ከ25 በመቶ እና የዋናው ስራ ተቋራጭ ደግሞ ከ40 በመቶ ማነስ የለበትም፡፡

ለምሳሌ፡-ዓመታዊ የግብይት መጠን (ተርንኦር) ስሌት ከወቅታዊ ምንዛሪ ለውጥ አንጻር ሲሰላ

- አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት በ2018 በጀት ዓመት G+7 ለቢሮ አገልግሎት የህንጻ ግንባታ ስራ በጨረታ ለመፈጸም በወጣው ጨረታ ላይ የተጠየቀው ዓመታዊ የግብይት መጠን (ተርንኦቨር) ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ 1 ቢሊዮን ብር ተጠይቋል፡፡ ነገር ግን አንድ ሥራ ተቋራጭ ያቀረበው ዓመታዊ የግብይት መጠን (ተርንኦቨር) የተጠየቀውን 1 ቢሊዮን ብር ሳይሆን ባለፉት አምስት ዓመታት (ከ2012-2017) ከሰራው የተሻለው (ከፍተኛው) በ2012 ዓ.ም 500 ሚሊዮን ብር ነው፡፡

  ለግምገማ ዓላማ የዚህ ተጫራች ወቅታዊ ዋጋ የሚሰላው እንደሚከተለው ይሆናል፡

  የሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም (1 ዶላር = 58 ብር)፣ ከጨረታው መዝጊያ 28 ቀን በፊት (2018 ዓ.ም) ያለው ምንዛሬ (1 ዶላር =150 ብር) 150/58x500,000,000 =2.59x500,000,000.00=1,295,000,000.00

- ይህም ማለት ከፍተኛ ዓመታዊ ሽያጭ (የ2012 ዓ.ም) 500 ሚሊዮን ብር ከወቅታዊ ዋጋ አንጻር ሲሰላ 1,295,000,000.00 ነው፡፡ በመሆኑም ተጫራቹ ያቀረበው ዓመታዊ የግብይት መጠን (ተርንኦቨር) በጨረታ ከተጠየቀው 1 ቢሊዮን በላይ ስለሆነ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

9.5 በግንባታ ስራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች ትምህርት እና ብቃት

1. እንደ ግንባታ ስራው ባህርይ ብቻ ለስራው የሚያስፈልጉ ብቁ ባለሙያዎችን በሚፈለገው መጠን እና ስብጥር እንደሚያቀርቡ ማሳየትና ባለሙያዎቹም ለስራው በሚያስፈልጉበት ጊዜ ሁሉ በተመደቡበት ቦታ ላይ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን የሚያመለክት አስተማማኝ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ባለሙያዎች የግንባታ ስራ ተቋራጩ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ሰራተኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
2. የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ከሥራ ተቋራጮች የቀረበላቸውን በግንባታ ስራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅትና ብቃትን የተመለከተ ማስረጃ ትክክለኛነት በግንባታ ጊዜም ቢሆን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

9.6 ለግንባታ ስራው የሚያስፈልግ መሳሪያ

እንደ ግንባታ ስራው ባህሪ ብቻ ለስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ዓይነትና መጠን በሚፈለጉበት ጊዜ ሁሉ ማቅረብ እንደሚችሉ የሚያሳይ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የሚቀርቡት መሳሪያዎችም በስራ ተቋራጮች ባለቤትነት ስር የሚገኙ ወይም በኪራይ የተገኙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

9.7 ከአንድ በላይ የግንባታ ስራዎች ግዥ ላይ የልምድ አያያዝ

1. በአንድ የጨረታ ማስታወቂያ የሚወጡ ንዑስ የግንባታ ስራዎች ቁጥር ከአንድ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ማንኛውም ተጫራች መሳተፍ የሚፈልግባቸውን ንዑስ የግንባታ ስራዎች ዓመታዊ ተርንኦቨር፣ የገንዘብ አቅምና ተዛማጅ የስራ ልምድ መስፈርት በድምር ማሟላት አለበት፤
2. አንድ ተጫራች ለእያንዳንዱ ንዑስ የግንባታ ስራ የተጠየቀውን መስፈርት አሟልቶ ነገር ግን ለተሳተፈባቸው ንዑስ የግንባታ ስራዎች በድምር የሚጠየቀውን መስፈርት በማያሟላበት ጊዜ ምንም እንኳን በተናጠል ሲታይ ለየንዑስ የግንባታ ስራዎቹ የተሻለ ዋጋ ቢያቀርብም ውል ሊፈጽም የሚችለው መስፈርቶቹን ማሟላት በቻለበት ልክ ብቻ ነው፡፡
3. ለመንግስት የልማት ድርጅቱ የተሻለ ጠቀሜታ ከማስገኘት አንፃር ሥራ ተቋራጩ በሰጠው ዋጋ ውል የሚገባበትን ንዑስ የግንባታ ስራ ወይም የግንባታ ስራዎች የመወሰን ስልጣን የመንግስት የልማት ድርጅቱ ነው፡፡

10. የጨረታ ሥነ-ስርዓት

10.1 የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ

የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያው በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 72 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

10.2 የቅድመ ብቃት ጥሪ

1. የመንግስት የልማት ድርጅቱ አቅም ያላቸው ተወዳዳሪዎች በቅድሚያ በመለየት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 32 መሰረት በቅመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ለአንድ ጊዜ ለሚፈጸም ግዥ ወይም በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 48 መሰረት በስትራቴጂክ አጋርነት ለረጅም ጊዜ (ለሁለት ዓመት) ለሚፈጸም ግዥ አቅራቢዎችን ለመምረጥ የሚከናወን የቅድመ ብቃት ጥሪ ያደርጋል፤

2. የመንግስት የልማት ድርጅቱ ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱን የሚያሟሉ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ሊያወጣ ይችላል፤
   - ሀ) በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ወይም በባህሪው ውስብስብ የሆነ የዲዛይን፣ የማምረትና የተከላ ሥራ በአንድ ድርጅት መጠናቀቅ ያለበት የግንባታ፣ የማምረቻ መሳሪያ ወይም የቴክኖሎጂ ግዥ ሲሆን፣ ወይም
   - ለ) የሚቀርበው ዕቃ ወይም መሳሪያ ጥራትና ጠቀሜታ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው እና የተከላ አገልግሎትን ያካተተ ሲሆን፣ወይም
   - ሐ) የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ግዥ በመሆኑ ብቃታቸው በቅድመ ብቃት ምዘና የሚረጋገጡ ተጫራቾች ብቻ በውድድሩ ተካፋይ መሆን እንደሚገባቸው ሲታመንበት፣
   - መ) በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 48 መሰረት አቅራቢዎች በአጋርነት መዝግቦ በረጅም ጊዜ ለሚፈጸም ግዥ ለመጠቀም፣

3. የቅድመ ብቃት ጥሪ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የቅድመ ብቀት መስፈርቱን ከአለፉ ለአንድ ጊዜ ለሚወጣ ጨረታ ወይም ለተከታታይ ሁለት ዓመት በተለያየ የግዥ ዘዴዎች ለሚፈጸሙ ግዥዎች እንዲሳተፉ ይደረጋል፤

4. የቅድመ ብቃት ጥሪው ፍላጎት ለአላቸው ለሁሉም ተወዳዳሪዎች ክፍት መሆን የሚገባው ሲሆን ተወዳዳሪዎች በቂ መረጃ ማግኘት እንዲችሉ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

- የመንግስት የልማት ድርጅቱ ስምና አድራሻ፣
- የግዥውን ምንነት የሚያመለክት መግለጫ፣
- የማቅረቢያና ማጠናቀቂያ ጊዜ፣
- የጨረታው ሠነድ የሚገኝባቸውን ሁኔታና ቦታ፤
- ዝቅተኛውን የብቃት መገምገሚያ መስፈርት፣
- የብቃት ማመልከቻው የሚቀርብበት ጊዜ፣
- ሌሎችም አስፈላጊ መረጃዎች፣

10.3 የጨረታ ሠነድ

የጨረታ ሠነድ አተቃቀመን በሚመለከት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 73 መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡

10.4 የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ

በመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚዘጋጀው የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 74 መሰረት የሚዘጋጅ ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪም የተጫራቾች መመሪያን መሰረት አድረጎ የሚዘጋጅ ሲሆን በተጫራቾች መመሪያ እና በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰነጠረዥ መካከል ልዩነት ካለ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ ላይ የተገለጸው የበላይነት ይኖረዋል፡፡

10.5 የብቃትና የግምገማ መስፈርት አዘገጃጀት

በጨረታ ሠነዱ ክፍል 3 የሚዘጋጀው የብቃትና የግምገማ መስፈርት ሲዘጋጅ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 75 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. ይህ ክፍል በጨረታው የሚያሸንፈው ድርጅት ውሉን በብቃት ስለመወጣቱ ለማረጋገጥ ተጫራቹ ቀደም ሰል ስለአከናወናቸው ስራዎች እና ወቅታዊ አቅም ለመለካት የሚያስችል መስፈርት የሚገለጽበት ክፍል ነው፤

2. በዚህ ክፍል የተጫራቾችን የፋይናንስ አቅም፣የሰው ኃይል፣ለስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች እና ሌሎችም ስራውን ለማከናውን የሚያስችሉ የብቃት መስፈርቶች የሚገለጹበት ነው፡፡
3. የግምገማ ዘዴዎች ማለትም፡-
    - ለግዥው የተቀመጠውን የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት ካሟሉት ተጫራቾች መካከል አነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች መምረጥ፣ወይም
    - ግዥው የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴት ሊወስኑ የሚችሉ የቴክኒክ መስፈርቶችን ድርሻ እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን አንፃራዊ ክብደት በጨረታ ሰነዱ ላይ በማስቀመጥ በቴክኒክ እና በዋጋ ድምር ውጤት ከፍተኛ ያመጣው ተጫራች የሚመረጥበት ዘዴ የሚገለጽበት ክፍል ነው፡፡
4. ከላይ በተራ ቁጥር 3 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በቴክኒክ እና በዋጋ በድምር ውጤት የሚደረገው ግምገማ ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች እንዲያሸነፍ እና የተቋሙን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያሳጣ ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል፡፡

10.6 የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

በጨረታ ሠነዱ ክፍል 6 የሚዘጋጀው የቴክኒክ መስፈርት ሲዘጋጅ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 77 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚጠይቁ ግዥዎች በአዋጁ አንቀጽ 25 መሠረት ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው፤
2. የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍለጎት መግለጫ በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ እንደግዥው ዓይነት ጠቀሜታን፣ አሠራርን፣ የቴክኒክ ወይም የዲዛይን ባህርይን እና የመሳሰሉትን መሠረት በማድረግ ውድድርን እንዳይገድብ ተደርጎ መዘጋጀት አለበት፤
3. የሚፈለገው ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ የግንባታ ሥራ ወይም አገልግሎት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ግዥው እንዲፈፀምለት በሚፈለገው ክፍል ወይም ስለሚፈፀመው ግዥ በቂ ዕውቀት ባላቸው የመንግስት የልማት ድርጅቱ ባለሙያዎች እና በግዥ የሥራ ክፍሉ በጋራ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን ውስብስብ ለሆኑ ግዥዎች የፍላጎት መግለጫ አዘገጃጀት ከመንግስት የልማት ድርጅቱ ውጭ ያሉ ባለሙያዎችን ድጋፍ ሊጠይቁ ወይም አማካሪ ቀጥረው ሊያሠሩ ይችላሉ፣

4. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ ግዥ ሚፈጸምለት አካል በሚጠይቅበት ወቅት ካልተፈቀደ በስተቀር የተወሰነን በተለየ ሁነአምራች የንግድ አገልግሎት ሰጪ እና የተመረተበትን አገር ማመልከት የለበትም፤
5. ከዚህ በላይ በተቀመጡት ስነስርዐቶች ወይም ሂደቶች መሰረት የተዘጋጀው የፍላጎት መ□ለ□ በሁሉም ተጫራቾች ዘንድ ፍትሃዊና ግልጽ ውድድር እንዲኖር ማስቻል ይኖርበታል፤
6. ምርታቸው ከተገለጸው ዲዛይን ወይም መግለጫ ጋር ተዛማጅ ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ተጫራቾችን ብቻ የሚጋብዝ በመሆኑ በቀጥታ ዲዛይንን ወይም ባህሪያትን በመዘርዘር ላይ የተመሰረተ መግለጫ ውድድርን ሊያጠብ ወይም ሊወስን እንደሚችል መታወቅ ይኖርበታል፤

- *ለምሳሌ አንድ የመንግሥት የልማት ድርጅት ተሽከርካሪ መግዛት ቢ□ል□ የጨረታ ሰነዱ በስም የተገለጸን ተሽከርካሪ የሚመለከት፣ ብራንድ፣ ሞዴል፣ ወጁም □ር□ር የቴክኒክ መግለጫው ከአንድ አምራች ጋር የተያያዘ መሆን የለበትም:: ምክንያቱም በዚህ መንገድ የተዘጋጀ የፍላጎት መ□ለ□ ስፔሲፊኬሽኑ በአንድ አቅራቢ ብቻ እንዲሟላ የማድረግ ውጤት ስለሚያስከትል ሌሎች የተሽከርካሪ አምራቾች በጨረታው እንዳይሳተፉ ያደርጋል:: ሁለት የተለያዩ ተሽከርካሪዎች አንድ ዓይነት ሊሆኑ አይችሉም፣ ነገር ግን በአብዛኛው የተሽከርካሪ የቴክኒክ መግለጫዎች የተቀራረቡ በመሆናቸው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው ዋናና መሠረታዊ የሆኑ የጥራት ባህርያትን ብቻ እንዲጠቅስ ተደርጎ ከተዘጋጀ ሁሉም ተጫራቾች መወዳደር ይችላሉ ለምሳሌ 2055 ኪ.ግራም ክብደት ያለው ተሽከርካሪ ከማለት ይልቅ ክብደቱ ከ1800 እስከ 2100 የሆነ ቢባል ይመረጣል::*

  በተመሳሳይ የኮምፒዩተር ግዥን በሚመለከት የሚዘጋጀው የፍላጎት መግለጫ በዋና ዋና የጥራት ባህርያት ላይ ያተኮረ ሆኖ የሚገጣጠመው የኮምፒውተር ክፍል ጥራት በISO *የተረጋገጠ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል:: ሆኖም የኮምፒውተሩ ብራንድ ወይም ስም በምንም መንገድ መጠቀስ የለበትም አስገዳጅ ወይም ሌላ አሳማኝ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በፍላጎት መግለጫው ውስጥ የሚካተቱት መለኪያዎች ተቀባይነት ያለውን አነስተኛና ከፍተኛ ገደብ በመግለፅ ቢዘጋጁ ይመረጣል::*

  ነገር ግን የመንግሥት የልማት ድርጅቱ የቴክኒክ መግለጫውን ለማዘጋጀት በሚፈልግበት ጊዜ ዕቃው ከአንድ የተለየ ድርጅት ብራንድ (የንግድ ምልክት) ብቻ

የሚገኝ መሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቱ ማረጋገጥ ከተቻለ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ንግድ ምልክቱን በማስቀመጥ እና ወይም ተመሳሳይ የሚለውን ሐረግ/ቃል በመግለጫው ውስጥ በማካተት መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

7. □ረጸ□ች ከዚህ በታች በተ□ረ□ሩት ብቻ የሚዘጋጁ ባይሆኑም በነዚህ ድርጅቶች የሚወጡ ደረጃዎችን መከተል ያስፈልጋል፡፡

ሀ. □ለም አቀፍ የደረጃ□ች ድርጅት (ISO)፣

ለ. የአሜሪካ □□ረጸ□ች መመዘኛ □□□ች (ASTM)፣

ሐ. አገር አቀፍ ደረጃ□ች ለምሳሌ የኢትዮጵያ ደረጃ□ች ኢንስቲትዩት፣

8. በየጊዜው ለሚገዙና ግዥያቸው ተከታታይነት ባለው መንገድ የሚፈፀም ለምሳሌ ለወረቀት፣ ለቢሮ መሣሪያዎች፣ ለሌሎች አላቂ ዕቃዎች ወዘተ... የመንግሥት የልማት ድርጅቶች መደበኛ የፍላጎት መግለጫ በማዘጋጀት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

9. በ□ዱ □ነሚው የመንግስት የልማት ድርጅት የሚዘጋጀው የቴክኒክ ዝርዝር አግባብነት እስካለው ድረስ የሚከተሉትን ነገሮች መሰረት ያደረገ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ስፔሲፊኬሽን በዲዛይን ወይም በዝርዝር ባህሪያት ላይ ሳይሆን በጠቀሜታ ላይ ማተኮር ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ አንድ የውሃ መሳቢያ ሞተር መግዛት ቢያስፈልግ የጠቀሜታ የቴክኒክ ዝርዝሩ የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊይዝ ይችላል፡፡

- በአንድ ሰዓት ውስጥ የሚስበው ውሃ የሊትር መጠን፣
- ተቀባይነት ያለው የሞተሩ አነስተኛ (□ቅተኛ) የፈረስ ጉልበት ፣
- ሞተሩ በሚሰራበት ወቅት የሚፈጠረው ከፍተኛው የድምጽ መጠን፣ ..ወዘተ

10. ለሚገዛው ዕቃ የጥራት ደረጃዎች መኖራቸው ከታወቀ እንደአግባብነቱ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ወይም አገር አቀፍ ደረጃዎች ወይም ኮዶችን በማመልከት የፍላጎት መግለጫን ማዘጋጀት ይቻላል፡፡

11. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ምርታቸው ከተገለጸው ዲዛይን ወይም መግለጫ ጋር ተዛማጅ ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ተጫራቾችን ብቻ የሚጋብዝ በመሆኑ በቀጥታ ዲዛይንን ወይም ባህሪያትን በመዘርዘር ላይ የተመሰረተ መግለጫ ውድድርን ሊያጠብ ወይም ሊወስን እንደሚችል መታወቅ ይኖርበታል፡፡

12.የመንግሥት የልማት ድርጅቱ የቴክኒክ መግለጫውን ለማዘጋጀት በቂ የቴክኒክ እውቀት ከሌለው ወይም መግለጫውን ተጫራቾች በቀላሉ የማይረዱት ከሆነ አንድ የተለየ ብራንድ (የንግድ ምልክት) መጠቀም የሚቻል ሲሆን፣ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ወይም ተመሳሳይ የሚለውን ሐረግ በመግለጫው ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል፡፡

13. የፍላጎት መግለጫው እንደግዥው ዓይነት በተለያየ መንገድ የሚዘጋጅ ቢሆንም፣ እንደአጠቃላይ መርህ ቢያንስ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

- ለመግዛት የተፈለገው ዕቃ ስያሜ ወይም መግለጫ፣
- ለመግዛት የሚፈለገው ዕቃ ነገር ጥራት፣
- የአፈፃፀም (የክንውን) ደረጃዎች (መለኪያዎች)፣
- የደህንነት መለኪያዎችና (Safty Standarde) ልክ (ቅርፅ)
- የዕቃውን አስተሻሸግና የመለያ ምልክቱ አደራረግ፣
- ለመግዛት የተፈለገው ዕቃ የአመራረት ሂደትና ዘዴዎች፣
- የሚገዛው ዕቃ ወይም መሣሪያ ማሟላት የሚገባውን የጥራት ደረጃ ማሟላቱን ለማረጋገጥ ፍተሻ የሚካሄድበትን ሁኔታ፣

14.**የፍላጎት መግለጫ እንደ □□ ዉ ሁኔታ የተለያየ መጠሪያ ያለው ሲሆን፣**

- ለዕቃ (Specfication)
- ለግንባታ ሥራ (Bill of Quantity)
  - የግንባታ ዘርፍ ስራዎች የጥራት ባህሪያት የቁጥጥር ዘዴዎችንና የግንባታ ቴክኒኮችን ያካትታሉ
- ለምክርና ለሌሎች አገልግሎቶች ቢጋር (TOR)
  - የፍላጎት መግለጫ የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት አይነት፣ የሚጠበቀውን ውጤት፤ የሚፈጀውን ጊዜ፣ አማካሪው ሊኖረው የሚገባውን የድርጅትም ሆነ የሰው ኃይል ብቃት፣ የስራ ልምድ እና የመሳሰሉትን የሚገልጽ መሆን አለበት፣

15.የዕቃ ወይም የመሳሪያ የፍላጎት መግለጫዎች **(Specification)**

የዕቃ ወይም የመሳሪያ የፍላጎት መግለጫዎች (Specification) የዕቃ ወይም የመሳሪያ የፍላጎት መግለጫዎች (Specification) በሶስት ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡ እነሱም የዲዛይን ወይም ቴክኒካዊ (Design or technical Specification)፣ የክዋኔ (Performance Specification) እና መሣሪያው የሚከናውነው ተግባር (Functional specification) ናቸው፡፡ እነዚህም ሲተነተኑ፤

- በዲዛይን ወይም ቴክኒካዊ (Design or technical Specification) የፍላጎት መግለጫ ዝግጅት ወቅት መንግስት የልማት ድርጅተመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚፈለገውን ዕቃ ለማምረት ወይም ለማዘጋጀት የሚያስፈልገውን የጥሬ ዕቃና ሌሎች ግብዓቶች እንዲሁም ዕቃውን ለማምረት ወይም ለማዘጋጀት የሚከናወኑትን ተግባራት በግልጽ ማስፈር ይኖርበታል፡፡ የዚህ ፍላጎት መግለጫ ዓይነት ንድፎችን፣ ልኬቶችን፣ የሚቀርበው ዕቃ በመግለጫው ከሰፈረው ደረጃ ወይም ስታንዳርድ ወይም ገደብ የሚርቅበት መጠን (Tolerance፡ Allowance made for deviation) ወይም፣ የሙከራ ወይም የፍተሻ ሂደቶች (Testing Procedure) እና ሌሎች ዝርዝሮችን የሚያካትት ሲሆን የመንግስት የልማት ድርጅቱ ይህን ዓይነት መግለጫ ጥቅም ላይ የሚያውለው የተፈላጊውን ዕቃ ወይም ምርት ጥራትና ክንውን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም የመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚፈልገው ዕቃ በጠየቀው መስፈርት መሰረት እንዲቀርብለት ግዴታ የሚጥል ሲሆን የዚያኑ ያህል በኋላ ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ወይም ኃላፊነት ለመሸከም ዝግጁ መሆን ይኖርበታል፡፡
- የክዋኔ የቴክኒክ መግለጫ (Performance Specification) ከዲዛይን ወይም ከቴክኒካዊ መግለጫ ጋር ሲነጻጸር ዝርዝሩ አነስተኛ ሲሆን የልማት ድርጅቱ አቅራቢው ዕቃውን ለማዘጋጀት ስለሚሰራው ንድፍና ስለ አመራረቱ ሂደት ሳይገልጽ የሚፈለገው ዕቃ መፈጸም ያለበትን ተግባር ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ አንድ የማተሚያ ማሽን በደቂቃ ውስጥ ሊያትም የሚችለው የወረቀት መጠን፡፡

- ዕቃው ወይም መሳሪያው የሚሰራው ወይም የሚፈጽመው ተግባር የቴክኒክ መግለጫ (Functional specification)፡፡ ይህ የስፔሲፊኬሽን አዘገጃጀት በክዋኔ ላይ ተመስርቶ ከሚዘጋጅ ስፔሲፊኬሽን ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ልዩነቱ የዲዛይን ስራውን ኃላፊነት ለአቅራቢው መስጠት ላይ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ፍላጎትን በክዋኔ ደረጃ ከመግለጽ ይልቅ ይህ ዓይነት የመግለጫ ዓይነት የሚያተኩረው የተጠየቀው ዕቃ በሚሰጠው ጥቅም ላይ ነው፡፡

16. በመንግስት የልማት ድርጅቱ የቴክኒክ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ መግለጫው ከፍላጎቱ በላይ እንዳይለጠጥ መጠንቀቅ አለበት፡፡ ከሚፈለገው በላይ የተለጠጠ የቴክኒክ መግለጫ አላስፈላጊ ተጨማሪ በመንግስት የልማት ድርጅተ ቱ ላይ የሚያስከትል ሲሆን የህዝብ ገንዘብ እንዲባክን ምክንያት ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተለጠጠ የቴክኒክ መግለጫ የተጫራቾችን ቁጥር ሊገድብ ስለሚችል በአቅራቢዎች መካከል አድልዎ ይፈጥራል፡፡ ከዚህ ሌላ የቴክኒክ

መግለጫንም አላግባብ ማሳነስ ወይም ቁጥብ ማድረግ የሚፈለገውን ዕቃ በሚገባ እንዳይገልጽ ስለሚያደርገው በተጫራቾች ምዘናና በውል አፈጻጸም ወቅት እንቅፋት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ስለዚህ የመንግስት የልማት ድርጅቱ ፍላጎቱን በሚያሟላ መልኩ የተመጣጠነ የቴክኒክ መግለጫ ማዘጋጀት አለበት፡፡

17.የግንባታ ስራ የቴክኒክ መግለጫ (Works Technical Specification)

ከላይ ለዕቃ ግዥ የተገለጹ የቴክኒክ መግለጫ ጽንሰ ሃሳቦች ለግንባታ ስራ የቴክኒክ መግለጫም ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ በነጠላ ዋጋ የውል ዓይነት (Unit Price Contract) ላይ የመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚሰሩትን የግንባታ ዝርዝሮች የሚያሳይ መግለጫ (Bill of Quantity) አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ተጫራቹ ደግሞ ለእያንዳንዱ የግንባታ የስራ ዝርዝር በመጠን ላይ ተመስርቶ የሚወዳደርበትን የነጠላ ዋጋ ያሰፍራል፡፡ በቁርጥ ዋጋ ላይ ተመስርቶ የሚፈጸም የግንባታ ስራ ውል (Lump Sum Contract) ሲሆን ደግሞ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚሰሩ የግንባታ ስራ ዝርዝሮችን በቴክኒክ መግለጫው ላይ ያሰፍርና አቅራቢው ጥቅል ዋጋ ይሰጣል፡፡

18.የመወዳደሪያ ሃሳብ በመጠየቅ የሚፈጸም ግዥ (የምክር አገልግሎት ግዥ) የስራ ዝርዝር ማጣቀሻ ወይም የቴክኒክ መግለጫ (ቢ.ጋር)

1. ቢ.ጋሩ የመንግስት የልማት ድርጅቱ መግዛት የሚፈልገውን ነገርና አቅራቢው ሊፈጽመው የሚገባውን ተግባርና በመጨረሻ የሚጠበቀውን ውጤት (Expected Result) መግለጽ አለበት፡፡ የስራ ዝርዝር ማጣቀሻው የሚሰራውን ስራ፣ የአቅራቢውንና የመንግስት የልማት ድርጅቱን ኃላፊነት፣ ስራው የሚከናወንበትን ዘዴና የክትትል መርሃ ግብሩ የሚጠናቀቅበትን ጊዜ የሚገልጽ ከመሆኑም በላይ ለውል አፈጻጸም መሰረትም ይሆናል፡፡
2. የመግለጫው ማቅረቢያው ፎርም የምክር አገልግሎቱን ዓላማ፣ ተግባራት፣ የስራውን ወሰን፣ አማካሪው ለስራው ሊኖረው የሚገባውን የሰው ኃይል፣ መጠን፣ የብቃት ደረጃ ይዞታ የግብዓት ስራው የሚከናወንበት፣ ቦታና ጊዜ የሪፖርትና የርክክብ መርሃ ግብር፣ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችና በየደረጃው የሚጠበቁ ውጤቶችን (Deliverables) ባካተተ መልኩ መዘጋጀት አለበት፡፡

ለምሳሌ፣

- የክንውን መርሃ ግብር (Schedule of Performance)

  በዚህ ክፍል የመንግስት የልማት ድርጅቱ የምክር አገልግሎቱን ዋና ተግባራትንና የሚፈጸሙበትን ጊዜ የሚያመለክትበት ሲሆን፣ በዚህ መርሃግብር የክንውን ቅደም ተከተሎችን ሂደት እና ክፍያን ይቆጣጠርበታል፡፡

- ዋና ዋና የባለሙያ ፍላጎት (Key Personnel Requirement)

  በዚህ ክፍል በመንግስት የልማት ድርጅቱ ለምክር አገልግሎቱ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና የባለሙያዎች ዓይነትና የሙያ ደረጃ ያሰፍራል፡፡ የባለሙያዎች የትምህርት ወይም የቴክኒክ ብቃቶች፣ በስራው ላይ ያላቸው ልምድ፣ አጠቃላይ የስራ ልምድ፣ የውጭ አገር አሰራር እውቀት ወይም በውጭ አገር ያለ ልምድ፣ የአካባባቢው ሁኔታ እውቀት (የአገር ውስጥ ወይም የክልል ተመሳሳይ ልምድ) እና የቋንቋ አስፈላጊነት የዚህ ክፍል አካላት ተደርገው መገለጽ ይኖርባቸዋል፡፡

- ግብዓቶችን በተመለከተ

  - የእያንዳንዱ ባለሙያ ለሥራው የሚያውለው ወር/ቀን/ሰዓት ምጣኔ (Number of person month/sdays/hours
  - ጠቅላላ ሥራው የሚያሳየው ባለሙያዎች ወር/ቀን/ሰዓት ምጣኔ (Total number of person months /days/ hours)
  - ጠቅላላ የስራ ጊዜ ምጣኔን Total Work Duration) በሚገልጽ መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

3. ከዚህ በተጨማሪ ለምክር አግግሎቱ ስራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችና ሰነዶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቱ ባለሙያዎች በዚህ ስራ ውስጥ ያላቸው ሚና መገለጽ ይኖርበታል፡፡

4. የምክር አገልግሎቱ የሪፖርት ዓይነቶች የመነሻ ሪፖርት (Inception Report)፣ ጊዚያዊ ሪፖርት (Interim Report) እና የመጨረሻ ሪፖርት (Final Report) በመባል ይታወቃሉ፡፡

19.በቴክኒክ መግለጫ ዝግጅት ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ችግሮች

- የቴክኒክ መግለጫ የተወሰኑ አቅራቢዎችን ወይም ምርቶችን ወይም አቅራቢዎችን ፍላጎት ብቻ እንዲያሟላ ሆኖ በማዘጋጀት እንዲሁም በቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ላይ የዕቃን

ወይም የንግድ ምልክት ወይም ስያሜን ወይም የሚመረትበትን አገር በመጥቀስ በርካታ ተጫራቾችና ምርቶች በውድድሩ ውስጥ እንዳይሳተፉ በማድረግ መንግስት ከበርካታ ተጫራቾች ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም ማሳጣት፣

- ለሚሟላት ከባድ፣ ውስብስብና የሚያወዛግብ እንዲሁም ግልጽ ያልሆነ የቴክኒክ መግለጫ በማዘጋጀት የግዢ ሂደቱ ችግር ውስጥ እንዲወድቅ ማድረግ፣

መፍትሂዎች

- የተለየ ፍላጎት ለሚሟላት ካልሆነ በስተቀር የመንግስት የልማት ድርጅቶች የቴክኒክ መግለጫ ሲያዘጋጁ ውድድርን የማይገድብ ወይም በርካታ ተጫራቾችን ሊያሳትፍ የሚችል የፍላጎት መግለጫ እንዲያዘጋጁ ይጠበቃል፡፡
- የቴክኒክ መግለጫው ከባድ፣ ውስብስብ እና ግልጽ በማይሆንበት ጊዜ ተጫራቾች ለመረዳት የሚቸግራቸው ሲሆን በውል አፈጻጸም ወቅት ከመንግስት የልማት ድርጅቱ ጋር አላስፈላጊ ውዝግብ ውስጥ እንዲገቡ ከማድረግ አልፎ ውል እንዳይፈጸም አንድ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ የመንግስት የልማት ድርጅቶች መግለጫውን በሚያዘጋጁበት ጊዜ እነዚህን ችግሮች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

10.7 ስለ ናሙና አቀራረብ

የመንግስት የልማት ድርጅቱ ለሚፈጸመው ግዥ የቴክንክ ፍላጎት ለማዘጋጀት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወይም ከተዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጨማሪነት ግዥው በተሻለ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የናሙና ምልከታ ሲኖረው መሆኑ ሲታመንበት ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 80 በተደነገገው መሰረት ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም፡

1. በግምገማ ወቅት ናሙና የሚመረጠው በተጠቃሚ ክፍል ወይም ስለግዥው በቂ ዕውቀት ባላቸው ባለሙያዎች መሆን ይገባዋል፤
2. በተቻለ መጠን ውድድርን ለማበረታታት ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይነት ያላቸውን ከአንድ በላይ ናሙናዎች መመረጥ አለባቸው፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ከአንድ በላይ ናሙና ለመምረጥ ታስቦ ጥራት የሌላቸውን ናሙናዎች መምረጥ የማያስፈልግ ሲሆን ከአንድ በላይ ወይም የሚረጥ ናሙና ካልተገኘ ናሙና የሚመርጠው ኮሚቴ ማብራሪያ ሊሰጥ ይገባዋል፡፡

10.8 አጠቃላይና ልዩ የውል ሁኔታዎች

አጠቃላይ እና ልዩ የውል ሁኔታዎች በጨረታ ሰነዱ ክፍል 7 እና 8 ላይ የሚገለጽ ሲሆን በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 78 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪም፡-

1. ይህ ክፍል በጨረታው አሸናፊ የሚሆነው ድርጅት ከግዥ ፈጻሚው የመንግስት የልማት ድርጅቱ ጋር ውል የሚገባበት የውል ረቂቅ ሲሆን ተጨራቾች በጨረታ ወቅት ማወቅ ይገባቸዋል፤
2. አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች የማይቀየር(Standared) ሲሆን ልዩ ውል ሁነታዎች ደግሞ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎችን መሰረት አድርጎ በግዥ ፈጻሚው የመንግስት የልማት ድርጅት የሚዘጋጅ ሲሆን በአጠቃላይ ውል ሁኔተዎች እና በልዩ የውል ሁኔታዎች መካከል ልዩነት ካለ በልዩ የውል ሁኔታዎች ላይ የተገለጸው የበላይነት ይኖረዋል፡፡
3. በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ድርጅት ጋር የሚገባው የውል ስምምነት ሰነድ በተቻለ መጠን በጨረታ ወቅት ለተጫራቾች ከተሸጠው መደበኛ የጨረታ ሰነድ ላይ ከአለው የውል ክፍል ጋር መሰረታዊ የሆነ ልዩነት ሊኖረው አይገባም፡፡

10.9 ጨረታ ለተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ

ጨረታ ለተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 79 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. የመንግስት የልማት ድርጅቱ ጨረታ ለተጫራቾች ክፍት ሆኖ የሚቀይበት ቀን በመመሪያው ከተቀመጠው አነስተኛ ቀን ማነስ የለበትም፤
2. የመንግስት የልማት ድርጅቱ የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የመጫረቻ ሰነድ ለተጫራቾች ክፍት ሁኖ የሚቆይበት ቀናቶች የሚከተሉትን መሠረት አድርጎ ይወስናል፤
    - ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተቀባይነት ያለው የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት፣ መረጃ ለማሰባሰብ፣ ለመተንተን.....፣ እንደአግባብነቱ እሽሙር ወይም ሽርክና ለመመስረት፣ ከአምራቹ የሚሰጥ ውክልና እና የመፈረም ሥልጣን ማረጋገጫ ለማግኘት እና ሌሎች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚፈጅባቸውን ጊዜ፣

- ከዕጩ ተወዳዳሪዎች በጨረታ ሰነዱ ይዘት ላይ ሊቀርቡ ለሚችሉ ጥያቄዎች ማብራሪያ ለመስጠት፣ እንዲሁም ማሻሻያ ለማድረግ የሚፈጅበትን ጊዜ፣
- ለግዥው ናሙና ማቅረብ የሚያስፈልግ ከሆነ ናሙና ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ጊዜ፣
- በተለይ የግንባታ ሥራ ግዥ በሚሆንበት ጊዜ ለግንባታ ቦታ ጉብኝት የሚያስፈልገውን ጊዜ፣

10.10በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ

በጨረታ ሰነድ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 81 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፤

1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ራሳቸው ወይም የጨረታ ሠነዱ በገዙ ተጫራቾች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሰረት የጨረታ ሠነድ የማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት የቸረታ ሠነድ ይዘት ማሻሻያ ሊያደርጉ ይችላሉ፤
2. ማሻሻያው የጨረታ ሰነዱ አካል የሚሆን ሲሆን በጽሁፍ ወይም በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ዘዴ የጨረታ ሠነድ ለገዙ እንዲሁም የጨረታ ሰነድ ለሚገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርሳቸው ይደረጋል፤
3. ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ለሚቀርበው ማብራሪያ ምላሽ የሚሰጠው በግዥ አፈጻጸም መመሪያ እና በጨረታ ሠነዱ ላይ ማብራሪያ መጠየቂያ ቀነ ገደብ ከማለፉ በፊት ለቀረበ ማብራሪያ ነው፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 3 የተገለጸው ቢኖርም የመንግስት የልማት ድርጅቱ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበው ማብራሪያ ጠቀሜ መሆኑን ከተረዳ የማብራሪያ መጤቂያ ቀነ ገደብ ከአለፈ በኂላ እና ከጨረታ መዝጊያው በፊት ለቀረበ ማብራሪያ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል፤
5. በጨረታ ማሻሻያ ምክንያት በሌላ አሳማኝ ምክንያት የመንግስት የልማት ድርጅቱ የጨረታ ማቅረቢያ ከመጠናቀቁ በፊት የጨረታውን ማቅረቢያ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

10.11 የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 84 ላይ በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ ፤

1. አሳማኝ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ጨረታው ጸንቶ መቆ ጊዜ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ጨረታው ከሚከፈትበት ቀናት ጀምሮ ከአሸናፊው ድርጅት ጋር የውል እስኪጸም ደረስ ከሰላሳ (30) ቀናት መብለጥ የለበትም፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ጨረታው ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የጨረታ ሂደቱን ለማጠናቀቀቅ በግዥ ግምገማው እና የማጽደቅ ስራው ላይ የሚሳተፉ አካላት በፍጥነት ኃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተገለጸው መሰረት የጨረታው ሂደት ከ30 ቀናት የማይጠናቀቅ ከሆነ ወይም በለያየ ምክንያ የጨረታ ሂደቱ ሳጠናቀቅ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ጨረታ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ከመጀመሪያው ከ3 ቀናት በላይ በማደረግ ወይም ተወዳዳሪዎች ጨረታ ጸንቶ የሚቆበትን ጊዜ እንዲያራዝሙ በደብዳቤ በመጠየቅ ችግሩን መፍታት ይችላሉ።

10.12 የጨረታ ማስከበሪያ

የጨረታ ማስከበሪያን በተመለከተ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 85 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፦

1. የመንግስት የልማት ድርጅቱ የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ ለሚያስፈልጋቸው ግዥዎች የጠቅላላ ግዥውን ግምታዊ ዋጋ መሠረት በማዬረግ ከ0.5% ያላነሰ እና 2% ያልበለጠ የጨረታ ማስከበሪያ በገንዘብ መጠን ተስልቶ ተጫራቾች እንዱያቀርቡ ወስኖ በጨረታው ጥሪው እና በጨረታ ሰነደ ውስጥ መግለጽ የሚገባው ሲሆን ከፍተኛው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ብር 2 ሚሊዮን ይሆናል።
2. የመንግስት የልማት ድርጅቱ ከፍተኛ የገንዘብ ሊያወጡ የሚችሉ ተጫራቾች በቀላሉ ከጨረታ እንዳይወጡ እና የግዥውን ሂደት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሚጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከጠቅላላ ግዥው ግምታዊ ዋጋ 2% ሳይበልጥ የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠኑን ከብር 2 ሚሊዮን በላይ ሊጠይቅ ይችላል።

- ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሚፈጸመው ግዥ ግምታዊ ዋጋው ብር 300 ሚሊዮን ቢሆን የሚጠይቀው የጨረታ ማስከበሪያ
- ዝቅተኛው መጠን ብር = 300,000,000.00X0.5/100= 1.5 ሚሊዮን
- ከፍተኛው መጠን ብር =300,000,000X2/100= 6 ሚሊዮን

3. በዚህም መሰረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተገለጸው መሰረት የጨረታ ማስከበሪያው ከ1.5 እስከ 2 ሚሊዮን ድረስ መጠየቅ የሚቻል ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተገለጸው መሰረት ድግሞ እስከ 6 ሚሊዮን ድረስ የጨረታ ማስከበሪያውን ከፍ ማድረግ ይቻላል፡፡ነገር ግን ከፍተኛ የጨረታ ማስከበሪያ ሲጠየቅ ተጫራቾች እንዳይወዳደሩ ሊያደርግ ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
4. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደ ተጫራቹ ምርጫ ከባንክ በሚሰጥ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ፣ በሁኔታ ሊይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ይሆናል፡፡

10.13 የጨረታ አከፋፈት

የጨረታ አከፋፈትን በሚመለከት በግዥ አፈጻጸም በመመሪያው አንቀጽ 87 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. ጨረታ ሰነዱ እና የጨረታ ማስታወቂው ላይ በተለጸው የጨረታ መክፈቻ ቀንና ሰዓት የመንግስት የልማት ድርጅቱ የውስጥ ኦዲት ተወካይ፣ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ከፍል ተወካይ በጨረታው መከፈቻ ወቅት እንዲገኙ በግዥ የስራ ክፍል ወይም በግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ የሚነገራቸው ሲሆን የእነዚህ ክፍሎች ተወካዮች አለመገኘት የጨረታውን መከፈት አያስተጓጉልም፤
2. የዘገዩ ጨረታዎች ወይም ተጫራቾች ጨረታው በፊት የተቀየሩ ወይም ከጨረታው ለመውጣት በደብዳቤ ከአረጋገጡ ጨረታዎች ውጪ ሁሉም የጨረታ ፖስታዎች ይከፈታሉ፡፡

10.14 ጨረታን መገምገም እና ማወዳደር

የጨረታ ግምገማን በሚመለከት በግዥ አፈጻጸም በመመሪያው አንቀጽ 88 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. ጨረታውን የተሟላ ነው ብሎ ለቀጣዩ ዝርዝር ግምገማ ሂደት ሊያሳልፈው የሚችለው በተጫራቹ የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ በመክፈቻ ስነ-ስርዓቱ ወቅት የተከፈተ እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተዘረዘሩትን የቅድመ ግምገማ መስፈርቶችን እና ተፈላጊ ነጥቦች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡
2. ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ የተጠየቁትን የህጋዊነት ማረጋገጫ ሰነዶች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ባያቀርቡም የመንግስት የልማት ድርጅቱ እንደ ጥቃቅን ጉድለት በመቁጠር ከጨረታ መዝጊያ በፊት የተዘጋጀ ወይም የተሰጠ እስከሆነ ድረስ ከጨረታ መክፈቻ በኂላ እንዲያቀርብ በማድረግ ተጫራቹን ወደ ቀጣዩ የግምገማ ሂደት እንዲገባ ሊያደርግ ይቻላል፡፡
3. አሸናፊው የሚመረጥበት የግምገማ ዘዴ፡-

    ሀ) ለግዥው ተቀባይነት ያለውን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት በመወሰን፣ ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛውን ካሟሉት ተጫራቾች መካከል ወይም ለቴክኒክ በሚሰጥ ነጥብ ዬክኒክ ማለፊያ ውጤት ከአመጡት መካከል አነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች መምረጥ(Compliance to the Specification Evaluation)፣

    ለ) ግዥው የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴት ሊወስኑ የሚችሉ የቴክኒክ መስፈርቶችን ድርሻ በመወሰን እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን አንፃራዊ ክብደት በግልጽ በጨረታ ሰነዱ ላይ በማሳየትና በእነዚህ መስፈርቶች ላይ የተመረተ የቴክኒክ ግምገማ በማካሄድ አጠቃላይ የቴክኒክ እና ዋጋ ድምር ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን መምረጥ(Merit Point Evaluation Method)፣

4. ግዥ ፈጻሚው የመንግስት የልማት ድርጅት በጨረታ ሰነዱ ክፍል 3 ላይ የግምገማ እና የብቃት መስፈርቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) ወይም 3(ለ) በመምረጥ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤
5. በማንኛውም ግዥ ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) ወይም 3(ለ) ከተቀመጡት የግምገማ ዘዴዎች ውስጥ መርጦ የመጠቀም ኃላፊነት የመንግስት የልማት ድርጅቱ ኃላፊነት ቢሆንም ከምክር አገልግሎት ግዥ ውጭ ያሉትን የግዥ ዓይነቶች ለመጠቀም የተለየ የቴክኒክ ግምገማ ለሚያስፈልጋቸው ግዥዎብቻ ቢጠቀም ይመረጣል፤
6. አሸናፊው የሚመረጥበት የግምገማ ስልት፡-

ሀ) የተለመደው የግምገማ ስልት በተናጠል (Item Wise) ቢሆንም የመንግስት የልማት ድርጅቱ በተናጠል ለመፈጸም አስቸጋሪ ስሆን ወይም በጥቅል (Lot wise) ቢፈጸሙ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚኖራቸውን እንደ ኔት ወርክ መዘርጋት፣የተሽከርካሪ ጥገና‹የሆቴል አገልግሎት፣የላቦራቶሪ ዕቃዎች አቅርቦትና ተከላ እንዲሁም ሌል ተርንኪ ፕሮጀክቶችን በዚህ የግመገማ ሰልት መፈጸም ይችላሉ፤

ለ) የግመገማው ስልት አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ መግለጽ የሚኖርበት ሲሆን ተጨራቾች ሁሉንም ዋጋ የሚሰጥባቸውን ዝርዝሮች የሚሞሉ ሲሆን በድምር አሸናፊ የሆነው የሚመረጥ ይሆናል፡፡

7. በጨረታው እኩል ዋጋ ያመጡ ወይም እኩል ተመራጭ የሆኑ ተጫራቾች በሚያጋጥሙበት ወቅት፡፡-

ሀ) በዋጋ እና በቴክኒክ ድምር ውጤት ተወዲድረው እኩል የሆኑ ተወዳዳሪዎች በቴክኒክ ከፍተኛ ውጤት ለአገኘው ተጫራች ቅድሚያ ይሰጠዋል፤

ለ) በጨረታ ሠነዱ ሊይ የተገለጸውን ዝቅተኛ የመወዳደሪያ መስፈርት አሟልተው በዋጋ ብቻ የሚወደደሩ ተጫራቾች በሚኖሩበት ጊዜ አሸናፊውን ተጫራች ለመለየት በጨረታው ከሰጡት ዋጋ በታች እንደገና ዋጋ እንዲሰጡ ተደርጎ በዋጋ ዝቅተኛ የሰጠው ድርጅት አሸናፊ ይሆናል፤

ሐ) ዋጋ እንደገና እንዲሰጡ ተደርጎ እኩል ዋጋ ከአቀረቡ አሸናፊው ድርጅት በዕጣ የሚለይ ይሆናል፡፡

10.15 የሒሳብ ስህተቶችን ስለማረም

በጨረታ ግምገማ ወቅት በተጫራቾች ስህተት ምክንያት የሚፈጸሙ የሒሳብ ስህቶችን በሚመለከት በግዥ አፈጻጸም በመመሪያው አንቀጽ 89 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. የመንግሥት የልማት ድርጅቱ በዋጋ ግምገማ ወቅት የሚደረጉ የሒሳብ ስህተቶች ያለገደብ ማስተካከል የሚቻል ሲሆን ማስተካከያውን የሒሳብ ስህቱን ለሰራው ተጫራች ቢያንስ በሶስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ማስተካከያውን መቀበል አለመቀበሉን በደብዳቤ ወይም በኤሌክትሮኒክ የግንኙት ዘዴ ምላሽ እንዲሰጥ ይጠየቃል፤

2. ተጫራቹ በሒሳብ ማስተካከያው ከተስማማ ወደ ቀጣይ ግምገማ የሚሄድ ሲሆን በሂሳብ ማስተካከያው የማይስማማ ከሆነ የጨረታ ማስከበሪያው ተወርሶ ከጨረታው እንዲወጣ ይደረጋል፤

10.16 የተሰበረ እና የተጋነነ የጨረታ ዋጋ

በጨረታ ግምገማ ወቅት የአሸናፊ ተጫራቾች ያቀረቡት ዋጋ ከወቅቱ የገበያ ዋጋ አንጻር ሲታይ በጣም ከፍተኛ ወይም የተጋነነ እና በጣም ዝቅተኛ ወይም የተሰበረ ሲሆን በግዥ አፈጻጸም በመመሪያው አንቀጽ 90 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. ወቅታዊ የገበያ ዋጋ የሚወሰደው ከታወቀ አምራች ወይም አከፋፋይ ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቱ በሚያከናውነው የገበያ ዋጋ ጥናት መሰረት ሲሆን ወቅታዊው በተቻለ መጠን ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት የተሰበሰበ ሁኖ ከአንድ ወር ያልበለጠ ሊሆን ይገባል፤
2. ለዕቃ፣ የምክር እና ከምክር ውጭ ለሆኑ አገልግሎቶች የቀረበው ዋጋ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከተጠናው የገበያ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ ከሆነ በጣም ከፍተኛ ወይም እንደተጋነነ ዋጋ ይቆጠራል፤
3. ለዕቃ የቀረበው ዋጋ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከተጠና የገበያ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ከ30% በታች ሲሆን እንዲሁም የምክር እና ከምክር ውጭ ለሆኑ አገልግሎቶች ድግሞ ከ20% በታች ሲሆን በጣም ዝቅተኛ ወይም እንደተሰበረ ዋጋ ይቆጠራል፤
4. የግንባታ ሥራ ግዥን በተመለከተ በተጫራቹ የቀረበው የጨረታ ዋጋ ከምህንድስና ግምት ዋጋ ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ15% የበለጠ ሲሆን እንደተጋነነ ወይም በጣም ከፍተኛ ዋጋ የሚቆጠር ሲሆን በተጫራቹ የቀረበው የጨረታ ዋጋ ከምህንድስና ግምት ዋጋ ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ20% በታች በሚሆንበት ወቅት እንደተሰበረ ወይም በጣም ዝቅተኛ የጨረታ ዋጋ ይቆጠራል፤
5. የቀረበው ዋጋ እንደተጋነነ ወይም በጣም ከፍተኛ ዋጋ የሚቆጠር ከሆነ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 91 መሰረት ድርድር በማድረግ ከስምምነት ካልተደረሰ ጨረታው ይሰረዛል፤

6. የቀረበው ዋጋ የተሰበረ ወይም በጣም አነስተኛ ዋጋ የሚቆጠር ከሆነ በቅድሚያ ተጫራቹ ያቀረበውን ዋጋ አሳማኝ ስለሆኑ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ተደርጎ ያቀረበው ማብራሪያ በሰጠው ዋጋ መሰረት ግዥውን ማጠናቀቅ እንደሚችል አሳማኝ ከሆነ አሸናፊ የሚሆን ሲሆን የቀረበው ማብራሪያ አሳማኝ ካልሆነ ጨረታው ይሰረዛል፡፡

10.17 ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ድርድር

በጨረታ ግምገማ ወቅት ስለሚደረግ የዋጋ ድርደር በግዥ አፈጻጸም በመመሪያው አንቀጽ 91 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

በግዥ አፈጻጸም መመሪያው መሰረት ድርድር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ በግምገማ ወቅት ከታመነበት በግዥው የገንዘብ መጠን መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቱ በተቋቋመ ኮሚቴ ወይም ቡድን ድርድር ይደረጋል፤

10.18 ድህረ ግምገማ

በጨረታ ግምገማ ወቅት እንደአስፋላጊነቱ ደህረ ግምገማ የሚያደርገው በግዥ አፈጻጸም በመመሪያው አንቀጽ 93 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. የመንግስት የልማት ድርጅቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ለግንባታ ስራዎች፣ ለአገልግሎቶች እንዲሁም ከፍተኛ ዋጋ ለሚያወጡ ግዥዎች በጨረታ ሠነዱ ላይ በተለጸው የውል ስምምነት ከመግባቱ በፊት በጊዜአቂነት የተመረጠው ተጫራች ውሉን በአጥጋቢ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያስችል ብቃት መኖሩን ለማረጋገጥ ድርጅቱ በጨረታው ለውድድር ከአቀረባቸው ውስጥ የልምድ፣ አደረጃጀት፣ ህጋዊነት፣ የፋይናንስና የቴክኒክ አቋም በመጫረቻ ሰነድ በተገለጸው አግባብ በአካል ያረጋግጣል፤
2. በድህረ-ብቃት ግምገማ ወቅት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ተጫራች የድህረ ግምገማ መስፈርቱን የማያሟላ ከሆነ ሆኖ ከተገኘ በጨረታ ሠነዱ የተገለጹትን የግምገማ መስፈርቶች አሟልቶ ሁለተኛ ከወጣው ተጫራች ተመሳሳይ የሆነ የድህረ-መረጣ ብቃት ማረጋገጫ ሊያደረግ ይችላል፡፡

10.19 ጨረታን ስለመሰረዝ

ጨረታ የሚሰረዘው በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 95 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን

ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. ጨረታ የሚሰረዘው በመመሪያው ጨረታን ለመሰረዝ ከተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ መሟላት ይኖርበታል፤
2. ጨረታው ሲሰረዝ ጨረታውን የሚገመግመው ኮሚቴ ወይም የግዥ የስራ ክፍል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት መሆኑን በማረጋገጥ ለአጽቂ ኮሚቴ ወይም ግዥውን ለማጽደቅ ስልጣን ለአለው አካል በማቅረብ ይሆናል፡፡

11. የውል አስተዳደር

11.1 ውል መፈረም

የመንግሰት የልማት ድርጅቱ በጨረታ አሸናፊው የሆነው ድርጅት ጋር የውል ስምምነት የሚፈርመው በግዥ አፈጸጸም መመሪያው አንቀጽ 99 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. ጨረታውን ያወጣው የመንግስት የልማት ድርጅት የጨረታውን ወይም የአቤቱታው ውጤት ለተጫራቾች ከገለጸበት ቀን ጀምሮ 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ከመሙላቱ በፊት የግዥ ውል መፈጸም የለበትም፤
2. የግዥ ውል የሚፈጸመው በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም የበላይ ኃላፊው ውክልና በሰጠው አካል ይሆናል፤
3. የሚፈረመው የውል ስምምነት ሠነድ በጨረታ ሠነዱ ላይ ለተጫራቾች ይፋ በሆነው የውል ክፍል መሰረት ነው፡፡

11.2 ውል ስለማሻሻል

ከውል ማሻሻያ ጋር በተያዘዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 102 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. ውል አፈጻጸም ወቅት እንደሁኔታው የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያ የመንግስት የልማት ድርጅቱን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑ ሲረጋገጥ እና በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ ነው፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የማሻሻያውን ውሳኔ ሲወስን የውል ማሻሻያው በአቅራቢው ቸልተኝነት ምክንያት ያልተፈጠረ፣በተለየ ሁኔታ ውል የገባውን ድርጅት ተጠቃሚ የማያደርግ እና የውል ማሻሻውን ማደረግ ስምምነቱን በማቋረጥ በሌሎች አማራጮች ግዥው ቢከናወን የሚያስገኘውን ተጨባጭ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

11.3 የውል ማስከበሪያ

ከውል ማስከበሪያ ጋር በተያዘዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 103 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. የውል ማስከበሪያ ለሚያስፈልጋቸው ግዥዎች የጨረታው አሸናፊ ድርጅት ውል ከፈረመበት ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥ የውለን ጠቅላላ ዋጋ ቢያንስ 10% ግዥ ፈጻሚው የመንግስት የልማት ድርጅት በጨረታ ሰነድ ላይ በሚወስነው የዋስትና ዓይነት መሰረት የውል ማስከበሪያ ማስያዝ አለበት፤
2. የግዥው መጠን ከፍተኛ እና አቅርቦቱ ቀጣይነት ያለው ሲሆን አቅራቢዎች የሚያስይዙት የውል ማስከበሪያ ዋስትና ከጠቅላው ግምታዊ ውል መጠን ላይ የሦስት ወሩ የውል መጠን ከ10% ያላነሰ እንዲሆን በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሊወሰን ይችላል፡፡
3. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በማዕቀፍ ስምምነት የሚፈጸም ግዥ አቅራቢዎች የሚያስይዙት የውሌ ማስከበሪያ ዋስትና ከጠቅላላው ግምታዊ ውሉ መጠን ላይ የአንድ ዓመቱን የውል መጠን ከ10% (አስር በመቶ) ያላነሰ ይሆናል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸውን ተግባራዊ ለማድረግ አቅርቦቱ በአንድ ጊዜ ተጠናቆ የማይቀርብ እና ቢያንስ አቅርቦቱ ከ 3 ወር በላይ የሚወስድ መሆን አለበት፡፡
   ለምሳሌ አንድ የመንገስት የልማት ድርጅት ከአቅራቢው ጋር ብር 800 ሚሊዮን የሚያወጣ የውል ስምምነት ቢገባ እና አቅርቦቱ ለአንድ ዓመት ያክል የሚቀርብ ሁኖ ዓመቱን በሙሉ ወይም በተለያየ ጊዜ የሚቀርብ ከሆነና ይህ አቅራቢ የጠቅላላ ውሉን ቢያንስ 10% (ብር 80 ሚሊዮን) ማስያዝ የማይችል በመሆኑ ግዥውን ከመሰረዝ ይልቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተገለጸውን ተግባራዊ ማደረግ የተሻለ መሆኑን በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ከወሰነ በ3 ወር በአማካይ ሊቀርብ የሚችለውን መጠን የብር 200 ሚሊዮን 10% ወይም ብር 20 ሚሊዮን የውል ማስከበሪያ እንዲያስይዝ ሊደረግ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸውን ተግባራዊ ለማድረግ የማዕቀፍ ስምምነቱ ለ3 ዓመት የሚቀርብ ቢሆንና አንድ የመንገስት የልማት ድርጅት ከአቅራቢው ጋር ብር 900 ሚሊዮን የሚያወጣ የማዕቀፍ የውል ስምምነት ቢገባ በአማካይ ሊቀርብ የሚችለውን መጠን የብር 300 ሚሊዮን 10% ወይም ብር 30 ሚሊዮን ያላነሰ የውል ማስከበሪያ እንዲያስይዝ ሊደረግ ይችላል፡፡
6. በግዥ አፈጻጸም መመሪያው መሰረት የኪራይ አገልግሎት የውል ማስከበሪያ እንደማይያዝ የሚደነግገው የህንጻ ኪራይ ወይም የተሽከርካሪ ኪራይ ሁኖ ተሽከርካሪው ወይም ህንጻው በመንግስት የልማት ድርጅቱ በጊዜአዊነት የሚያስተዳድረው ሲሆን ነው፡፡

11.4 የቅድመ ክፍያ አከፋፈል

ከቅድሚያ ክፍያ ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 105 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. የመንግስት የልማት ድርጅቱ የሚፈጸመው ግዥ ለአቅራቢው ቅድሚያ ክፍያ እንደሚያስፈለገው ሲያምን ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30% የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠን በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ እና በልዩ የውል ሁኔታዎች ላይ መገለጽ አለበት፤
2. አቅራቢዎች ከሚጠይቁት የቅድሚያ ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንደአቅራቢው ምርጫ ከታወቀ ባንክ የሚሰጥ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ አሁባቸው፡
3. ለ|ቅራቢው ከ30% በላይ የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ ለመፈጸም አሳማኝ ምክንያት ሲኖር እና ግዥውን ለመፈጸም ሌላ አማራጭ ከሌለ፣ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የቅድሚያ ክፍያው መጠን ከፍ ተደርጎ ሊከፈል ችላል፡፡

11.5 የዋጋ ማስተካከያ

ከዋጋ ማስተካከያ ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ከአንቀጽ 105-109 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. አንድ ዓመትና እና ከዚያ በላይ ለሚቆዩ ለግንባታ ስራዎች እንዲሁም ከ6 ትወራት እና

ከዚያ በላይ ለሚቆይ በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ዕቃ እና ከምክር ውጭ ለሆነ አገልግሎት ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚችል ሲሆን አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት አለበት፤

2. ለግንባታ ሥራ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከ6 ወራት በኂላ ሲሆን፣በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ ደግሞ ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3 ወራት በኂላ ለሚኖረው የዋጋ ለውጥ ነው፤
3. በአማካሪው ሰህተት ባልሆነ ምክንት 24 ወራት እና ከዚህ በሊይ ለሚቆዩ የምክር አገልግሎት ግዥዎች፣ ከ12 ወር በኂላ የዋጋ ማስተካከያ ይደረጋል፤
4. በማንኛውም ዕቃ፣የምክር አገልግሎት እና ከምክር ውጪ ለሆኑ አገልግሎቶች ላይ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ጭማሪ ከውል ዋጋው ከ20% (ሃያ በመቶ) እንዲሁም ለግንባታ ስራ ለሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ጭማሪ ከጠቅላላ የግንባታ ሥራው የውል ዋጋ ከ30% (ሠላሳ ከመቶ) በላይ ሲሆን በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃለፊ ውሳኔ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፤
5. ዋጋቸው በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ ለሆኑ ምርቶች ወይም አቅርቦቶች ወይም ዋጋ ለማስተካከል አሳማኝ የሆነ ምክንያት ሲያጋጥም እና በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተቀባይነት ሲያገኝ ለግንባታ ሥራ የዋጋ ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከ6 ወራት በፊት እንዲሁም በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ ደግሞ ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3 ወራት በፊት የዋጋ ማስተካከያ ሊደረግ ይችላል፤
6. የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ጊዜ እንደሁኔታው ከታወቀ አምራች ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በተደረገ ገበያ ዋጋ ጥናት በሚገኝ የገበያ ዋጋ መረጃ መሠረት ነው፤

11.5.1 የግንባታ ሥራ የዋጋ ማስተካከያ

ከግንባታ ሥራ የዋጋ ማስተካከያ ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 107 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፦

1. ዋጋቸው በአንጻራዊነት በአጭር ጊዜ ሊቀያየር የሚችሉ እና የግንባታ ሥራውን ለማከናወን የሚያስልጉ ዋና ዋና ግብዓቶችን እንዲሁም በእያንዳንዱ ዋና ግብዓት ሥር ሊካተቱ የሚችሉ ስብስቦችን መለየት፤
2. አስቀድሞ የጨረታ ሰነዱ ይፋ ከመደረጉ በፊት በተለዩት የወካይ ግብዓቶችን እና በወካይ ግብዓቶች ውስጥ የተካተቱ ግብዓቶችን የሚለይ ሲሆን የተለመዱት ወካይ ግብዓቶች

የሚባሉት ሲሚንቶ፣ ብረት፤ ነዳጅ እና ሲራሚክ ግብዓቶች ሲሆኑ በተመረጡት ወካይ ግብዓቶች ውስጥ የሚካተቱት ሌሎች ግብዓቶች ከዋጋ አጨማመራቸው አንጻር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ የሆኑትን በአንድ ላይ በማሰባሰብ ይሆናል፤

3. ወካይ ግብዓቶች አስቀድሞ በጨረታ ሠነዱ ላይ መገለጽ የሚኖርበት ሲሆን የዋና ዋና የግንባታ ግብዓቶች ወካይ ድርሻ የሚሰላው ከጨረታው መዝጊያ ቀን በፊት በሚኖረው በወቅታዊው የአገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር አምራች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቱ በሚያጠናው ወቅታዊ የመነሻ ዋጋ (Base Price) መሰረት ነው፤
4. የወካይ ግብዓቶች የመነሻ ዋጋ (Base Price) እና በዋጋ ማስተካከያ ውቅት የሚገኝ ዋጋ (Current Price) በተቻለ መጠን ከተመሳሳይ ምንጭ (Source) የተወሰደ ሊሆን ይገባል፣
5. የወካይ ግብዓቶች በፕሮጀክቱ ያላቸውን ድርሻ (Weighting Factor) ለማወቅ እያንዳንዱ ለግንባታው የሚያስፈልገው የወካይ ግብዓት መጠን በመነሻ ዋጋ ተባዝቶ(Total Quantity of each material x Base Price of material) ለጠቃላይ የፕሮጀክቱ ዋጋ በማከፈል ሲሆን የእያንዳንዱ የወካይ ግብዓት ተጨማሪ እሴት ታክስን ስለማያካተት አጠቃላይ የፕሮጅክቱ ዋጋም ከተጨማሪ እሴት ታክስ ያላካተተ መሆን አለበት፤
6. በፕሮጀክቱ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸው የግብዓቶች ድርሻን Weighting Factor (%) በመደመር የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸው (Adjustable) ግብዓቶች አጠቃላይ ድምር ድርሻ ማስላት ያስፈልጋል፣
7. አጠቃላይ ዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸው ግብዓቶች ድርሻ ተደምሮ ከ100% ሲቀነስ ቀሪው ድርሻ የሚሆነው የፕሮጀክት መጠን የዋጋ ማስተካከያ የማይደረግበት ሲሆን የዋጋ ማስተካከያ የማይደረግበት (Non Adjustable) ማለት Overhead, Profit እና የዋጋ ማስተካከያ የማይደረግባቸውን የግንባታ ግብዓቶችን ያካትታል፤
8. ዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸው (Adjustable) ግብዓቶች ድርሻ እና የዋጋ ማስተካከያ የማይደረግበት (Non Adjustable) ድርሻ ከፕሮጀክት ፕሮጀክት ይለያያል፤
9. የዋጋ ማስተካከያ ክፍያ ተግባራዊ የሚደረገው ዋናውን የሥራ መርሃ ግብር መሰረት ሲሆን፤ በውል ስምምነቱ ውስጥ የዋጋ ማስተካከያ ለሚፈቅድ የግንባታ ስራ በመጀመሪያው የሥራ መርሃ ግብር (Work Schedule) መሠረት በመጀመሪያ 6 ወራት ውስጥ መሠራት ያለባቸው የግንባታ ሥራዎች የዋጋ ማስተካከያ አይደረግላቸውም፤

ለምሳሌ አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ብር 460 ሚሊዮን የሚያወጣ የግንባታ ስራ ከአሸናፊው ድርጅት ጋር የዋጋ ማስተካያ የሚፈቅድ የውል ስምምነት ቢፈጸም በውል ስምምነቱ ውስጥ በመጀመሪያ 6 ወራት ውስጥ የብር 80 ሚሊዮን ብር ስራ መሰራት እንዳለበት በስራ መርሀ ግብሩ (Work Schedule) ላይ የተገለጸ ከሆነ ለብር 80 ሚሊዮን የግንባታ ስራው ዋጋ ማስተካከያ የማይደረግ ሲሆን ለቀሪው 320 ሚሊዮን ብር የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባል፡-

በውል ስምምነቱ ውስጥ በአራቱ ወካይ ግብዓቶች እና በስራቸው ለተካተቱ ግብዓቶች አጠቃላይ በፕሮጀክቱ በሚኖራቸውን ወካይ ድርሻ (Weighting Factor) መሰረት የተሰላው እና ከጨረታ መክፈቻ ቀን በፊት የነበረው የወካይ ግብዓቶች ዋጋ (Base Price) እና በዋጋ ማስተካከያ ውቅት የሚገኝ ወቅታዊ ዋጋ (Current Price) ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ተ.ቁ	ዋና ዋና ወካይ ግብዓቶች	የወካይ ግብዓቶች ዋጋ በሚሊዮን ብር	የወካይ ግብዓቶች ድርሻ(Weighting Factor)	መነሻ ዋጋ(Base Price)	ወቅታዊ ዋጋ(Current Price)	ወቅታዊ ዋጋ ሲካፈል ለመነሻ ዋጋ
1	ሲሚንቶ	60	0.15	1500	2500	1.67
2	ብረት	80	0.20	750	1100	1.47
3	ነዳጅ	40	0.10	100	130	1.30
4	ሴራሚክ	120	0.30	3000	4500	1.50
ዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት		300				
የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ዋጋ ከተ.እ.ታ ውጭ		400				

የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ዋጋ ከተ.እ.ታ ጋር	460				
ማስተካከያ የሚደረግላቸው ድርሻ(Adjustable)					0.75
ማስተካከያ የማይደረግላቸው ድርሻ (Non Adjustable)					0.25

- በውል ማሻሻያ ወይም በውል ስምምነቱ ውስጥ የተቀመጠው የወካይ ግብዓቶች ድርሻ (Weighting Factor) ከላይ በተቀመጠው አግባብ ተሰልቶ የሚመጣ እና በየክፍያው የማይቀያየር ሲሆን፤ወቅታዊ ዋጋ(Current Price) የዋጋ ማስተካከያ በሚደረግበት ወቅት አገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር አምራች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቱ በሚገኝ ዋጋ መሰረት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ የሚችል እና ለዋጋ ማስተካከያው ምክንያት የሚሆን ነው፣
- የዋጋ ማስተካከያ (Price Adjustment Factor) ፎርሙላ፡-

$$Pn = A + B\frac{(Bn)}{(Bo)} + C\frac{(Cn)}{(Co)} + D\frac{(Dn)}{(Do)} + E\frac{(En)}{(Eo)}$$

የቀመር መግለጫ

A+B+C+D+E=1

- Pn=የዋጋ ማስተካከያ ክፍያ የምስክር ወረቀት መጠን ላይ የሚተገበር የዋጋ ማስተካከያ ማባዣ ነው፤
- A=ከአጠቃላይ ፕሮጅክቱ ውስጥ የዋጋ ማስተካከያ የማይደረግለት ድርሻ (Non Adjustment Weighting)
- B=ከአጠቃላይ ፕሮጅክቱ ዋጋ ውስጥ የሲሚንቶ ዋጋ ድርሻ (Cement Weighting)
- C= ከአጠቃላይ ፕሮጅክቱ ዋጋ ውስጥ የብረት ዋጋ ድርሻ (Re-Bar Weighting)
- D= ከአጠቃላይ ፕሮጅክቱ ዋጋ ውስጥ የነዳጅ ዋጋ ድርሻ (Fuel Weighting)
- E= ከአጠቃላይ ፕሮጅክቱ ዋጋ ውስጥ የሴራሚክ ዋጋ ድርሻ (Ceramic Weighting)
- Bn= ዋጋ በሚስተካከልበት ወቅት የሲምንቶ ዋጋ (Current Price of Cement)
- Bo= ከጨረታ መክፍቻ በፊት የሲሚንቶ ዋጋ (Base Price of Cement)
- Cn= ዋጋ በሚስተካከልበት ወቅት የብረት ዋጋ (Current Price of Re-bar)

- Co= ከጨረታ መክፍቻ በፊት የብርት ዋጋ (Base Price of Re-bar)
- Dn= ዋጋ በሚስተካከልበት ወቅት የነዳጅ ዋጋ (Current Price of Fuel)
- Do= ከጨረታ መክፍቻ በፊት Base የነዳጅ ዋጋ (Price of Fuel)
- En= ዋጋ በሚስተካከልበት ወቅት የሴራሚክ ዋጋ (Current Price of Ceramic)
- Eo= ከጨረታ መክፍቻ በፊት የሴራሚክ ዋጋ (Base Price of Ceramic)

Pn = 0.25+0.15 x (2500/1500) +0.20 x (1100/750) +0.10 x (130/100) +0.30x (4500/3000) =1.375

Pn = 0.25+0.15x1.67+0.2x1.47+0.10x1.30+0.30x1.5 = 1.375

Pn = 0.25+0.251+0.294+0.130+0.450= (0.25+1.125) = 1.375

- ሁለተኛው የዋጋ ማስተካከያ እስከሚደረግ ደረስ በሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ በ1.375 በማባዛት የዋጋ ማስተካከያ ተደርጎ የሚከፈል ይሆናል፡፡
- **ለምሳሌ** ቀመሩን እና የስራ መርሃ ግብሩን ተከትሎ የቀረበው ክፍያ ቫትን ጨምሮ ብር 100 ሚሊዮን ቢሆን (100 ሚሊዮን x 1.375) = የብር 37,500,000.00 የዋጋ ማሻሻያ በማድረግ በአጠቃላይ ቫትን ጨምሮ ብር 137 ሚሊዮን 500 ሺህ ክፍያ ይፈጸማል፡፡
- **ከላይ በተቀመጠው ቀመር መሰረት** የሁለተኛ የዋጋ ማሻሻያ ሲደረግ ለምሳሌ የዋጋ መቀነስ ቢያጋጥም A (.25) +B+C+D+E=0.9 ሆኖ ሥራ ተቋራጩ የጠየቀው ክፍያ 100 ሚሊዮን ቢሆን በዋጋ ማስተካከያው መሰረት የሚከፈለው (100 ሚሊዮን x 0.9) = ቫትን ጨምሮ 90 ሚሊዮን ይሆናል፡፡

ከላይ በተቀመጠው ቀመር መሰረት የሶስተኛ የዋጋ ማሻሻያ ሲደረግ ለምሳሌ A (.25) +B+C+D+E= 1 ቢመጣ ሥራ ተቋራጩ የጠየቀው ክፍያ 100 ሚሊዮን ቢሆን በዋጋ ማስተካከያው መሰረት የሚከፈለው (100 ሚሊዮን x 1.00) = ቫትን ጨምሮ 100 ሚሊዮን ይሆናል፡

11.5.2 ለዕቃ እና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ዋጋ ማስተካከያ

ከዕቃ እና ከምክር ውጭ የሆኑ ሌሎች አገልግሎቶች ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው በአንቀጽ 108 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. በማዕቀፍ ስምምነት መሰረት የሚፈጸም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከሶስት (3) ወራት በኋላ ነው፤
2. የማዕቀፍ ግዥ አቅራቢዎች ቁጥር ከአንድ በላይ ሲሆንና የሚያቀርቡት ዕቃ ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ምርት መለያ ወይም የንግድ ስም የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ ለአቅራቢዎቹ የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ እያንዳንዱ አቅራቢ ውል የገባበት በገበያ ላይ ያመጣውን የዋጋ ልዩነት ብቻ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፤
3. በዕቃዎችና ከምክር ውጭ የሆኑ ተያያዥ አገልግሎቶች ዓይነት ላይ ተመስርቶ በውሉ ዋጋ ላይ የሚደረጉ የዋጋ ማስተካከያዎች የሚደረገው ጊዜ እንደሁኔታው ከታወቀ አምራች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቱ በተደረገ ገበያ ዋጋ ጥናት በሚገኝ የገበያ ዋጋ መረጃ መሠረት ነው፤
4. የመንግስት ልማት ድርጅቱ በሁለቱም ዋጋዎች መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት በማስላት ልዩነት በውሉ ዋጋ ላይ እንዲጨምር ወይም እንዲቀነስ በማድረግ የሚቀጥለው የዋጋ ማስተካከያ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ የተስተካከለውን ዋጋ ተፈፃሚ ማድረግ አለበት፤
5. በቀጣይ የዋጋ ማስተካከያዎች ሲደረጉ ደግሞ እንደ መነሻ ዋጋ የሚወሰደው ቀደም ብሎ የዋጋ ማስተካከያ ወቅት የነበረውን ወቅታዊ ዋጋ እና የዋጋ ማስተካከያ በሚጠየቅበት ወቅት ባሉ የገበያ ዋጋዎች መካከል ያለውን ልዩነት አሁን ባለው የውል ዋጋው ላይ በመጨመር ወይም በመቀነስ ነው፤
6. አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሠረት በወቅቱ ላላቀረባቸው እና ዘግይተው ለቀረቡ አቅርቦቶች የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው አቅርቦቶቹ መቅረብ በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡
7. የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀው ቀመር መሰረት ሲሆን የዋጋ ማስተካከያው ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት ይሆናል፤

የተስተካከለ የውል ዋጋ (Adjusted Contract Price)=   የአሁን ዋጋ (Current Price)) - የቀድሞ መነሻ ዋጋ (Base Price) + የውል ዋጋ Contract Price)
"የተስተካከለ የውል ዋጋ (Adjusted Contract Price)" ማለት ወቅታዊውን የገበያ ዋጋ ማሰረት በማደረግ በቀጣይ ዋጋ እስከሚስተካከል ደረስ የማዕቀፍ

ስምምነት አቅራቢው ለሚያቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚከፈለው የተሻሻለ የውል ዋጋ ማለት ነው፡፡
"የአሁን ዋጋ (Current Price)" ማለት የዋጋ ማስተካከያ በሚደረግበት የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ከታወቀ አምራች ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በተደረገ ገበያ ዋጋ ጥናት መሰረት ወቅታዊ ዋጋ ነው፡፡
"የቀድሞ ዋጋ (Base Price)" ማለት ጨረታው በሚከፈትበት ወቅት የነበረው የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ከታወቀ አምራች ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በተደረገ ገበያ ዋጋ ጥናት መሰረት የነበረው ዋጋ ነው፡፡
"የውል ዋጋ Contract Price)" ማለት በውል ስምምነቱ ላይ የተገለጸው እና ዋጋ ከመስተካከሉ በፊት ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ሲከፈል የነበረው የውል ዋጋ ነው፡፡

ለምሳሌ አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ለምርት ግብዓት የሚሆን ጥሬ ዕቃ በጨረታ አወዳድሮ አሸናፊ ከሚሆነው ድርጅት ጋር የአንዱ ዋጋ ብር 15,000.00 በየ3 ወሩ ዋጋ በማስተካከል ለሁለት ዓመት የማዕቀፍ ስምምነት ውል ቢገባ የዋጋ ማስተካከያ ከዚህ በሚከተለው መሰረት ይስተካከላል፡፡

ከታወቀ አምራች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቱ በተደረገ ገበያ ዋጋ ጥናት የተገኘ ወቅታዊ ዋጋ			
በጨረታው መከፍቻ ወቅት ወቅታዊው ዋጋ	ከ 3 ወር በኂላ የዕቃው ወቅታዊ ዋጋ	ከ 6 ወር በኂላ የዕቃው ወቅታዊ ዋጋ	ከ 9 ወር በኂላ የዕቃው ወቅታዊ ዋጋ
14,500.00	16,000.00	15,000.00	17,000.00

- በመጀመሪያው 3 ወር ውስጥ አቅራቢው የውል ስምምነት በገባው መሰረት በብር 15,000.00 ያቀረባል፤

- ከ 3 ወር በኋላ እስከ 6ኛው ወር ድረስ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግ ሲሆን የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ 15,000.00+(16,000.00-14,500.00)=15,000.00+ 1,500.00=16,500.00 ይሆናል፤
- ከ 6 ወር በኋላ እስከ 9ኛው ወር ድረስ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግ ሲሆን የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ 16,500.00+(15,000.00-16,000.00)=16,500.00-1,000.00=15,500.00 ይሆናል፤
- ከ 9 ወር በኋላ እስከ 12ኛው ወር ድረስ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግ ሲሆን የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ 15,500.00+(17,000.00-15,000.00)=15,500.00 +2,000.00=17,500.00 ይሆናል፤

11.5.3 የምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

የምክር አገልግሎት ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው በአንቀጽ 108 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. የመንግስት የልማት ድርጅቱ 24 ወራት እና ከዚህ በሊይ ለሚቆዩ የምክር አገልግሎት ግዥዎች፣ ከ12 ወር በኋላ የዋጋ ማስተካከያ እንደሚደረግ አስቀድሞ በጨረታ ሠነዱ ላይ መገለጽ አለበት፤
2. በምክር አገልግሎት ግዥ የውል አፈጻጸም ወቅት የአማካሪው ስህተት ባሌሆነ ምክንያት የውል መፈጸሚያ ጊዜው በመራዘሙ ለአማካሪው የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የመንግስት የልማት ድርጅቱ ሲያምንበት የዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፤

11.6 ርክክብ እና ክፍያ አፈፃፀም

ከርክክብ እና ክፍያ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው በአንቀጽ 110 እና 111 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. አቅራቢው በውሉ በተገለጸው መሠረት ዕቃዎቹን እና ተያያዥ አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ሥራዎቹን ለምንግሰት የልማት ድርጅቱ ሲያስረክብ ጊዜያዊ ርክክብ መደረጉን ዕቃ ግምጃ ቤት አስተዳደር ወይም ሌሎች የሚመለከታቸው ክፍሎች ማረጋገጫ ይሠጣሉ፤

2. የፍተሻ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ የመንግስት የልማት ድርጅቱ የአቅራቢው መገኘት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እንዲገኝ ያደርጋል፡፡
3. ፍተሻውን ያካሄዱ ባለሙያዎች አቅርቦቱን በውሉ መሠረት መከናወኑን ማረጋገጥ እና መፈረም አለባቸው፤
4. ፍተሻው እና ርክክብ ከተጠናቀቀ በኋላ በውል ስምምነቱ መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቱ ለአቅራቢው ክፍያውን ይፈጽማል፡፡
5. የግንባታ ሥራ ክፍያ ሲፈጸም ከሚፈጸመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ሥራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን በውል በሚገለጸው መጠን በመያዣ መልክ ተቀንሶ የሚያዝ ሲሆን በዚህ መልኩ ተቀንሶ የተያዘው ገንዘብ የሚለቀቅበት አግባብ በውል ስምምነቱ ላይ ይወሰናል፡፡

11.7 ውል ማጠናቀቅ

ከውል ማጠናቀቅ ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው በአንቀጽ 112 መሰረት በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

11.8 የጉዳት ካሳ

ከጉዳት ካሳ ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው በአንቀጽ 113 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ፡-

ለምሳሌ፡- የመንግስት የልማት ድርጅቱ ከአቅራቢው ጋር የተፈራረመው አጠቃላይ የውል ዋጋ 10 ሚሊዮን ብር ሆኖ በውል ስምምነቱ መሰረት በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ለማቅረብ የተስማሙ ቢሆንም አቅራቢው ለማቅረብ በተስማማበት ጊዜ ውስጥ የ6 ሚሊዮን ብር ዋጋ ያለውን አቅርቦት ቢያቀርብ እና ቀሪውን የአራት (4) ሚሊዮን ብር ዋጋ ያለውን አቅርቦት ድግሞ የማቅረቢያ ጊዜው ከተጠናቀቀ በ18ኛ ቀኑ አቅርቦ ቢያጠናቅቅ፤ቀሪውን ክፍያ እንዲከፈለው ጥያቄ ቢያቀርብ ሊከፈለው የሚችለው የገንዘብ መጠን የጉዳት ካሳ ተሰልቶ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

የነበረ ቀሪ ክፍያ በብር4,000,000.00- በውሉ ጊዜ ውስጥ ባልፈጸመው መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000 የጉዳት ካሳ ከክፍያው ላይ ተቀናሽ በማድረግ- ከውል ውጪ የዘገየበት ጊዜ 18 ቀን የጉዳት ካሳ መጠን በቀን = 4,000,000.00x1/1000/1ቀን=4,000.00

ከአቅራቢው ቀሪ ክፍያ ተቀናሽ የሚደረግ የጉዳት ካሳ መጠን በብር 4,000.00 x18=72,000.00

ብር ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ለአቅራቢው የሚከፈል ክፍያ = 4,000,000.00-72,000.00 = 3,928,000 ብር ይሆናል፡፡

11.9 ከአቅም በላይ የሆነ ችግር

ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው በአንቀጽ 115 መሰረት በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

12. አቤቱታ እና ይግባኝ አፈጻጸም

ከአቤቱታ እና ይግባኝ አቀራረብ ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ከአንቀጽ 118-124 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተገናኘ በግዥ ፈጻሚው የመንግስት የልማት ድርጅት በህጉ መሰረት ካልተከናወነ ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡት ቅሬታ ሲሆን ለመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ውክልና ለተሰጠው ኃላፊ የሚቀርበው ቅሬታ አቤቱታ የሚባል ሲሆን በቀጣይ በገንዘብ ሚኒስቴር ለተቋቋመው አቤቱታ ሰሚና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ የሚቀርበው ቅሬታ ደግሞ ይግባኝ ይባላል፤
2. በግዥና ንብረት አዋጁ አንቀጽ 74 መሰረት አቤቱታ የሚቀርበው የጨረታውን ውጤት ካወቁበት ወይም ማወቅ ከነበረባቸው ቀን ቀጥሎ በአሉት 5 ተከታታይ የስራ ቀናት ሲሆን ለቦርዱ ቅሬታ የሚቀርበው የአቤቱታውን ውጤት ከአወቁበት ወይም ማወቅ ከነበረባቸው ቀን ቀጥሎ ባሉት አምስት የስራ ቀናት ነው፤
3. አቤቱታው በስምምነት ካልተፈታ በስተቀር አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሰባት (7) የሥራ ቀናት ውስጥ የመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ውክልና በተሰጠው አካል ውሳኔውን እና የውሳኔውን ቅጅ አቤቱታውን ላቀረበው ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፤
4. አቤቱታ አቅራቢው በግዥ ፈጻሚው የመንግስት የልማት ድርጅት ውሳኔ እና ምላሽ ቅር ከተሰኘ የአቤቱታውን ውጤት ከአወቁበት ወይም ማወቅ ከነበረባቸው ቀን ቀጥሎ ባሉት

አምስት የስራ ቀናት ውስጥበገንዘብ ሚኒስቴር ለተቋቋመው አቤቱታ ሰሚና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ ቅሬታውን ያቀርባል፤

5. ቦርዱ ከተጫራቾች ይግባኝ የቀረበበት የመንግሥት የልማት ድርጅት የሰጠው ምላሽ ከደረሰው ወይም ሊደርሰው ይገባ ከነበረበት የመጨረሻ ቀን ቀጥሎ ባሉት 15 (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ለውሳኔው መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች እና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ካሉ በመጥቀስ ውሳኔ ይሰጣል፤
6. ቅሬታ ሰሚና ውሳኔ ሰጪ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ተጫራች ቦርዱ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ቀጥሎ ባለት 15 (አስራ አምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ሊያቀርብ የሚችለው በሕግ ትርጉም ረገድ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ብቻ ነው፡፡

13. ጥፋተኝነት ሪፖርት የሚቀርብበት እና የሚጣራበት ሥርዓት

የጥፋተኝነት ሪፖርት አቀራረብ እና የሚጣራበት ስርዓት ጋር በተያያዘ በግዥ አፈጻጸም መመሪያው ከአንቀጽ 125-128 በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ፡-፡

1. ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተገናኘ በግዥ ፈጻሚው የመንግስት የልማት ድርጅት በህጉ መሰረት ካልተከናወነ ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡት ቅሬታ ሲሆን ለመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ውክልና ለተሰጠው ኃላፊ የሚቀርበው ቅሬታ አቤቱታ የሚባል ሲሆን በቀጣይ በገንዘብ ሚኒስቴር ለተቋቋመው አቤቱታ ሰሚና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ የሚቀርበው ቅሬታ ደግሞ ይግባኝ ይባላል፤
2. በማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ግዥ ላይ የተሳተፈ ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ በተሳተፈበት ግዥ የሚመራበት ህግ ከሚያዝዘው ውጭ መፈጸሙ ከተረጋገጠ በግዥ ፈጻሚው በኩል የሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃዎች(የጨረታ እና ውል ማስከበሪያ መውረስ) ለፌደራል የመንግስት የግዥና ንብረት ባለስልጣን በድርጅቱ ላይ የጥፋተንነት ሪፖርት ያቀርባል፤
3. የግዥና ንብረት ባለስልጣን የጥፋተኝነት ሪፖርት በቀረበበት ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የቀረበበትን የጥፊተኝነት ሪፖርት መሰረት በማዴረግ ያለውን ማስረጃና ማብራሪያ በመመርመር አስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤
4. በባልስልጣኑ የሚሰጠው ውሳኔ የቀረበው የጥፋተኝነት ሪፖርት አሳማኝ ካልሆነ

የጥፋተኝነት ሪፐፖርቱን ውድቅ ማደረግ ወይም የቀረበው የጥፋተኝነት ሪፖርት አሳማኝ ከሆነ ደግሞ የጥፋተኝነት ሪፖርት በቀረበበት ተጫራች ወይም አቅራቢ ላይ ማስጠንቀቂያ መስጠት ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ ከማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ግዥ ላይ እንዳይሳተፍ ሊያግደው ይችላል፤

5. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተጫራቾችን ወይም አቅራቢዎችን በሚፈጽሙት ግዥ እንዳይሳፉ የማገድ ስልጣን የግዥና ንብረት ባለስልጣን ስለሆነ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በራሳቸው ተጫራቾች እንዳይወዳደሩ ማድረግ አይችሉም፤

6. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባቀረቡት የጥፋተኝነት ሪፖርት ላይ ግዥና ንብረት ባለስልጣን በሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኙ የባለስልጣኑ ውሳኔ ከደረሳቸው የመጨረሻ ቀናት ቀጥሎ ባሉት 15 (አስራ አምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል ይችላሉ፡፡

14. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14.1 ማንዋሉን ስለማሻሻል

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የግዥና ንብረት ባለሥልጣን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህንን የግዥ አፈጻጸም ማንዋል ሊያሻሽል ይችላል፡፡

14.2 ማንዋሉ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

1. ይህ ማንዋል ቀደም ብለው የወጡ የግዥና ንብረት አዋጅ ቁጥር 1333/2016፣የግዥ አፈጻጸም መመሪያ 1070/2017 መሰረት በማድረግ የወጣ የአሰራር ማንዋል ስለሆነ ማንዋሉ በደብዳቤ ከደረሳችሁ ቀን ጀምሮ የአፈጻጸም መመሪያው ተግባራዊ በሚደረግባቸው የመንግስት ልማት ድርጅቶች ላይ ሁሉ ተግባራዊ ይሆናል፡፡
2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም በዚህ ማንዋል ያልተሸፈኑ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚፈልጉ አሰራሮችን ብቻ በመለየት እና በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በማጸቅ ስራ ላይ ማዋል ይችላሉ፡፡

አዲስ አበባ

ህዳር 16/ 2018 ዓ.ም

መሠረት መስቀሌ

የኢ.ፌ.ድ.ሪ የመንግስት የግዥና ንብረት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር

አባሪ 1፡-በመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥ አፈጻጸም ሂደት ውስጥ የሚኖረው ኃላፊነትን የሚሳይ መግለጫ(Matrix)

ተ.ቁ	ዝርዝር ስራዎች	በግዥ ሂደት ውሳኔ ውስጥ የሚሳተፉ አካላት					
		ተጠቃሚ ክፍል	የግዥ የስራ ክፍል	ግምጋሚ ኮሚቴ	የቴክኒክ ኮሚቴ	አጽዳቂ ኮሚቴ	የበላይ ኃላፊ
1	**ቅድመ ጨረታ ወቅት**						
1.1	የዕቅድ ፍላጎት ማቅረብ	✓					
1.2	የዕቅድ ፍላጎት መሰብሰብ		✓				
1.3	የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት		✓				
1.4	የግዥ ዕቅድ ማጽደቅ						✓
1.5	የግዥ ዕቅድ ማሻሻል						✓
1.6	የግዥ ሥልቶችን ማጽደቅ						✓
1.7	በዕቅድ ውስጥ የጸደቁ የግዥ ዘዴዎች የግዥ ሂደቶችን መጠየቅ	✓					
1.8	በዕቅድ ውስጥ ያልጸቁ የግዥ ዘዴዎች የግዥ ዘዴዎችን መፍቀድ						✓

1.9	የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎችን መጠየቅ		✓				
1.10	የልዩ ፈቃድ ጥያቄዎችን ማጽቅ						✓
2	**በጨረታ ወቅት**						
2.1	የቴክኒክ ግምገማን ማድረግ				✓		
2.2	የቴክኒክ ግምገማን ማጽደቅ					✓	
2.3	የአንድ አቅራቢ እና በዋጋ ማቅረቢያ የግምገማ ውሳኔ ኃሳብ ማቅረብ፣		✓	✓			
2.4	የአንድ አቅራቢ እና በዋጋ ማቅረቢያ የግምገማ ውሳኔ ኃሳብ ማጽደቅ፣						✓
2.5	ከአንድ አቅራቢ እና ከዋጋ ማቅረቢያ ውጭ ያሉ የግዥ ዘዴዎችን የግምገማ ውሳኔ ኃሳብ ማቅረብ፣		✓	✓		✓	
2.6	ከአንድ አቅራቢ እና ከዋጋ ማቅረቢያ ውጭ ያሉ የግዥ ዘዴዎችን የግምገማ ውሳኔ ኃሳብ ማጽደቅ፣					✓	
2.7	የዋጋ ድርድር ማድረግ፣					✓	✓
2.8	ከተጫራቾች የሚቀርቡ አበቴታዎችን ምላሽ መስጠት፣						✓
3	**ከጨረታ በኋላ**						
3.1	የውል ስምምነት መፈረም፣						✓

3.2	ውል ማስተዳደር፣		✓				
3.3	የውል ማሻሻያ ማደረግ፣						✓
3.4	ሌሎች ለበላይ ኃላፊ የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች	✓			✓		

አባሪ 2፦የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ኃላፊነት

የግዥ አፅዳቂ ኰሚቴ ሰብሳቢ ኃላፊነት፣

የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመንግስት የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚመረጥ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴን የስብሰባ ቀንና ሰዓት ይወስናል ስብሰባ ይመራል፡፡
2. ከጨረታ ሂደት ጋር የተያያዙ ተግባራት የመንግስት ግዥ አዋጅና የመንግስት የልማት ድርጅቶች መመሪያውን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ያረጋግጣል

4.2 የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ፀሐፊ ኃላፊነት፣

የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ፀሐፊ በመንግስት የልማት ድርጅተ የሚመደብ ሆኖ የሚ ከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. ማንኛውንም የአጽዳቂ ኮሚቴ የስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ይመዘግባል፣ ኮሚቴው የተሟሉ ሠነዶች እና መዛግብቶች እንዲኖሩት ያደርጋል፣ በጥንቃቄ ይይዛል፡፡
2. በውሳኔ አሠጣጥ ሂደት ከአቅራቢዎች ጋር የተደረገ ውይይት ካለ በቃለ ጉባዔ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡
3. ከኰሚቴው ሰብሳቢ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት አጀንዳ ያዘጋጃል፡፡
4. በአፅዳቂ ኮሚቴ ስብሰባዎች ድምፅ ይሰጣል፡፡

4.3 የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ስብሰባ ሥነጠሥርዓት፣

1. የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ሊሰበሰብ የሚችለው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ሲሆን ውሣኔ የሚተላለፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፡፡
2. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ በውሳኔ አሰጣጥ ወቅት እኩል ድምጽ በሚኖረው ጊዜ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
3. በድምፅ አሰጣጥ ወቅት በሃሳብ የተለየ አባል ሲኖር የተለየበት ምክንያት በቃለጠጉባዔው እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡

አባሪ 3-ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማቅረቢያ ቅጽ

ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ዝርዝር ተግባራት														
ተ.ቁ	የሚገዛው ዕቃ፣ የግንባታ ስራ ወይም አገልግሎት መግለጫ	ግዥው የሚፈጸምበት የገንዘብ ምንጭ			ለግዥው የተያዘው በጀት		የግዥው ዓይነት*	የግዥው ዘዴ**	የግዥው ምድብ***		ግዥውን ለመፈጸም የሚወስደው ጊዜ			ምርመራ
		ከውስጥ ገቢ	ከብድር	ከእርዳታ	ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት					የጨረታ ጥሪው የሚካሄድበት ቀን	ውል የሚገባበት ቀን	ግዥ ርክክብ የሚካሄደበት ቀን	
	1	2	3	4	5	6	7	8		9	10	11	12	13

✶የግዥው ዓይነት የሚለው፡-ዕቃ፣ የግንባታ ሥራ፣ የምክር እና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች የሚገለጽበት ነው፡፡

✶✶ የግዥው ዘዴ የሚለው፡-ከግልጽ ጨረታ፣ የተገደበ፣ ጨረታ ….ወዘተ የሚገለጽበት ነው፡፡

✶✶✶ የግዥው ምድብ የሚለው፡-ዓለም አቀፍ ወይም አገር ውስጥ በማለት የሚገለጽበት ነው፡፡